# መንፈስ ቅዱስ እና እኛ

መንፈስ ቅዱስ፣ የመንግሥት ገዢ

በዶ/ር ማይልስ ሙንሮ

ተርጓሚ ደረጀ በቀለ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 2001 ዓ.ም.

# መንፈስ ቅዱስ እና እኛ

**ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው**
**The Most Important Person on Earth**
**ከሚለው መጽሐፍ ነው::**
**Dr. Myles Munroe**

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም
እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው::

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RPTR-31 3M

## መታሰቢያነቱ

መነሻውን በመፈለግ ላይ ላለው የሰው ልጅ ህያው መንፈስ::

ያለንበትን የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ተግዳሮቶች በመጋፈጥ ላይ ላሉ የአገራት መሪዎች::

በተስፋ ቢስነት ውስጥ ሆኖ የነገሮችን ትርጉምና ተስፋ በናፍቆት ለሚጠባበቀው ላለንበት ክፍለ ዘመን የሰዎች ልብ::

የሰው ልጆች እንደገና መንግስቱን እንዲያገኙ ካለኝ መሻት ጋር ቆመው ለሚያገለግሉና ለረዱኝ ቤተሰቦች::

ለባለቤቴ ሩትና በምድር ላይ ላሉኝ የከበሩ ሃብቶቼ ለሆኑ ልጆቼ ቻሪሣና ቻኢሮ::

ዘላለማዊ፣ የማይሞት፣ ጥበብን የተሞላና የሁሉ ነገር ፈጣሪ ለሆነ ንጉሥና አምላክ::

የእውነትና የሕይወት ምንጭ ለሆነው ለተከበረው ሰማያዊ ገዢ::

መንግሥታት፤ ህዝቦቻቸው እየተጋፈጡት ባለው መሠረታዊ የሆነ ችግር ዙሪያ ለመሥራት ሥልጣኑም፣ ችሎታውም ይሁን መሻቱ የላቸውም።

አብዛኛውን ጊዜ በዓለም ላይ የሚገኙ መንግሥታት ከችግሮቹ ጋር አብረው የሚጓዙ ይመስላሉ፤ በመሆኑም ብዙ ሰዎች፤ እነዚህን ችግሮች ለማቃለል የሚችለው ማን እንደሆነ ለማወቅ ይፈልጋሉ። ዓለም ዓቀፋዊ የሆኑ ችግሮቻችንን ለምሳሌም፤ ሽብርተኝነትን፣ ጦርነትን፣ ወንጀልን፣ ርሃብን፣ ኤድስን፣ የኢንፍሎዌንዛ ወረርሽኝንና የኢኮኖሚ አለመረጋጋትን እንዴት ማስወገድ እንደምንችል ማወቅ ያስፈልገናል። አስፈላጊ የሆነው ሥልጣን፣ አቅምና መሻቱስ ያለው ማነው?

ግለሰቦች፣ አገራትና አንዳንድ ማህበራትም ሳይቀሩ ከእነኝህ ችግሮች እንዳንዶቹን ለማቃለል በመስራት ላይ ይገኛሉ፤ ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ ዘላቂ የሆነ ለውጥ ለማምጣት አስቸጋሪ ነው።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውሳኔዎቹንና ፕሮግራሞቹን ለማስፈፀም የሥልጣንና የሃይል ውስንነት አለበት፤ በመሆኑም ስኬታማ ባለመሆኑ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ጥብቅ ፍተሻና ቁጥጥር እየተደረገበት ይገኛል።

ለችግሮቻችን እውነተኛ የሆኑ መፍትሔ ለማግኘት አለመቻላችን አብዛኛውን ጊዜ በግል ሕይወታችንም ላይ ተንጸባርቆ ይታያል። ገንዘብ ነክ የሆኑ እጥረቶች ሲነሱ፤ ግላዊ የሆኑ ራእዮቻችን ይከስማሉ፣ ወይም ደግሞ ልጆቻችን ራሳቸውን ለማጥፋት ጎዳና ላይ የሚራመዱ ሲመስሉ "ማነው መቆጣጠር የሚችለው?" እያልን ራሳችንን እንጠይቃለን። ይህን ማድረግ የምንችለው በእርግጠኝነት እኛው ራሳችን መሆናችን አይሰማንም። በቤተሰባችን ውስጥ እንደገና ሥርዓትና ሰላምን፣ ሁለንተናዊ ደህንነትን ለመፍጠር እንፈልጋለን። ሁኔታዎቻችንን ለመለወጥ የሚያስፈልገንን ሥልጣንና ሃይል እንሻለን።

በዚህ ምክንያት ነው በሕይወት ማናቸውም ሁኔታዎች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች - ዓለም ዓቀፋዊ ይሁኑ ግለሰባዊ በቁጥር አንድ ላይ ያሰለፉት መሻታቸው *ኀይል እንደሆነ ያመነኩት። ኀይል በሁኔታዎች ላይ ተጽእኖ ማሳደርና የመቆጣጠር ብቃት* ነው።

ኀይል የሰው ልጆች ሁሉ ዋነኛ ጉዳይ ነው። ሰዎች ምናልባት በቀጥታ በዚያ መንገድ ላይገልጹት ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ ታላቁ መሻታቸው፣ ያሉበትን ሁኔታ መቆጣጠርና መልክ ማስያዝ፣ ግለሰባዊና ቤተሰባዊ ሕይወትን መቀየርና ለራሳቸውም የተሻለ ሕይወት ማመቻቸት ነው። ሚሊየነር ለመሆን የሚፈልግ ሰው የሚፈልገው በርግጥ ገንዘቡን አለመሆኑ ለዚህ ነው። ይልቁን ኀይልን ይፈልጋል። የሚበላውን ነገር ምንነት፣ የት እንደሚኖር፣ ምን አይነት መኪና እንደሚነዳ፣ ሕይወቱን እንዴት እንደሚመራ መቆጣጠር የሚያስችለውን ብቃት ይፈልጋል።



እንዲያም ሆኖ በዚህ ፕላኔት ላይ የሚኖር እጅግ ባለጠጋውም ይሁን የመጨረሻው ደሃ ሰው ሁለቱም ይሄ መሻት አላቸው። ይህ ታላቅ የሆነ የሰው ልጆች ጉዳይ እውነት፣ ለቤት እመቤቶችም ይሁን አለቆች ለሆኑ የሚሠራ ነው። ሰውዬው የየትኛው አገር ዜጋ ወይም ጎሣ አባል መሆኑ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ማናቸውም ሰው ሕይወቱንና በዙሪያው ያለውን ዓለም መቆጣጠር ይፈልጋል። እናም አብዛኛውን ጊዜ ይህንን ለመቆጣጠር አለመቻል ወደ ስጋትና ስቃይ ያመራናል።

በዓለማችን ዙሪያ ያለው ምስቅልቅልና ዋስትና የሌለው ግለሰባዊ ሕይወታችን ባህሪ፤ ጥልቅ ፍላጎቶቻችንንና እጅግ ወላኝ የሆኑ ችግሮቻችንን ለማቃለል ሥልጣንም ይሁን ኀይል እንደሌለን ይገልጻሉ። ስለዚህም ነው አብዛኞቻችን ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን፣ ኀያላንንና ተሰሚነት ያላቸውን የምናደንቀውና እነርሱን ለመምሰል የምንሞክረው። ስለዚህም ነው ልዩ የሆኑ የሰው ልጅ ብቃቶችን ለማዳበር ተስፋና እምነት በውስጣችን የሚያቆጠቁጠው። እንቆቅልሾቻችንን ለመፍታት በራሳችን ችሎታ ለመተማመን እንፈልጋለን። ለምሳሌ፡-

- ✓ በርካታ ሰዎች በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተከበሩትን የኖቤልና የቴምፕልተንን የመሳሰሉ ሽልማቶችን ይቀዳጃሉ።
- ✓ ህዝባዊ ፍቅር የተለኙ የቴሌቪዥን መርሃ ግብሮች፤ *ሚሊየነር ለመሆን የሚፈልግ ማነው? በድርድር ወይስ ያለድርድር? የሕይወት ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ በሕይወት መኖር፣ የአሜሪካ ኮከቦች* (የአሜሪካ አይዶል) በሚሉ ርእሶች ያለማቋረጥ በአየር ላይ ይውላሉ።
- ✓ *ታይምስ እና ኒውስ ዊክን የመሳሰሉ ታዋቂ መጽሄቶች "የዓመቱ ታላቅ ሰው" ማን እንደሆነ ለመለየት ይሞክራሉ።*

በአሁኑ ጊዜ አርባ በሚያህሉ አገራት ውስጥ "የአሜሪካን ኮከቦች" ከተባለው መርሃግብር ጋር የተመሳሰሉ ስርጭቶች ይተላለፋሉ። ፍላጎቱ ዓለም ዓቀፋዊ ነው፤ ብሔራዊ፣ ባህላዊና ጎሣዊ የሆኑ መስመሮችን ሁሉ ዘልቆ ያልፋል። ዓላማውም ምርጥ ሆኖ እንዲቆጠርና የበለጠ የመቆጣጠር ኀይል እንዲኖረው ነው። ሰዎች በመገናኛ ብዙሃን ወይም በሩጫ ውድድር ወይም በንግድ ወይም በሃይማኖት ኮከብ ሆነው ለመገኘት ይፈልጋሉ፤ ምክንያቱም ኮከቦች ተጽእኖን ማሳደር ይችላሉ። ተጽእኖም በሁኔታዎችና በሌሎች ሰዎች ላይ ኀይል እንዲኖርህ ያደርጋል። እነኝህ የቴሌቪዥን መርሃግብሮች ስኬታሞች ናቸው፤ ምክንያቱም የሰው ስር ጠልቆ የዘቀጠበትን ባህል፣ ማህበራዊ ኑሮና ኢኮኖሚ ለመቆጣጠርና ከችግሩም ለማምለጥ ብዙዎች መንገድ በመፈለግ ላይ ስለሚገኙ ነው። እኛ ሁላችን ኀይልን እንፈልጋለን፤ ምክንያቱም ሕይወት መረጋጋት የሌላት፣ ፍርሃትና ስቃይ የሞሉባት በመሆኑ ነው።

ምናልባትም ይህ ታላቅ የሆነ ሁኔታዎቻችንን የመቆጣጠር መሻታችንና በውስጣችን የተጠነሰሰ ምኞት ሊሆን ይችላል፤ "ልዩ ሰው" "የሌሊት ወፍ

የሰው ልጆች ወደዚህ ዓለም የመጣነው ስለ ራሳችንና ስለምንኖርበት ዓለም ያሉንን ጥልቅ የሆኑ ጥያቄዎች መመለስ ከሚያስችል፤ ከአሠራር መምሪያ ጋር እና ከተተካከለ ከፊብራኪው መመሪያ ጋር እንደሆነ እምናለሁ:: ከእነዚህ አንዳንዶቹ መረጃዎች በእኛ ውስጥ የተቀመጡ ናቸው፤ ቀሪዎቹ ደግሞ በፈጣሪያችን ወይም በፊብራኪያችን በጽሑፍ ሆነው ለእኛ ተሰጥተውናል:: ስለሕይወት ባሉን ጥርጥሮችና ግራ መጋባቶች የተሞላንበት ምክንያት እውነተኛ ከሆኑት ከእነዚህ መመሪያዎች ጋር በመለያየታችን ነው:: ውስጣዊ የሆነ የአሠራር ሂደቶቻችንን ማስላሰል ወይም ያሰንን እምቅ ኀይል ለመረዳትና እንዴት መሥራት እንደሚገባን የሚነግረንን የሕይወት መመሪያ ማንበብ እቁመናል:: ስለዚህም ነው የዓለምን የራሷን ዓላማና እንዴት መስራት እንደሚጠበቅባት ለማየት የተሣነን::

ሕይወታችን የተሰበረውን አንድ ነገር ለመጠገን ሞክረን ያልተሳካልን ቢሆን፤ ምክንያቱ የፊብራኪው መመሪያ የጠፋብን በመሆኑና እንዲህ የሚለውን ወሳኝ መመሪያ ባለማንበባችን ነው፤ "በራስህ ልትጠግነው አትሞክር:: ወደ ፊብራኪው ተመለስ::"

ፊብራኪው ነው . . .

- ✓ ወጥ የሆነ የስራው ንድፍ ያለው::
- ✓ በእኛ ውስጥ የተሰበረውን ነገር እንዴት መጠገን እንዳለበት የሚያውቀው::
- ✓ ከሕይወታችን የጠፉ ነገሮችን መተካት የሚችለው::

የፊብራኪውን ቀዳሚ እቅድ ስናውቅ፤ የሕይወት ዓላማችንን እናውቃለን፤ በውስጣችን ያሰውን ኀይልና በዚህ ዓለም ውስጥ ያለንን ታላቅ ሚና እንገነዘባለን::

## መንግሥታዊ አስተዳደር

ፊብራኪያችን ሲያስበን አሁን እንዳለንበት ሁኔታ ዓይነት በአገራት፣ በሰው ቡድኖች፣ በቤተሰብ መካከል፣ በአታላይነት፣ በአድሏዊነት፣ በጭቆናና በጥፋት የተከፋፈለና የተበታተነ ሕይወት እንዲኖረን አድርጎ አልነበረም የሠራን:: በእርሱ ሃሣብ ውስጥ የተጠነሰሰው፣ በሥርዓት የተደራጀ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ለግለሰባዊና ለማህበረሰብ እንዲሁም ለመላው የሰው ልጆች ከፍ ያለ ጥቅም፤ ከሌሎች ጋር በመተባበር ሙሉ ኀይሉን መጠቀም የሚችልበት ሕይወት ነበር::

*የፈጣሪ የመጀመሪያው ንድፍ በምድር ላይ መንግሥታዊ አስተዳደርን* ማስፈን ነበር:: ይህም የርሱ የራሱ የሆነው የታላቁ መንፈሳዊ መንግሥት ነጸብራቅና ቀጣይ ክፍል ነበረ:: ይህ ምድራዊ መንግሥት እየሰፋ



የሚሄድና ሰዎችን (1) ዜጎቹ አድርጎ ያቀፈ (2) መንግሥቱን የሚወክሉ የአካባቢ ምክትል ገዥዎች (ተጠሪዎች) ነበር:: ተሰጥቶን የነበረው ተግባራዊ ግዳጅም ይህ ቅኝ ግዛቱ የመንግሥቱን ባህርይ እንዲመስል መለወጥ ነበር::

ከፈጣሪ ሉአላዊ ከሆነ የቸርነት ባህሪ የተነሣ የቅኝ ግዛቱ የመጀመሪያ ባህርይ ሰላማዊና ውጤታማ ነበር:: የእርሱ ፍላጎት የዜጎች ሁለንተናዊ ደህንነት፣ መብዛትና መባዛትም ነበር:: የእርሱ አስተዳደር ፍጹማዊ፣ አገዛዙም በርኅራኄ የተሞላ ነው::

## የሁለት ዓለማት የጋራ ግንኙነት

ለዚህ እቅድ ስኬታማነት ቁልፍ ነገር የሁለቱ ዓለማት የጋራ ግንኙነት መመሥረትና ግንኙነቱም በእናት አገርና በቅኝ ግዛቱ መካከል ሳይቋረጥ መቀጠሉ ነበር:: ይሄው ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ ስኬታማ የነበረበት ምክንያት - ከሉአላዊው እስከ ግለሰብ ዜጋ ድረስ - ዜጋው የንጉሡን መሻትና እቅድ እንዲያውቅ በሚያስችል ልዕለ ተፈጥሯዊ ግንኙነት ቀጥተኛ ትስስር ስለነበር ነበር:: ያ ግንኙነት የሆነው በሰው ልጆች ውስጥ በሚኖረው በሉአላዊው መንፈስ - እርሱም መንፈስ ቅዱስ - ነበረ::

ይህንን የሁለት ዓለማት ውስጣዊ ግንኙነት ለመረዳት፤ *የልዕለ ተፈጥሮን ንድፈ ሃሳብ መመልከት ያስፈልገናል፤* በተጨማሪም *መንፈስ ቅዱስ* የሚለውን ቃል ሲሰሙ ሰዎች ለሚኖራቸው የተለያዩ የተሳሳቱ አመለካከቶች ተገቢውን መልስ ልንሰጥ የግድ ነው:: እሁን እያወራሁ ያሰሁት ስለሆነ አይነት "ኀይል"፣ "ደመና" ወይም "ስሜት" አይደለም - ይልቁን ስለስብእና ነው:: የምናገረው ከእኛ ጋር ግላዊ ግንኙነት ለማድረግ የስብእና ከስብእና ጋር ግንኙነት ለመመስረት ከአለንበት ድረስ ስለዘለቀው ፈጣሪ ነው::

## የልዕለተፈጥር ጽንሰ ሃሳብ

ልዕለ ተፈጥሮ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ አይገኝም፤ ይሁን እንጂ በዚያ የሰፈረውን ንድፈ ሃሳብ ቁልጭ አድርጎ ያብራራል:: ልዕለ ተፈጥሮ ማለት በአጭሩ ከተፈጥሯዊው ነገር "ውጭ የሆነ" ወይም "በላይ የሆነ" ማለት ነው:: ከተፈጥሯዊው ነገር ይልቅ መንፈሳዊውን የሚያመለክት ነው:: ልዕለ ተፈጥሯዊው ዓለም ከተፈጥሮው ዓለማችን በላይ የሆነ ነው:: የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂ የተርሴሱ ሰው ጳውሎስ ይህንን ንድፈ ሃሣብ የማይታየው ወይም የተሰወረው ሲል ይገልጸዋል::

በመሆኑም ልዕለ ተፈጥሯዊው ዓለም የማይታይ ወይም የተሰወረ ዓለም ሲሆን እኛ ከምንኖርበት ፍጥረታዊ ዓለምም የተለየ ነው:: እቻ ያልተገኘለት ወጣቱ መምህር የናዝሬቱ ኢየሱስ፤ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም

አይደለም. . . . አሁን ግን መንግሥቴ ከሌላ ስፍራ ነው ሲል ይህንን ማመልከቱ ነበር::

አንድ ሰው በፈጣሪው ንጉስ ልዕለ ተፈጥሯዊ ዓለም ውስጥ ሲገባ፤ ይህ ልምምድ ከሉዓላዊው መንግሥት ጋር ግንኙነት ማድረጉን የሚያመለክት ነው:: ከዚህ የማይታይ ዓለም ጋር እንዲገናኝ ቁልፉ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ በእርሱም፤ ወደ ምድር ይዞት የሚወርደውን የንጉሡን ሃሣብና ልብ ማግኘት ይችል ዘንድ ግንኙነቱን ያደርጋል::

በዚህ በማይታየው ዓለም መንግሥትና በሚታየው ፍጥረታዊ የምድር መንግሥት መካከል ያለው የግንኙነት ባህርይ፤ በሁለቱ ዓለማት መካከል ግንኙነቱ የሚቻል ይሆን ዘንድ ያደረገውን ስንመዝነው ከቶውን ስፍር በሌለው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ያረፈ ነው::

## የመንግሥት ጽንሰ ሃሣብ

የማይታየውን ዓለም መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ማድነቅ እንድንችል፤ መንግሥት የሚለው ሃሳብ በምድር ላይ በነበሩት ጥንታዊ የባቢሎንና የግብፅ ሥልጣኔዎች ዘመን እንዳልተጀመረ ልንገነዘብ የግድ ነው:: ቃሉ ፈጽሞውኑ ምድራዊ አይደለም:: መንግሥት የሚለው ንድፈ ሃሣብ መሠረት ያደረገው፤ ፈጣሪ ሁለቱንም የማይታየውንና የሚታየውን ዓለም የባህርዩ መገለጫዎችና ውክልናዎች አድርጎ ለመፍጠር በነበረው በራሱ ፍላጐት ነው::

በህልውና ውስጥ ሀሣቦች እጅግ ብርቱ ኃይሎች ናቸው:: ታላላቅ ሀሣቦች እንዴት አድርገው ትውልድን በመሻገር የሰዎች የፈጠራ እንቅስቃሴና ለምርታማነታቸውም እንቀሳቃሽ ምንጭ በመሆን እንዳገለገሉ እናያለን:: ለተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ሀሳብ የመነሻ ነጥብ ነው:: ሀሣቦች ሲፈጠሩና ሲሞከሩም የበሰሉና ተግባራዊ ጽንሰ ሀሣቦች ይሆናሉ::

የምቹ መንግሥት ጽንሰ ሀሣብ ልዩ የሆነ ባህርይ ያለው ፈጣሪ - ንጉሥ ብቻ ሊጠነሰስውና ሊመሠርተው የቻለ በመሆኑ እጅግ ውበት ያለው ነው:: የተገኘንበትን ንጉሥና የመንግሥቱን ምንነት ልንገነዘብ ያስፈልገናል::

ንጉሥ የሚለው ቃል የሚያመለክተው፤ ዋናኛ ለሆነው ሀሣቡና በመንግሥቱም ውስጥ ላሉ ዜጎች ሁሉ ጥቅም በቁጥጥሩ ሥር ባለው ግዛቱ ውስጥ ያለውን የምርታማነት እድገትና ትርፋማ የሆነ አገልግሎት የሚቆጣጠርና የሚያስተዳደር ግለሰብ ወይም ስብእና ነው:: እርሱ የሚያስተዳድረው የሥልጣን ክልልና ከባቢ የእርሱ "ግዛት" ወይም "ዓለም" ተብሎ ይጠራል:: ግዛቱን ስኬታማ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድር ንጉሥ፤ የመንግሥት ጽንሰ ሀሣብ መነሻ ሀሣብ ነው::



በመሆኑም መንግሥት ፍፁም የሆነ የፈጣሪ መለኮታዊ የፈጠራ ሥራ ምሣሌ ነው:: የግዛቱ የመጀመሪያው ዓለም መንግሥተ ሰማይ ተብሎ ይጠራል:: መንግሥተ ሰማይ የመጀመሪያ መንግሥት ሲሆን የሌሎች መንግሥታትም መነሻ ምንጭ ነው:: ከሱ በፊት ሌሎች መንግሥታት አልነበሩም፤ ፍጥረታዊ የሆነው ማንኛውም ነገር ከቶውን ሊመሣሰለው አይችልም:: ይህ መንግሥት የመጀመሪያው እውነተኛ መንግሥት ነው፣ ምክንያቱም የመጀመሪያው ንጉሥ ፈጥሮታልና:: መንግሥተ ሰማይ አሁን ላሉት መንግሥታት ሁሉ ፍፁምና ብቸኛው መታያ (ምሳሌ) ነው::

ፈጣሪው - ንጉሥ ፍጹማዊ የሆነ መንግሥቱን ከማይታየው ዓለም ወደሚታይ ዓለም ለማስፋት ባቀደ ጊዜ፣ ውጤቱ የመለኮታዊ ህልውናው ልዩ ማረፊያ የሆነው ግዝፈ ዓለምና በእርሱም ውስጥ ያለች ምድር የምትባል ፕላኔት መፈጠር ነበር:: የተርሴሱ ሰው ጳውሎስ በቆላስይስ ከተማ ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች፤ የዚህን መለኮታዊ የአፈጣጠር ሂደትና አዘረጋግ (extension) በፃፈላቸው ውስጥ ሊያብራራላቸው ሞክሯል፤ *"የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና . . . ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥረዋል"*

መንግሥተ ሰማይና ቅኝ ግዛቱም የሆነችው ምድር ህልውናቸውን ጠብቀው ያሉት በፈጣሪ ንጉሣችን ፈቃድ አማካይነት ነው:: በመሆኑም አስቀድመን የመንግሥትን ጽንሰ ሀሣብና በምድርም ሳለን በመንግሥቱ ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለብን ካልተገነዘብን በስተቀር በምድር ላይ ሰዎች የተፈጠሩበትን ዓላማ ልንረዳው ፈጽሞ የማይቻል ነው::

በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚፈጠረው የሁለቱ ዓለማት ግንኙነት በምድር ላይ ያለንን ዓላማ ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችለን ነው:: መንግሥታዊ አስተዳደር፤ ስለማንነታችን ትርጉምና በዙሪያችን ስላለው ዓለም ላለን ጥያቄና ፍተሻ ሁሉ የምናገኘው የመጨረሻው መልስ ነው::

እየደበዘዘ የመጣውን የፈብራኪያችንን "የአሠራር መመሪያ" ከዚህ በኋላ ቸል ልንለው አንችልም:: ወደ ፈጣሪ - ንጉሣችን የመነሻ ሀሳብ እንመለስ፤ ያን ጊዜ የመንግሥቱን የቅኝ ግዛት ንድፎች ሀሳብ ልንረዳ እንችል ይሆናል::

## ለመነሻ

በመጀመሪያው የንጉሥ ቃል ነበረ። ይህም ቃል ራሱ ነበር፤ ከእርሱም ያልተለየ ነበር። ይሄ ቃል በመጀመሪያውም በእርሱ ዘንድ ነበረ። የሆነው ነገር ሁሉ ወደ ህልውና የመጣው በንጉሡ ቃል በኩል ነው፤ ምንም ዓይነት ሌላ የሕይወት ምንጭ አልነበረም። በእርሱ ቃል ውስጥ ሕይወት ነበረ፤ ይህም ሕይወት ለጨለመውና ግራ ለተጋባው የሰው ዘር የንጉሡን እውቀትና መንግስቱንም ገለጠላቸው። ነገር ግን ምንም እንኳን የዚህ እውቀት ብርሃን እያንጸባረቀ ቢያበራም፤ በጨለማው መንግሥት ውስጥ መቀመጥ የመረጡት ሲያዩት አልቻሉም።

በመጀመሪያው፤ ንጉሡ ለመንግሥቱ ቅኝ ግዛትን መሠረተ። ቅኝ ግዛቱም ጠፍና ያላደገች ነበረች፤ በእርሷም ውስጥ ሕይወት አልነበረም። የንጉሡ ገዢ በንጉሡ ቃል በኩል በቅኝ ግዛቱ ውስጥ ሥርዓትንና የመንግሥቱን በጎ ተጽእኖ ለማምጣት ዝግጁ ነበር . . .



# ክፍል አንድ

## የሰማያዊው መንግሥት የመስፋፋት መርሃ ግብር

# ምዕራፍ አንድ

## የተስሚነት ኃይል

አዲስ ለሚገለጥ እውነት ከቀድሞው ስህተት የበለጠ ጠላት የሚሆነው የለም::

ጆሃን ዎልፍጋንግ ቮን ጎተ

አንድ ጊዜ ራሴን በገዢ መንግሥትና በቅኝ ተገዢ መካከል ተቀምጬ አገኘሁት::

ይፋ ስሆነ መንግሥታዊ የስራ ጉዳይ፤ በባሃማስ የአሜሪካ አምባሳደር መኖሪያ ቤት በእንግድነት ተገኝቼ ነበር:: በተመሣሣይ የሥራ ጉዳይ የሁለቱም የቱርክስና የካይኮስ ደሴቶች ጠቅላይ ሚኒስትሮች የተገኙ ሲሆን ተጨማሪ ደግሞ የእነኝህ ሁለት ደሴቶች ጠቅላይ ገዢ የሆኑት የተከበሩ ሰው በዚያው ነበሩ::

ይህ የደሴቶች ቡድን የእኔ አገር ከሆነችው ከባሃማስ በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ነው:: ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ የቱርክስና የካይኮስ ደሴቶች የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ነበሩ:: ቅኝ ግዛቶቹን የሚያስተዳድሩት ከእንግሊዝ ንግሥት ኤልሳቤጥ ሁለተኛዋ ሹመትን የተቀበሉ ልዑላዊ ገዢ ናቸው:: በእነዚህ ቅኝ ግዛቶች ውስጥ የእርሳቸው ባለሥልጣን ትልቁ እርሱ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግን በህዝቡ የተመረጡ ባለሥልጣንና እነዚህን ትናንሽ ደሴቶች በሚመሩት ንግሥት እውቅና የተሰጣቸው ናቸው::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአሜሪካው አምባሳደር ልዩ እንግዳ ነበሩ:: አምባሳደሩ የዲፕሎማሲያዊ አባላትን፣ ታዋቂ የመንግሥት ባለሥልጣናትንና ከመላው ዓለም የሆኑ እንግዶችን ጨምረው ጋብዘዋል:: ከዚህ ስብሰባ በፊትም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የቅርብ የሆነ ትውውቅ አለኝ:: ልዩ የሆኑ አገራዊ ክብረ በዓላት በሚኖሩበት ጊዜ፤ እጅግ ውብ የሆነችውን የደሴታቸውን ግዛት እንድጎበኝ የሚጋብዙኝ በመሆኑ ለመንግሥትና ለህዝቡ ባለሥልጣናት ንግግር አድርጌአለሁ:: ከዚህ የተነሣ ወዳጅነታችን የቀረበ ነበር::

የተሰበሰብንበት የመንግሥታዊ ሥራ ጉዳይ ሂደቱ በአሜሪካው አምባሳደር ቤት ቀጥሎ እያለ፤ ልዑላዊ ገዢውን በመጠኑም ቢሆን ደህና አድርጌ ላውቃቸው ችዬ ነበር:: ምክንያቱም በጠቅላይ ሚኒስትሩና



በእርሳቸው መካከል ሆኜ ለሦስት ሰዓታት ያህል በጉባኤው ውስጥ ተቀምጫለሁ:: የቱርክስና ካይኮስ ደሴቶች ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት ሰው የአገሬው ተወላጅ ሲሆኑ፤ ክቡር ገዢው ግን ንጹህ እንግሊዛዊ ናቸው:: በሚናገሩበት ጊዜ የእነዚያ ደሴቶች ተወላጅ አለመሆናቸውን ወዲያውኑ ታውቃላችሁ::

ሁለቱም በግራና በቀኜ እንደተቀመጡ፤ ከእነዚህ ታዋቂ መሪዎች ጋር እየተወያየሁ ሳለ፤ አንድ ነገር እንደገና ልገነዘብ ቻልኩ፤ ይሄውም የገዥነትን መርህና በሚገዟቸው ቅኝ ግዛቶች ላይ ያላቸውን ተፅእኖ ነው:: አይታዬን እንደገና አደሰልኝ፤ እኔ ራሴ ደግሞ የቀደመችው የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ቅኝ ግዛት በነበረችው በአገሬ እንደ ዜጋ የነበረኝን ግላዊ ልምምድ አስታወሰኝ:: በዚያ ስፍራ ተቀምጬ የነበረው በልዑሉና በቅኝ ተገዢው፤ በገዢውና በአስተዳዳሪው፣ በሥልጣንና በኃይል መካከል ነበር:: ገዢው የተላኩት በቅኝ ግዛቱ ውስጥ በአገሬው ህዝብ መካከል የእንግሊዝን መንግሥት ንግሥት እንዲወክሉና በቅኝ ግዛት ውስጥም ንግሥቲቱ ያላቸውን ምኞትና ፈቃድ እንዲፈጽሙ በመንግሥት ተወክለው ነው:: እርሳቸው በዚያ የሚኖሩበት ዋንኛው ዓላማ የመንግሥታቸውን አገዛዝ ተፅዕኖና ህልውና በግዛቶቹ ላይ ለማስፈን ነው::

## የመንግሥት ሕይወት

ለዓመታት ያደረኳቸው ጥናቶች ወደ አንድ ድምዳሜ መርተውኛል፤ የመንግሥታት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ከአገራቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውጤታማነት ባሻገር የሚያመለክቱን እውነቶችና መርሆዎች መኖራቸውን ነው:: ነገሮቹ እንዴት እንደሚሰሩ እንመልከት::

- ስለራሳችን ተፈጥሮና ሰብእዊነት ጥልቅ የሆነ መረዳትን ያቀርቡልናል::

- እጅግ አስፈላጊ ለሆነው የሕይወታችን አላማ ቁልፉን ያሳዩናል::

- በዓለም እስካለን ድረስ ሙሉ ኃይላችንን መጠቀም እንድንችል ያደርጉናል::

እነዚህ ነገሮች ለሰው ዘር ፍጥረት ግላዊ፣ ሙያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ ለሆኑ ጉዳዮችና ለቤተሰቦቻችን፣ ለማህበረሰባችን፣ ለአገራችንና ለመላው ዓለም እጅግ ጠቃሚ የሆነ አተገባበርን የሚያሳዩ ናቸው::

እኔ የመንግሥታትንና የቅኝ ግዛቶቹን ጉዳይ በየአቅጣጫው ለማስተዋል በሚያስችል ልዩ በሆነ ስፍራ ላይ ነው ያለሁት:: ለሁለት መቶ አመታት ያህል የታላቋ ብሪታኒያ ቅኝ ግዛት በሆነች አገር ውስጥ አድጌአለሁ፤ ወደ ነፃነት የተደረገውንም ሰላማዊ ሽግግር ተመልክቻለሁ:: በቅኝ ግዛት ሥር መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አስታውሳለሁ፤

> **የሕይወትህ ስኬት**
> **የተመሠረተው**
> **የመንግሥትን ሕይወት**
> **በምትኖረው ስውነታ ነው።**

የመንግሥትን የአመለካከት ዘይቤ፣ አሠራሩንና የአተገባበር ሂደቱን ሁለቱንም አውቃለሁ። ይህንን ብቻ አይደለም፤ በቅኝ እየተገዛ ባለ አገር ውስጥ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነም አውቃለሁ። እንደ ወጣትነቴ የራሳችን ነፃ መንግሥት እንዲኖረን ታላቅ ጉጉት ነበረኝ። በእነኝህ ሁለት የአገዛዝ ዐይነቶች ውስጥ በማለፌና ስለ እነርሱ የቀረበ እውቀትን በማግኘቴ እጅግ ተጠቃሚ ሰው ሆኛለሁ። የመንግሥትን ባህርይ ምንነትና በዚህ ፕላኔት ላይ ለሚኖር ሰው ሁሉ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቄ ተገንዝቤአለሁ።

በመንግሥት ጽንሰ ሀሣብ ላይ ያደረኩት ፍተሻዬ አንድ ነገር እንዳምን አድርጎኛል፤ የአንተና የእኔ የሕይወት ስኬት የተመሠረተው፤ "የመንግሥት ሕይወት" ብዬ የምጠራውን በምንረዳውና በምንኖርበት እውነታ ላይ ነው። አሁን እየተናገርኩ ያለሁት ፖለቲካዊ ስለሆነ ሥርዓት ወይም ስለየትኛውም የተለየ ብሔራዊ መንግሥት አይደለም፤ ይልቁንም የየዕለት ሕይወታችንን የምንገነዘብበትንና የምንኖርበትን መንገድ ነው።

## ፀረ መንግሥታዊ አመለካከት

ለሰለጠነው ዓለም አዕምሮ፣ የመንግሥት ጽንሰ ሀሳብ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ይመስል ይሆናል። ቅኝ ገዢና ቅኝ ተገዢ መንግሥታት የቀደመ ዘመን መታሰቢያነታቸውን ብቻ ትተው በሃያኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ቀርነት ተፈርጀው አልፈዋል። ዛሬ ብዙ ህዝቦች እነርሱን የሚወክሉ መንግሥታት አሏቸው። እጅግ ብዙ የሆኑ የቀደሙ ቅኝ ግዛቶችና በሞግዚት ይተዳደሩ የነበሩ አገራት ነፃነታቸውን ተቀዳጅተዋል። በመላው ዓለም ራስን የማስተዳደር መብት እየተስፋፋ ሄዷል፤ እነዚህ ለውጦች ባስከተሏቸው የፖለቲካ ነፃነቶችና በተገኙት ዕድሎች የደስታ ፈንጠዝያዎችን አድርገናል። ሰብአዊ የሆነው ታሪክ ጨቋኝ የነበሩ መንግሥታትና አምባገነኖች ለተለየ ዓይነት የመንግሥት ስርአት ሥፍራቸውን ሲለቁ አሳይቶናል።

*ዲሞክራሲ በመሠረቱ አግባብነት በሌላቸው መንግሥታት ላይ የሚነሳ የህዝቦች ተቃውሞ ነው። የአሜሪካ መስራቾች ጨቋኝ ነው ባሉት* መንግሥት ላይ ተቃውሞን እንስተዋል፤ አሁን ያለው የምዕራቡ ዓለም ዘመናዊ ሥነ ባሕርይ ፀረ-መንግሥት አቋም ያለው ነው። ፖለቲካዊና ማህበራዊ የሆኑ አስተሳሰቦች ነፃ በመውጣትና በነፃነት ላይ አሳድረውት በነበረው ጠንካራ ተጽእኖ ምክንያት፤ እንዲህ ያለው አመለካከት በዓለም ውስጥ ሊገባ ፈቃድ ከማግኘቱም በላይ መንግሥታዊ በሆነ አመለካከታችን በብዙ አቅጣጫዎች አሉታዊ ተጽእኖን አሳድሯል። ይህም በግላዊ



ግንኙነቶቻችን፣ በንግድ፣ በመገናኛ ብዙሃን፣ በትምህርት፤ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጭምር ባለን ቅኝትና አተገባበር ራሱን ይገልጻል፤ ምክንያቱም ባህላዊ የሆኑ ልምምዶቻችን ለነገሮች የምንሰጠውን ትርጉም የሚፈጥሩ ናቸው።

ይሁን እንጂ ከእድገት እይታ አንጻር ስንቃኝ፣ አብዛኛው ህዝብ ህጋዊ በሆነና በሙሉና ባልተበከለ መንግሥት ውስጥ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልተረዳም። ይህ የግንዛቤ እጦት ደግሞ ሕይወታቸውን የሚመሩበትን መንገድ አቅጣጫ እንዳያገኙ እንቅፋት እንደሆነባቸው አምናለሁ። ብዙዎቻችን፣ መንግሥታት በታሪካቸው እንዲህ ያለውን ጠንካራ ተጽእኖ በሰዎች ላይ ለምን ሊያመጡ እንደቻሉና ህዝቦችስ በሺህ ለሚቆጠሩ ዓመታትና እስከ ዛሬም ድረስ ስለ መንግሥት የሚሰማቸውን ስሜት እንዲሰማቸው ለምን እንደሆነ ዘንግተነዋል። የመንግሥት ጽንሰ ሀሳብና ታሪካዊ አነሳሱን ምንነት አልተገነዘቡትም - ለእኛ ግን አሁን ይህ እጅግ ጠቃሚ ነው።

በዚህ ምክንያት እኔ፣ ደረጃ በደረጃ፤ የመንግሥት ሕይወት እንዴት አድርጎ ስለ ሰብአዊ ህልውናችን መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን እንደሚመልስ፣ ዓላማውንና ስኬታማነቱን ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ። ግለሰባዊ የሆነ ግባችንንና ችግሮቻችንን፣ ብሄራዊና ዓለም ዓቀፋዊ የሆኑ ቀውሶችን ጭምር ጠቃሚ ከሆኑ ነጥቦች አንፃር እንቃኛቸዋለን፤ ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ ከዚህ እይታ አንፃር አንመለከታቸውም። ዛሬ ዴሞክራሲ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ፖለቲካዊ ተቋማችን ነው፤ ነገር ግን ዘመናዊ ነው ከምንለው ፖለቲካና መንግሥት በላይ አልፎ ስለ ሚሄድ ነገር ነው እኔ የምናገረው - እንደ ሰብአዊ ፍጥረትነታችን መሠረታዊ የሆነውን ነገር የሚያብራራ እውነት። ለሁሉም አገር ህዝቦች፣ ሃይማኖቶችና ቤተ እምነቶች ሁሉ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው። በምድር ላይ በሚኖር በማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ የሚያርፍም ነው፤ ክርስቲያን ይሁን ቡዲስት፣ ሂንዱ፣ ሙስሊም፣ አይሁድ፣ በእግዚአብሔር መኖር ለማያምኑና ለግብረገባውያን ሁሉ ያስፈልጋል።

እኔ በመንግሥት እና በቅኝ ግዛት መካከል ተቀምጬ ራሴን እንዳገኘሁት፤ አንተና በዚህ ፕላኔት ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው፤ በመንግሥትና በቅኝ ግዛት ባለ ግንኙነት ውስጥ ራስህን ፈልገህ እንድታገኝና የግኝትህ ውጤት የሆነው ኃያል ነገር በራስህ ሕይወት እንዲሠራ እንድታደርግ ይጠበቅብሃል።

## የመንግሥት ኃይል

አሁን እኔ የምናገርበት መንግሥት በባሕርዩ፣ ከዚህ ቀደምም ይሁን አሁን እንዳሉት በመንግሥታቸው ኃይል፤ በስግብግብነትና በሃይማኖታዊ አስተምህሯቸው ሌሎችን በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ኃይልን መጠቀም እንደሚፈልጉት ዐይነት መንግሥት አይደለም። እነዚህ

መንግሥታት ባሪያ ያደርጋሉ:: ይሁን እንጂ የማንኛውም ሰብአዊ ፍጥረት ባህርይ፤ እንዲሁም የመላው ዓለም ግለሰባዊና የጋራ እድገት ስሪቱ ይህ መንግሥት ከሚሠራበት አሠራር በላይ መዳበርና ማደግ ነው::

በዚህ መጽሐፍ መቅድም ላይ እንደገለጽኩት፤ የሰብአዊነት ዋነኛው ጥያቄ የኃይል ጥያቄ ነው:: ይህም ማለት፤ በሁኔታዎች ላይ ተጽእኖ ማሣደርና መቆጣጠር ማለት ነው:: ሁላችንም ብንሆን ሕይወታችንን አዎንታዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ መምራትና መቆጣጠር እንፈልጋለን:: የዚህ መንግሥት ባህርይ በቀጥታ ስለዚህ ፍላጎታችን ይናገራል::

ከዚህ መንግሥት ጋር ያለንን ግንኙነት መረዳታችን የሚጀምረው፤ የትኞቹም ሰብአዊ የሆኑ መንግሥታት በጋራ የሚካፈሉትን ነገርና ዛሬ ለብዙዎቻችን አዲስ ያልሆነውን ከዘመናዊው መንግሥት አስተሳሰብ የሚለዩበትን ሁኔታ ማጥናት በመጀመር ነው:: ከዚያ በኋላ ሰፋ ወዳለው የእኛን ሰብአዊ ህልውናና የሕይወት ግብ የሚመለከተውን ጠለቅ ያለ ዐውድ መመልከት እንጀምራለን::

## የመንግሥት አስተዳደር ባህርይ

እኔ መንግሥትን የምተረጉመው፤ "የአንድ ሉአላዊ የሆነ አገር ገዢ በሚገዛው ክልል ውስጥ በራሱ ህዝብ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ ደረጃ ፍቃዱን፣ ዓላማውንና ፍላጎቱን የሚያስፍንበት የአገዛዝ ስልጣን ብዬ ነው":: ንጉሥ የሚገዛው የራሱ የሆነ ግዛት ወይም ክልል ሊኖረው ያስፈልገዋል:: ይህንን ደግሞ "የንጉሥ ግዛት" ወይም "የእርሱ መንግሥት" እንለዋለን:: ያለ ግዛት ወይም ያለመንግሥት ንጉሥ ልትሆን አትችልም፤ የምትገዛው (የምታስተዳድረው) አንድ ነገር መኖር አለበት:: እንዲሁም በምትገዛው ግዛት ውስጥ የሚኖሩና የሚሠሩ የመንግሥቱ ነዋሪዎች ከሌሉ ንጉሥ ልትሆን አትችልም::

> እውነተኛ በሆነ ወግ አጥባቂ አስተዳደር፤ ሁሉም ኀይል ተሰብስቦ የተከማቸው በንጉሡ ነገሥቱ እጅ ውስጥ ነው

እውነተኛ በሆነ፣ ወግ አጥባቂ መንግሥት ውስጥ ሁሉም ኃይል ተሰብስቦ የተከማቸው በንጉሡ ነገሥቱ እጅ ውስጥ ነው:: በተለይም ንጉሡ በግሉ ህዝቡን ጨምሮ የሀገሪቱ ባለቤት ነው:: በተቃራኒው ደግሞ፣ በሕዝብ በተወከለ አስተዳደር ውስጥ ፕሬዚዳንቱ ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገሩን በባለቤትነት አይገዝም፤ ህዝቡን በመወከል ያስተዳድራል::



ንጉሡ ለግዛቱ ያለውን ራዕይ ተግባራዊ ያደርጋል:: በየትኛው ህግ እንደሚተገበሩት የሚወያይ ጉባኤ ወይም ምክር ቤት የለም:: ያለው አንድ ነገር ንጉሡ ነገሥቱ ብቻ ነው፤ እርሱ ደግሞ ወዲያውኑ ሊያገኛቸው የሚችል፣ ፍላጎቱን ተግባራዊ የሚያደርጉለት ታማኝ አማካሪዎች አሉት:: የእነኝህ አማካሪዎች ተግባር የንጉሡን ፈቃድ ማድረግ፣ ወደ አገሪቱ ህግ መተርጎምና በግዛቱ ውስጥ ሁሉ መተግበሩን ማረጋገጥ ነው::

> ንጉሡ ለግዛቱ ያለውን ራዕይ ተግባራዊ የሚያደርገው በግል ፈቃዱ ላይ ተመስርቶ ነው::

ስለዚህ ይህ መንግሥት በግዛቱ ሁሉ ውስጥ የንጉሡ የአገዛዝ ተጽእኖ ሥር የሚሆን ሲሆን፤ ይህንንም ተጽእኖ የሚያሳድረው በራሱ ፈቃድ ላይ ተመስርቶ ነው:: በመንግሥቱ ውስጥ የንጉሡ ግላዊ ፍላጎት ፖሊሲ ይሆናል፤ የንጉሡ ግላዊ ፈቃድ ደግሞ ህግ ይሆናል::

በመሆኑም የግዛቱ ውጤታማነትና ያለው ኃይል የሚወሰነው፤ በንጉሡ ራዕይ መሠረት በግዛቱ ውስጥ ማሳደር በሚችለው ተጽእኖና የመቆጣጠር ችሎታው ነው::

## የመንግሥት ዋንኛ ግብ፡ ግዛትን ማግኘትና መግዛት

ብዙ መንግሥታት በታሪክ ሁሉ ውስጥ ተጨማሪ መሬቶችን ለማግኘት ሲፈልጉ ኖረዋል፤ አንዳንድ ጊዜ እነኝህ መሬቶች ከራሳቸው ግዛት እጅግ ሩቅ በፍራ ላይ ያሉ ናቸው:: ይህንን የሚያደርጉበት ምክንያት የንጉሡ ኃይል የሚለካው ባሉት ግዛቶች መጠን በመሆኑ ነው:: ንጉሡ ብዙ ግዛቶች ካሉት፤ በሌሎች መንግስታት የበለጠ ክብርን ያገኛል፤ ይልቁንም ደግሞ ግዛቶቹ በርካታ የተፈጥሮ ሀብት ካላቸው ክብሩ የበለጠ ይሆናል:: የንጉሡ የትውልድ አገር የራሱ ግዛት ሲሆን በተጨማሪ የያዛቸው መሬቶች ደግሞ ቅኝ ግዛቶች ይባላሉ::

አንድ አገር በቅኝ ግዛትነት አንድ ጊዜ ከተያዘ፤ የሉአላዊ ገዢው ዋናኛ ግብ በቅኝ ግዛቱ ላይ ግላዊ የሆነ ተጽእኖ መፍጠር (መለማመድ) ነው::

## የቅኝ ግዛቶች ወደ መንግሥትነት የመቀየር ሂደት

ቅኝ ግዛት የሚያቅፈው፤ "የሰደተኞችን ቡድን ወይም ደግሞ በሩቅ አገሮች በጭቆና ያሉ ዘሮቻቸውን ነው":: *ቅኝ ግዛት* የሚለው ቃል የተገኘው *ኮሎኒያ* ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን፤ ይህም የተወሰደው ኮሊር ከሚለው "ማልማትን" ከሚያመለክት ቃል ነው:: በዚህ ስሜት ቅኝ ግዛት ማለት:

- ✓ የተለየ ባህል ያላቸው ሰዎች በባዕድ አገር ውስጥ መገኘትና በተገኙበት አገር ውስጥ በራሳቸው አገር ህግና ባህላዊ ሥርዓት መሠረት መተዳደራቸውን ያሳያል።
- ✓ በተገኙበት ምድር ላይ የአገራቸውን መንግሥት በመወከል ተጽእኖ ለማሣደር መደራጀታቸውን ያሳያል።

በዚህ መሠረት የቅኝ ግዛት መሠረታዊ ዓላማ፤

1. በሌላ ግዛት ውስጥ የትውልድ አገራቸውን ማስፋፋት (መመስረት) ነው።
2. በሌላ ግዛት ውስጥ አገራቸውን የምትመስል ሌላ አገር መመስረት ነው።
3. የትውልድ አገራቸውን እሴት፣ ስነምግባርና የአኗኗር ዘይቤ ማሳየት ነው።
4. የመጡበትን ህዝብ ባህልና የአኗኗር ልምምድ መግለጽ ነው።

በመሆኑም አንድ መንግሥት ቅኝ ግዛትን ሲወስድ፣ ዋነኛው ግቡ ያንን ግዛት ልክ የራሱን መንግሥት እንዲመስል ማድረግ ነው። ዐላማው መሬትን ብቻ መያዝ ሳይሆን፣ ይልቁንም ያንን ግዛት በአመሰካከቱ፣ በአኗኗር ዘይቤው፣ በባህርይው፣ በባህሉ፣ የትውልድ አገሩ ፍቶ ኮፒ ዓይነት አድርጎ መለወጥ ነው። በዚህ መንገድ አንድ መንግሥት የሚያስፋፋው ኃይሉን ብቻ ሣይሆን የባህርይውን ተጽእኖ ጭምር ነው።

የሮም ግዛት በቅኝ ግዛትነት በያዛቸው የመንግሥቱን ተጽእኖ በዘላቂነትና ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚያስፍንበት የተለየ መንገድ ነበረው። ሮማውያን አንድን ግዛት ሲቆጣጠሩ፤ የሦስት ሦስት መቶ ዜጐቻቸውን ቡድን በየቦታው ያሰፍራሉ፤ በተጨማሪም በርካታ ቁጥር ከመንግሥቱ ጋር ቀረቤታ ያላቸውን ሰዎችና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሰፋሪዎች እንደ ወታደራዊ ደጀን በመጠቀም ያሰፍራሉ። የእነኝህ ሁሉ ስብስብ ደግሞ የሮም ዜጎችን ስብስብ ወይም "ትንሿን ሮም" ይመሰርታል። ሮማዊ ዜግነት ያሰው የዚህ ስብስብ ዜጋ ታክስ ለመክፈልም ይሁን በወታደራዊ ግዳጅ እንዲሳተፍ አይገደድም። ስብስቡ በሮም ህገ መንግሥት ላይ የተመሠረተ የራሱ ህገ መንግሥት አለው፤ የራሱን የምክር ቤት ተወካዮችና ሌሎች የመንግሥት ቢሮ ተወካዮችን ለመምረጥ ይፈቀድለታል። በግዛቱ ውስጥ የሚኖሩ ቀደምት ሰፋሪዎች አዲሱን መንግሥትና የመንግሥቱንም ህገመንግሥት የመደገፍ ግዴታ አለባቸው። እነዚህ "ትንንሽ ሮሞች" የሮም መንግሥትን ባህልና እሴት በመላው አውሮፓና በሰሜን አፍሪካ አገራት ላይ አምጥተዋል።

መንግሥታት በያዟቸው ግዛቶች ላይ ያሳረፉትን የኃይል ተጽዕኖና የአኗኗር ዘይቤ አስደናቂ የሆነ ምስል በካሪቢያን በሚገኙ የተለያዩ



ህዝቦችና በምዕራብ ኢንዲስ ውስጥ ማየት ይቻላል። የአገሮቹን ህዝቦች ባህል በማጥናት አገራቱን በቅኝ ግዛትነት የያዛቸው ማን እንደነበረ በቀላሉ ለመለየት ይቻላል። ባሃማስ፣ ጃማይካ፣ ትሪኒዳድና ባርባዶስ፣ የእንግሊዝ የቀደሙ ቅኝ ግዛቶች ናቸው። ኩባ የስፔን ቅኝ ግዛት ነበረች። ሃይቲ ደግሞ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ነበረች። የእነኚህን ደሴቶች ሁሉ ባህል በቀላሉ መለየት በሚቻልበት ጊዜ በቅኝ የገዟቸውን አገራት ባሕል የሚመስል ነው።

> የአንድ መንግሥት ቀዳሚ ግብ፤ በቅኝነት የያዘውን ግዛት በትክክል የራሱን መንግሥት መስል ማስያዝ ነው።

እስከ አሁንም ድረስ የመንግሥታቱን ተጽእኖ በህዝቡ የዕለት ኑሮ ዘይቤ ላይ ማየት ይቻላል። ባሃማስን የምትጎበኙ ከሆነ፤ •የታላቋ ብሪታንያን ተጽእኖ ጠባብ በሆኑ መንገዶቻችን፣ መኪናዎቻችንን የመንገዱን ቀኝ ይዘን በመንዳታችን፣ ሻይ በመጠጣት ልማዳችን ልትለዩ ትችላላችሁ። ወጣት በነበርኩበትና ትምህርቴን በምከታተልበት ወቅት እኔና የክፍል ጓደኞቼ ያደግነው "እግዚአብሔር ንግሥቲቱን ይጠብቅ" እያልን በመዘመር ነው። "ትንሿ ብሪታኒያውያን " እንደሆንን እንማር ነበር። በተመሣሣይ ሁኔታ ወደ ኩባ ብናቀና፤ በህገሪቱ ያሉትን የህንጻዎች አሠራርና ምግባቸውን በመመልከት በስፔን ውስጥ ያላችሁ ነው የሚመስላችሁ። ይልቁንም ደግሞ በባህላቸው ላይ ያጠላው ትልቁ ጥላ እያንዳንዱ ቅኝ ግዛት የሚናገረው ቋንቋ ቀድሞ ገዢዎቻቸው የነበሩ አገራትን ቋንቋ ነው።

በቅኝ ግዛት ዘመን አብዛኞቹ መንግሥታት ለአዳዲስ ግዛቶች ይዋጉ የነበሩበት ምክንያት በዓለም ላይ የቀረው ጥቂት መሬት ብቻ በመሆኑ ነው። በአውሮፓ ቁጥጥር ስር ከነበሩት አገሮች ባሃማስን በቅኝ ግዛትነት ለመያዝ አስቀድማ የጠየቀችው አገር ስፔን ነበረች። ፈረንሳዮች ሊይዟት ሞከሩ፤ ስፔኒያውኑ ግን መክተው መለሷቸው። በመጨረሻው ብሪታንያ ከእስፔን እጅ ቀምታ የራሷ አደረገቻት። እንደዚያ ባይሆን ምናልባትም ዛሬ የስፓንሽ ቋንቋ ተናጋሪ ነበርኩ። እናም ምንም እንኳን ባሃማስ ሀይቲና ኩባ እርስ በእርስ የተያያዙ ደሰቶች ቢሆኑም፤ ማንም በቅኝ ግዛትነት ይያዛቸው፤ በቅኝ ግዛትነት የያዛቸው መንግሥት የህዝቡን ቋንቋና ባህል ይቆጣጠራል። በእውነት የመንግሥትን ኀይል ምንነት ለማወቅ የምትፈልጉ ከሆነ፤ የዶሚኒካ ሪፐብሊክና የሀይቲ የሁለቱም መነሻ የሆነችውን የሂስፓኞላ ደሴትን ሁኔታ አጥኑ። ሁለቱም መንግሥታት አንዷን ደሴት ተቀራምተዋት ነበር። በመሆኑም በደሴቲቱ መሃል ለመሃል የተሰመረ መስመር ነበር። አንደኛው ጎን እንግሊዝኛ ይናገራል፤ ሌላኛው ወገን ደግሞ በስፓኝ ቋንቋ ያወራል።

## በቅኝ ግዛት ውስጥ ከፍተኛው ሰው

ቅኝ ግዛትን ወደ ገዢው መንግሥት ባህል የመለወጥ ሂደት ወዲያውኑ የሚፈጠር ነገር አይደለም። ኃይለኛ የሆነ እድገትን የሚያካትት ጉዳይ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ንጉሡ ቢያዛቸው ቅኝ ግዛቶች ውስጥ ተጽእኖውን የሚያሳድረው በቀጥታ በአካል በዚያ በመገኘት አይደለም። ፈቃዱን በግዛቶቹ ላይ ተግባራዊ የሚያደርገው፤ ገዢዎች ወይም ወኪሎች ተብለው በሚጠሩ የግል ተወካዮቹ አማካይነት ነው። እርሱን ተክተው በቅኝ ግዛቶቹ ውስጥ በአካል ይኖሩ ዘንድ ተወካዮቹን ይሰዳቸዋል። በዚህም ምክንያት በቅኝ ግዛቱ ውስጥ በውክልና ያለው ልዑላዊ የሆነው ገዢ በአካል ያልተገኘው ንጉሥ የህልውና መገለጫ ነው።

በቅኝ ግዛቱ ውስጥ ያለው ገዢ እስካለ ደረስ፤ በዚያ በንጉሡ ተጽእኖ ሥር ለመተዳደር የንጉሡ በአካል መገኘት አያስፈልግም። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑትን የካሪቢያን ህዝቦች የገዙት የእንግሊዝ ነገሥታት፤ ቅኝ ግዛቶቻቸውን አዘውትረው ይጐበኙ እንዳልነበሩ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። ይሁን እንጂ በበሃማስ ሁላችን እንግሊዝኛ መናገር ተምረናል፤ ሻይ መጠጣትና የእንግሊዝን መዝሙሮች መዘመር ተለማምደናል። የተባበረው የእንግሊዝ መንግሥት አካል ሆነናል። እናም ልዑላዊ የሆኑት ገዢዎች የዚህ ሽግግር ዋንኛና ቀጥተኛ መሣሪያዎች ነበሩ።

በመሆኑም ገዢው በቅኝ ግዛቱ ውስጥ ከፍተኛው ሰው ነው። ዓላማውንም መመልከት በምንጀምርበት ጊዜ፤ ይህ ለምን እውነት እንደሆነ ወደ ታላቅ መደነቅ እንመጣለን።

## የገዢው ዓላማ

የገዢው ዓላማ ስድስት እቅጣጫዎች ያሉት ነው፤

1. *ግንኙነት መፍጠር፦* የገዢው መኖር፤ መንግሥት ሁልጊዜም ቅኝ ግዛቱን መድረስ እንደሚችል ያመለክታል። በንጉሡና በቅኝ ግዛቱ መካከል ያለው ሁለንተናዊ ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ የሚመሠረተው በገዢው ላይ ነው።
2. *ተግባቦት፦* ንጉሡ፣ ቅኝ ግዛቱ እንዲያውቅለት ወይም እንዲቀበልለት የሚፈልገውን ነገር፤ በገዢው በኩል መላክ ይችላል፤ ገዢው የንጉሡ የተግባቦት መስመር ነው።
3. *ውክልና፦* ገዢው፣ በቅኝ ግዛቱ ውስጥ የንጉሡና የመንግሥቱ ከፍተኛው ወኪል ነው። እንዲሁም ደግሞ በንጉሡ ዘንድ ቅኝ ግዛቱን ይወክላል።



4. *ትርጉም፦* ገዢው የንጉሡን መሻት፣ ሃሣብ፣ አመለካከት፣ ዓላማ፣ ፈቃድና እቅድ ወዲያውኑ ይረዳል፤ በመሆኑም እነኝህን ነገሮች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለቅኝ ግዛቱ መተርጎም የሚችለው ብቸኛው እርሱ ነው።
5. *ኃይል፦* ገዢው የንጉሥን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግና ቅኝ ግዛቱን ለመቆጣጠር በሥልጣንና በችሎታም ኃይልን የተቀበለ ብቸኛው እርሱ ነው።
6. *አጋርነት፦* ገዢው በአገዛዝ ጉዳዮች ላይ የንጉሡ ውጤታማ የሆነ አመራር አጋር ነው።

## የገዢው ብቁነትና ሚና

መንግሥትንና ቅኝ ግዛቶቹን አስመልክቶ የገዢው ብቃት መስፈርትና ሚና ወሳኝ ጉዳይ ነው።

*1. ገዢው በንጉሡ የተወከለ ነው።*

በህዝብ ውክልና ሥልጣን እንደሚይዙት ሰዎች ገዢው በድምጽ የተመረጠ ሳይሆን፤ በቀጥታ በንጉሡ የተወከለ ነው።

*2. ገዢው የመጣው ከመንግሥት እንጂ ከቅኝ ግዛት አይደለም።*

ገዢዎች በጭራሽ በቅኝ ግዛት ከተያዘው ምድርካሉ ነዋሪዎች የሚመረጡ አይደሉም። ሁልጊዜም ገዢዎች የሚወከሉት ከመንግሥቱ ዜጎች መካከል ነው። ግን ለምን? ገዢው በመንግሥቱ ቅድመ ባህል ውስጥ ያደገ ሰው ሊሆን ስለሚገባው ነው። መንግሥቱን በአግባቡ የሚያውቅና የንጉሡን ልብ፣ ሀሣብ፣ እቅድ፣ ፈቃድና መሻት የሚገነዘብ ሰው ሊሆን ይጠበቅበታል። በዚህም በቀላሉ የመንግሥቱን ዓላማ ቅኝ በተገዛው አገር ላይ ተግባራዊ ያደርጋል።

*3. ገዢው ንጉሡን ብቻ የሚወክል ነው።*

እንደገና ደግሞ፤ ብዙዎቻችን እንደምናውቀው በቅኝ ግዛት ገዢዎችና በሕዝብ ውክልና ሥልጣን ላይ ባሉ ገዥዎች መካከል ያለው ልዩነት የሌሊትና የቀን ያህል ነው። በአሜሪካ ውስጥ በማንኛውም ግዛት ህዝቡ ድምፅ የሰጠበት ገዢ አለው፤ ይህንንም ገዢ ድምጽን በማቀብ ከገዢነቱ ሊያስወግደው ይችላል። እርሱ ወይም እርሷ በከፍተኛ ደረጃ ተጠሪነታቸው ለግዛቱ ህዝብ ነው። ለማዕከላዊው መንግሥት ወይም ደግሞ ለመሪዎች አይደለም። በተቃራኒው ደግሞ በንጉሡ የተወከለው ልዑላዊው ገዢ ታማኝነቱ፣ ዝንባሌው፣ ተግባሩና ሃላፊነቱ ለንጉሡ ብቻ ነው።

*4. ገዢው፤ የንጉሡን ሀሣብና ፈቃድ ብቻ የሚገልጥ ነው::*

ገዢው በቅኝ ግዛቱ ውስጥ የሚኖረው የግሉን ፖሊሲዎችና አጀንዳዎች ሲያስተዋውቅ አይደለም:: የንጉሡን ራዕይና ፈቃድ በመውሰድ ከህዝቡ ጋር ማገናኘት አለበት፤ በፖሊሲና በህግ እንዲተረጐሙ (እንዲተገበሩ) ማድረግም ይጠበቅበታል::

*5. ገዢው፤ ቅኝ ግዛቱን ወደ መንግሥትነት የመለወጥ ሃላፊነት አለበት::*

በተጨማሪም፤ ቅኝ ግዛቱን በሾመው መንግሥት ባህርይ አኳያ ወደ መንግሥትነት የማሸጋገር እና የመቆጣጠር ተግባር በገዢው ላይ ያረፈ ነው:: ገዢው በቅኝ ግዛቱ ውስጥ የተተከለው፤ የአገሩን መንግሥት ዘር በአዲስ ግዛት ባህል ላይ ለመዝራት ነው:: ከቅኝ አገዛዝ ዓላማዎች አንዱ መለወጥ ነው - የቅኝ ተገዢውን አገር ባህል በቅኝ ገዢው አገር ባህል መለወጥ:: በአገር ውስጥ የሆነው ማንኛውም ነገር በቅኝ ግዛቱ አገር ውስጥም መደረግ ይጠበቅበታል::

*6. ቅኝ ግዛቱን በመለወጡ ረገድ፤ ገዢው የመንግሥቱን ባህል፣ እሴት፣ ባሕርይ፣ ቋንቋና የአኗኗር ዘይቤውን ወደ ህዝቡ ማሸጋገር ይገባዋል::*

ገዢው፤ ማናቸውም የመንግሥቱ ተገዢ ግዛት በባህል፣ በቋንቋ፣ በዝንባሌ፣ በአለባበስ፣ በአመጋገብና በመሳሰሉት ሁኔታዎች መለወጡን እርግጠኛ መሆን አለበት:: ቅኝ ግዛቶቹ የገዢውን መንግሥት ታሪክ እንኳን የራሳቸው አድርገው እንዲቀበሉ ይጠበቅባቸዋል:: እውነቱን ለመናገር አሁን እየሆነ ያለው ይሄው ነው:: ምክንያቱም ቅኝ ግዛቶች የገዢዎቹ ህዝብ ታሪክ አንድ አካል ሆነዋል:: ማንም ቅኝ ግዛቶቹን የሚጎበኝ የገዢው አገር ዜጋ በራሱ አገር ውስጥ እንዳለ እስኪሰማው ድረስ በተገዢዎቹ አመለካከትና የሕይወት ልምምድ ላይ ተጽእኖና ለውጥ ማምጣት አለባቸው::

*7. ገዢው ተገዢዎችን ለዜግነት የሚያዘጋጅ ነው::*

አንድ ንጉሥ ቅኝ ግዛትን በሚይዝበት ጊዜ፤ ህዝቡ የግድ የእርሱ የግል ይዞታ ነው የሚሆነው:: የቅኝ ግዛት ህዝቦች ወዲያውኑ ዜጎች አይሆኑም፤ ተገዢዎች ነው የሚባሉት:: ለምሳሌ ያህል ባሃማስ ቅኝ ግዛት በነበረችበት ጊዜ ህዝቡ የእንግሊዝ ዜጎች አልነበሩም:: ድምፅ አንሰጥም ነበረ፤ በመሆኑም የእንግሊዝ ዜጋ ለመሆን መብት አልነበረንም::

በመንግሥት ውስጥ፤ ዜግነት ችሮታ ነበር:: ዜግነትን ያገኘ ሰው የንጉሡን ቸርነት የተቀበለ ሲሆን ዜግነቱንም የሚያረጋግጥለት ራሱ ንጉሡ ነው:: ዜግነት ወዲያውኑ ተግባራዊ የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው:: አንድ ሰው ዜግነትን ከተቀዳጀ በዚያ መንግሥት ውስጥ የተለየ ጥቅምና ክለላ የማግኘት ዋስትና ይኖረዋል:: በሮም ግዛት ውስጥ ዜግነት ትልቅ ክብር የሚሰጠውና ብዙ መብቶችን አካቶ የሚይዝ ዕድል ነበር::



በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የተርሴሱ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ውስጥ ሰላምን አደፍርሷል በመባል ተወንጅሎ በሮማዊ የወታደሮች አዛዥ በቁጥጥር ስር ውሎ ነበር:: የሮማዊ ዜግነት ያለው መሆኑን በተናገረ ጊዜ ወዲያውኑ የወታደሮቹ ሁኔታ ተለወጠ:: የሁኔታዎቹ ፈጥነው ተውኔታዊ በሆነ መልኩ መስዋወጥ የሮም መንግሥት ዜጋ የመሆንን ኃይል በተለይም ደግሞ ዜጋ ሆኖ የመወለድን ኃይል ታላቅነት ያሣያል::

> ዜጐች፤ በመንግሥቱ ውስጥ የተለየ ጥቅምና ክበሳ ስባቸው::

ሲገርፉት በሰተሩት ጊዜ ጳውሎስ እዚያ ቆሞ ለነበረው ጠባቂ "ሮማዊ ዜግነት ያለውንና ወንጀለኛ እንደሆነ ያልተመሰከረበትን ሰው ልትገርፉ ህጉ ይፈቅድላችኋልን?" አለ:: ወታደሩ ይህንን በሰማ ጊዜ ፈጥኖ ወደ አለቃው በመሄድ ሪፖርት አደረገ:: "ምን ልታደርግ አሰበሃል? " ሲል ጠየቀው፤ "ይህ ሰው እኮ ሮማዊ ዜግነት ያለው ነው::" አዛዡም ወደ ጳውሎስ በመሄድ፤ "ንገረኝ እስኪ! አንተ የሮም ዜጋ ነህን?" ሲል ጠየቀው:: "አዎን ነኝ" ሲል መለሰ:: ቀጥሎም አዛዡ እንዲህ አለ፤ "እኔ ይህን ዜግነቴን በብዙ ገንዘብ ገዝቼ አገኘሁት":: ጳውሎስ ደግሞ፤ "እኔ ግን ዜጋ ሆኜ ተወልጃለሁ" ሲል መለሰለት:: በእርሱ ላይ የነበራቸውን ጥያቄ ሁሉ ፈጥነው አነሱ:: አዛዡ ራሱ የሮም ዜግነት ያለውን ሰው ማሰሩን በተገነዘበ ጊዜ ደነገጠ::

አንድ ጊዜ ዜጋ ከሆንክ፤ ዕድሎችህ፣ መብትህና ጥያቄዎችህ በዙፋኑ ፊት የተለዩ ይሆናሉ:: ንጉሡ አንተን ሲንከባከብህ ኃላፊነት አለበት:: በዚህም ምክንያት ተገዢዎችን ወደ ዜግነት በማሸጋገር ረገድ የገዢው ሚና ታላቅ ሃላፊነት ያለበት ነው:: ገዢው፤ ተገዢው ዜጋ ለመሆን የተዘጋጀ መሆኑን ካመነበት ወይም ዜጋ ለመሆን የሚያበቃ የተለየ ብቃት እንዳለው ካወቀ፤ ተገዢው የዜግነት መብት ይቀዳጅ ዘንድ በንጉሡ ፊት ያቀርበዋል:: ገዢው በቅኝ ግዛቱ ውስጥ ስለሚኖርና ተገዢውን በቅርብ የሚያውቀው በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የገዢውን ጥያቄ ንጉሡ ይቀበለዋል::

*8. ገዢው የሚኖረው በገዢው መንግሥት አስተዳደር በተሠራለት የመኖሪያ ቤት ውስጥ ነው::*

መንግስት በቅኝ በያዛቸው ግዛቶቹ ውስጥ ልዑላን ገዢዎች ለሆኑት ተወካዮች የመኖሪያ ህንፃ ይገነባል:: ይህ የሚያመለክተው ገዢው፣ በቅኝ ግዛቱ ውስጥ የመንግሥቱ ዋነኛ ተጠሪ እንደሆነ፣ ሰጉብኝት የመጣ ሰው እንዳይደለ፣ ተቀማጭነቱም በዚያ እንደሆነና በዚያ የሚቆይ፣ ቤቱም

እየተናገረ እንዳልሆነ ልብ ይበሉ። እዚህ ጋ ቆም ብለን ልንጠይቅ ያስፈልጋል።

- ✓ ይፋዊ አገልግሎቱን በጀመረበት በዚያ ወቅት ለምንድን ነው ይህንን መንግሥት ነክ ጉዳይ ያነሣው?
- ✓ መልዕክቱና ዓላማውስ ምንን ለመግለጽ ነበር?
- ✓ የመንግሥት አገዛዝ (ተፅዕኖ) ወደ ዓለም እየገባ ከሆነስ፣ ለምድር ዜጎች የሚያመጣላቸው አዲስ ባሕል ምን ሊሆን ይችላል?

ይህን ሀሳብን የሚፈታተን ዐውድ ለመረዳትና አተገባበሩንም ለማወቅ ወደ ዘፍጥረት መጽሐፍ መመለስ ያስፈልገናል፣ ስለዚህ መንግሥት መነሻ በዚህ መጽሐፍ እናገኛለን። ወደ መጀመሪያው መንግሥት ያመጣናል። ይህ መጥቶ የሚሄድ መንግሥት ወደዚህ ዓለም ሲመጣና በነዋሪዎቿ ላይ ተፅዕኖ ሲያሳድር የመጀመሪያው አይደለም።

- ✓ መልዕክቱና የመልዕክቱ ዓላማስ ምንን ለመግለጽ ነበር?
- ✓ የመንግሥቱ አገዛዝ ወደ አለም እየገባ ከሆነስ፤ በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ምን አይነት አዲስ ባህል ነው የሚያመጣላቸው?

ይህን ሀሣብን የሚፈታተን አውድ በቅጡ ለመረዳትና አተገባበሩንም ለማወቅ፤ ወደ ኋላ መለስ ብለን የሙሴ የመጀመሪያ መጽሐፍ የሆነውን ዘፍጥረትን እንመልከት ይህ ወደ መጀመሪያው መንግስት ያመጣናል። ይህ መጥቶ የሚሄድ መንግስት ወደዚህ አለም ሲመጣና በነዋሪዎቿም ላይ ተጽእኖ ሲያሳድር የመጀመሪያው አይደለም።



# ምዕራፍ ሁለት

## አዳማዊው አስተዳደር

*በውክልና የሚሰጥ ሥልጣን መርህና ዓላማው ተጠያቂነትና ሃላፊነት ነው*

በምድር ላይ የተመሰረተው የመጀመሪያው አስተዳደር የመጣው ከራሱ ውጭ ከሆነ መንግሥት ነው። ዓለም ትገዛ የነበረው ቀደም ባለው ምዕራፍ አይተነው በነበረው የቅኝ አገዛዝ ዐይነት ነው። ይሁን እንጅ ምጡቅ የሆነው መንግሥት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለው፤

- ✓ የምድር ግዛት በራሱ በትውልድ አገሩ የተፈጠረ እንጂ በኃይል የተወሰደ አይደለም። አስቀድሞ የማንም ይዞታ አልነበረም።
- ✓ በመጀመሪያው በምድር ላይ ምንም ዐይነት ነዋሪ አልነበረም፤ ገና በሀሣብ የታቀዱ ነበሩ። ስፍራውም የተዘጋጀው በተለይ በዚያ ስፍራ ይኖሩ ዘንድ ለታቀዱት ነበር።
- ✓ የመጀመሪያዎቹ ነዋሪዎች ከትውልድ ቀዬአቸው የመጡ የተለየ ባህል የነበራቸው አልነበሩም፤ ይልቁንም የንጉሡ የራሱ ልጆች ነበሩ።

ተመሳሳይነታቸው በእነዚህ ነው፦

- ✓ ገዢው አገር የአገዛዙን ተጽእኖ ባህርዩን፣ አመለካከቱንና የመንግሥቱን ዓላማ በምድር ላይ ባሉ ቅኝ ግዛቶች ውስጥ በማስፈን ግዛቱን የማስፋፋት እቅድ አለው።
- ✓ የንጉሡ ባለሟል የሆነው ገዢ ቅኝ ግዛቱን ለመቆጣጠርና የሽግግር ሂደቱን ለማቀላጠፍ በቅኝ ግዛቱ ውስጥ ይገኛል። የንጉሡ ልጆች የሆኑትን - ቅኝ ግዛቱን የመንግሥቱን ዐይነት ወደምትመስል መንግሥት የሚያሸጋግሩትን - የእርሱን የአካባቢ ገዢዎች ይመራቸዋል።

እስኪ አሁን በምድር ላይ የተፈጠረችው ቅኝ ግዛት እንዴት እንደተመሰረተች ቀረብ ብለን እንመልከት።

## የመጀመሪያው አስተዳደር

ቀዳሚው የሙሴ መጽሐፍ የሚከፈተው እንዲህ በሚሉ ቃላት ነው፤ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር (ፈጣሪው ንጉሥ) ሰማይንና ምድርን (ፍጥረታዊውን ግዝፈ ዓለም ፈጠረ)።" የአንደኛው ክፍለ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር የነበረው የተርሴሱ ሰው ጳውሎስ፤ ፈጣሪውን ንጉሥ "የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ... እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳን አላየውም፤ ሊያየውም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን" እያለ ገልጿል።

> *በፈጣሪነት መብቱ፣ ፍጥረታዊው ግዝፈ ዓለም የፈጣሪው ንጉሥ ንብረት ነው።*

የማይታየው መንግሥት ዘላለማዊ ንጉሥ በህሳቡ አቀደው፣ ደግሞም መላውን ፍጥረታዊ ግዝፋ ዓለም ፈጠረው። በፈጣሪነቱ መብት፣ የተፈጠረው ንብረቱ ነው።

ያለንበትን ግዝፈ ዓለም የጠቀሰሰውን የዚህን የማይታየውን መንግሥት ትልቅነት ለመረዳት የማይቻል ነገር ነው፤ ይልቁን ደግሞ አሁን ያለንባትን ምድር እንኳን ከታላቅነቷ የተነሳ ልንረዳት አለመቻላችንን ስናስብ አስቸጋሪነቱ የጎላ ይሆናል። አሁን የምንኖርበት ግዝፈ ዓለም ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ከየት ጀምሮ የት እንደሚጨረስ እንኳን እስካሁን ድረስ በፍለጋ ላይ ነን። የስነ ፍጥረት ተመራማሪዎች እንደደረሱበት ሊታይ በተቻለው ግዝፈ ዓለም ውስጥ ብቻ በቢሊዮኖች (አንዳንዶች እንደሚሉት 200 ቢሊዮን) የሚደርሱ ጋላክሲዎች (የከዋክብት ክምችት) አሉ። እያንዳንዱ ጋላክሲ ደግሞ እስከ በዐስርና በመቶ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ የከዋክብት ክምችቶች እንደሚያካትት ይገመታል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጋላክሲዎችን በእያንዳንዱ ጋላክሲ ውስጥ በሚገኙት ከዋክብት ቁጥር አባዙና እስኪ በግዝፈ ዓለሙ ውስጥ ያሉትን የከዋክብቶች ቁጥር ለመናገር ሞክሩ። ይህ ቁጥር የሚያስደነግጣችሁና የሚያስደንቀን ከሆነ፤ እስኪ እርስ በእርስ ተያይዘው የፀኑበት መንገድ ምን እንደሆነ ገምቱ።

የአሜሪካን የጠፈር ምርምር ኤጃንሲ ናሳ እንደዘገበው፦ በጠፈር ውስጥ ያለው - ሁሉም አካል ማለት ይቻላል - በአንድ ነገር ዙሪያ የሚሽከረከር ነው። ፕላኔቶች በፀሀይ ዙሪያ ይሽከረከራሉ፣ የእኛ ጨረቃና የሌሎች ፕላኔቶች ጨረቃዎች በፕላኔቶቻቸው ዙሪያ ይሽከረከራሉ፤ ጅራታም ኮከቦች (ኮሜትስ) በፀሐይ ዙሪያ ይሽከረከራሉ ... ፀሐይ ራሷ እንኳን በእኛ ጋላክሲ መሀከል ዙሪያ ትሽከረከራለች።

*ምህዋር፤ በህዋው ውስጥ ያለ የአንድ አካል (ለምሣሌም ፕላኔቶች ወይም ጨረቃ ሊሆኑ ይችላሉ) የፊት ለፊት አቅጣጫ እንቅስቃሴና ይህ አካል በምህዋሩ ዙሪያ ከሚሽከረከርበት ሌላው አካል በሚወጣ የስበት*



*ኃይል መካከል ያለ ፍጹማዊ የሆነ እኩል ሚዛን ነው። በእንቅስቃሴ ላይ ያለ አንድ አካል አንድ ነገር ካልገፋው ወይም ካልጎተተው በስተቀር እንቅስቃሴውን ይቀጥላል። ይህ የይስሐቅ (አይዛክ) ኒውተን የእንቅስቃሴ የመጀመሪያው ህግ ነው። ስበት ባይኖር ኖሮ በሳተላይቶች ዙሪያ በምህዋሯ ላይ የምትሽከረከረው መሬት ምህዋሯን ጥሳ በህዋው ውስጥ በቀጥታ መስመር ዝም ብላ ትጓዝ ነበር። አካሉ በቀጥታ መስመር ለመጓዝ ባለው ፍላጎትና አካሉን በቀጥታ መስመር ከመጓዝ በሚገታው ስበት መካከል የማያቋርጥ ጦርነት ይካሄዳል።*

ግዝፈ ዓለም አስደናቂ በሆነ በእኩል የኃይል ሚዛን ተሳስሮ ይገኛል። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ፤ ይህንን ግዝፈ ዓለም በስርዓት ያደራጀው ማንም የለም ብለው የሚያስቡ ሞኞች ብቻ ናቸው የሚለው። በግልጽ እንደሚታየው እጅግ ታላቅ ችሎታና ኀይል ያለው የተደራጀ አስተዳደር ግዝፈ ዓለማችንን በጥበብ ሠርቶታል።

## የማይታየውን መንግሥት ማስፋፋት

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከሆኑት አንዱ፤ "ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዮት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን" አለ። የማይታየው ዓለም ንጉሥ ግዝፈ ዓለምን ለመፍጠር ወሰነ። ይህን ያደረገው ደግሞ የእርሱና የእርሱም መንግሥት የሆነውን የማይታየውን ሰማያዊ ግዛቱን ለማስፋት አቅዶ ነው። ግዝፈ ዓለምን በመፍጠሩ፣ የሚገዛውን ተጨማሪ ግዛት ለማግኘትና ባህርዩንና እቅዱን ለማስተላለፍ አስችሎታል። ወደ መንግሥት ትንታኔያችን እንመለስና፤ የማይታየው መንግሥት ማለት በምድር ግዛት ላይ የእግዚአብሔርን አገዛዝ የሚያሰፍን፤ የፍቃዱን፣ የዓላማውንና የእርሱን መሻት ተጽእኖ የሚያመጣ ነው ለማለት እንችላለን። መንግሥተ ሰማይ የእግዚአብሔር መንግሥት ወይም አገር ቤቱ ሲሆን ምድር ደግሞ ቅኝ ግዛቱ ነች።

በየዕለቱ የሕይወት ልምምዳችን፣ በፖለቲካዊ ዐውዱ ሳይሆን፣ በተለያዩ ጉዳዮች የአገዛዝ ተጽእኖዎች ያጋጥሙናል።

- ✓ አንድ ሰዓሊ በሚሠራው ስዕል ወይም ቅርጻ ቅርጽ፤ በህሣቡና በልቡ ውስጥ ያለውን የራሱን ማንነት በመግለጽ፤ ሥራዎቹን በሚመለከቱ ሰዎች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል።
- ✓ አንድ ፀሐፊ በውስጡ ያለውን ራዕይ በሚታተመው ቃል ጽሑፎች አማካይነት ይገልፃል። እነዚህ ቃላትም በሚያነቧቸው ሰዎች አስተሳሰብና ዝንባሌ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ።
- ✓ አንድ ነጋዴ በውስጡ የተጠነሰሰውን የአንድ ምርት ጽንሰ ሀሳብ ወደ አንድ ኩባንያ በመሄድ ይገልጽለታል። ይህ ጽንሰ ሃሣብ

የእርሱን ግላዊ ፍልስፍናን የሚያንጸባርቅ ከመሆኑም በላይ ሌሎች ሰዎች የሚኖሩበትን የአኗኗር ዘይቤ የሚለውጥና አዲስ ምርትን የሚያስገኝ ነው።

እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች፣ ግለሰቦች የራሳቸው የሆነውን ተጽእኖ በዓለም ላይ የማያሳርፉበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው።

ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚፈጥሩት፣ የሚገልጹት ወይም የሚገነቡት የስብእናቸውና የአመለካከታቸው ነፀብራቅ ነው። በመሆኑም ፈጣሪ - ንጉሥ የማይታየውን መንግሥቱን አገዛዝ ለማስፋት ያለውን እቅድ ስንመለከት፤ የዚህን ንጉሥ ባህርይና የመንግሥቱን ምንነት ለማወቅ መፈለጋችን የሚያስገርም አይሆንም። በዚህ ምድር ላይ ምን አይነት አገዛዝ ለማስፈን ነው የሚፈልገው?

## የንጉሡ ባህሪይ

## ፍጹማዊ የሆነ አስተዳደር

የማይታየው መንግሥት ባህርይ በተለይ ጉልህ የሚሆነው፤ በምድር የሚኖሩ ራሳቸው የዚህ መንግሥት ትክክለኛ ባህርይ ሊኖራቸው እንደሚገባ ስንረዳ ነው። የሙሴ የመጀመሪያው መጽሐፍ የፈጣሪ - ንጉሥን ቃል እንዲህ ሲል ይዘግባል፤

> "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር፤ የባህርን ዓሶችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ (ግዛት ይኑራቸው)።" እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው። ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።

ሰብአዊ ሰዎች የተፈጠሩት እንደ ማሽኖች ወይም ከፈጣሪያቸው ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ነገሮች ሆነው አይደለም። ከእርሱ ስብእና ውስጥ የወጡ ናቸው። "ሰውን በመልካችን፣ እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር፣ በምድርም ላይ ሁሉ ... ይግዙ"

> **ፍጹማዊ የሆነ አስተዳደር ለዜጎቹ እንጂ ለራሱ አይኖርም**

የራሱ በሆነ መለኮታዊ ፍቃድ ግዝፈ ዓለምን ከፈጠረ በኋላ፤ ፈጣሪው በግዝፈ ዓለሙ ውስጥ ከፈጠራቸው ፕላኔቶች ሁሉ መካከል የአገዛዙ የመተገበሪያ ልዩ ሥፍራ ትሆን ዘንድ በማቀድ አንድ ፕላኔት መረጠ - ምድር። ከዚያም አገዛዙን በራሱ ምስል ለፈጠራቸው ወይም ልዑላዊ ለሆኑ "ልጆቹ" አስተላለፈ።



"መልክ" የሚለው በመጀመሪያው የዕብራይስጥ ቃል "ሴሌም" ማለትም "መሠረታዊ የሆነ ባህርይን ያቀፈ "መልክ" ማለት ነው"። "ምሳሌ" ለሚለው፣ የዕብራይስጡ ቃል ደግሞ "ደሙዝ" ነው፤ ይህም ማለት "የመጀመሪያውን ነገር መልክ የሚመስል" ማለት ነው። እነዚህ ቃላት የሚገልጹልን ስሪታችን፣ ችሎታችን፣ አቅማችንና እንደ ሰብአዊ ፍጥረትነታችን ያለን እሴት የፈጣሪያችንን ስብእና ለማንፀባረቅ መሆኑን ነው።

የፈጣሪ - ንጉሣችን ባህርይ በሙሴ እንዲህ ተዘግቦ ይገኛል፤ "መሃሪ፣ ሞገስ ያለው፣ ለቁጣ የዘገየ፣ በፍቅሩና በታማኝነቱ ባለጠጋ የሆ[illegible]፡ አንድ መንግሥት ፍፁማዊ በሆነ መንገድ ለመራመድ የሚችልበት [illegible]ኛ መንገድ፤ በሙስናና በጭቆና ህዝቡን አሳልፎ በማይሰጥ እውነተኛ ፅሆነ ንጉሥ ሲገዛ ብቻ ነው። በሙስና የሚገዛ ከሆነ እውነተኛ ንጉሥ ሳይሆን ጨቋኝና አምባገነን ነው። ንጉሡ በአገዛዙ ሥር የሚገኘው የማንኛውም ሰውና ነገር ምንጭና ባለቤት በመሆኑ፤ የእውነተኛ መንግሥት ቁልፍ ጉዳዩ ቅንነት ነው። ፍጹማዊ የሆነ አስተዳደር ለዜጎቹ እንጂ ለራሱ አይኖርም።

## የምድር ዜጎች ባህርይ

በፈጣሪ - ንጉሥ መልክና ምሳሌ መፈጠር ማለት፤ ሰብአዊ የሆኑት ፍጥረታት ከርሱ መንፈሳዊ ባህርይ፣ ጠባይና መሠረታዊ ከሆነው ማንነት ተካፋዮች ሆነዋል ማለት ነው። እኛ ታቅደን የተፈጠርነው እርሱን እንድንመስል፣ እንደርሱ እንድናደርግና እንደ ማይታየው መንግሥት መሪ አደራረግ እንድናደርግ ነው።

> *እኛ ታቅደን የተፈጠርነው እርሱን እንድንመስል፣ እንደርሱ እንድናደርግና እንደማይታየው መንግሥት መሪ አደራረግ እንድናደርግ ነው።*

ፈጣሪ፣ የራሱ የሆነውን ባህርይ ከሰጠን በኋላ፤ እርሱ ራሱ (1) ፍጥረታዊ የሆነ አካል ሰጠን፤ በመሆኑም በተለይ ለእኛ ብሎ ባዘጋጀው ፍጥረታዊ ዓለም ውስጥ ነገሮችን ማከናወን ቻልን፣ እና (2) የራሱ የሆነውን መንፈስ እፍ አለብን፤ በምድር ላይ የተፈጠርንበትን ተግባር እናሳካ ዘንድ ሕይወትንና ኃይልን ሰጠን። ሙሴ ይህን፤ "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ" ሲል ይዘግባል።

ፈጣሪ - ንጉሥ ሰውን፣ አዳምን፣ ከምድር አፈር አበጀው፤ ይህም ማለት ይህ ሰብአዊ "ምርት" በዓለም ነበረ፤ ነገር ግን ገና ሕይወትን አላገኘም። አካሉና አዕምሮው ተዘጋጅቶ ነበር፣ ግን ሕይወት

አልነበራቸውም:: አዳም "ሙት" ነበር ለማለት አንችልም፤ ምክንያቱም በዚያ ጊዜ ሞት የሚባል ነገር አልነበረም:: እኛ፤ "ሕይወት የሌለው ነገር" ብለን የምንጠራው አይነት ነበር:: ፈጣሪ በአዳም ላይ የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ባለበት ጊዜ ነበር አዳም ሕያው ነፍስ የሆነው::

ያ የመንፈስ እስትንፋስ በሦስት አይነት የተለዩ መንገዶች በአዳም ውስጥ ሕይወትን አቀጣጠለ፤ (1) በማይታየው የሰው መንፈስ ውስጥ - ይህም በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረና ዘላለማዊ ነው፤ (2) በሰው ነፍስ ውስጥ - ይህም ማለት አጠቃላይ የአዕምሮው ንቃተ ህሊና፣ ፈቃዱና ስሜቱ ማለት ነው፣ እና (3) ፍጥረታዊ በሆነ አካሉ፣ ይህም የመንፈሱና የነፍሱ ሕያው የሆነ ማደሪያ ነው:: የሰው አካልና ነፍሱ ምድራዊ የሆነውን ክባቢውን መረዳት ይችል ዘንድ አስቻለው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ በሰው መንፈስ ውስጥ አድሮ፤ ስለፈጣሪው ንጉሥ ግንዛቤ እንዲኖረውና ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያደርግ ዘንድ አስቻለው::

በዚህም ምክንያት መንፈስ በሁሉም ዐይነት ሁኔታዎች ውስጥ ለአዳም እንደ ሰብአዊ ፍጡር ሕይወትን ሰጥቶታል:: የመጀመሪያዋን ሴት የሔዋንንም አፈጣጠር ብንመለከት ሁኔታው ተመሳሳይ ነበር:: እግዚአብሔር መንፈሱን ወደ ሕያዋን ሰዎች ሲያስገባ፤ ሰብአዊው ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የእግዚአብሔርን መንፈስ መቀበልን ይሰማመዳል:: የፈጣሪ መንፈስ በምድር፣ የእኛ ሰማያዊ "ገዢ" ነው፤ እርሱም ከንጉሡ መጥቶ ቅኝ ግዛቱ በሆነችው ምድር በእኛ ውስጥ አደረ፤ ፈቃዱን እንድንቀበል፣ እንድናውቅና እናደርግ ዘንድ አስቻለን፤ ልክ ልዑላዊ ገዢዎች በቅኝ ግዛቶቻቸው ውስጥ ያሉትን ህዝቦች እንደሚመሩአቸውና መንገድ እንደሚያሳዩአቸው ማለት ነው::

"ሰውን በመልካችን እንፍጠር" የሚለው ገለፃ *በመልክ መመሳሰልን* የሚገልጽ አይደለም፤ ይልቁንም *በሁኔታ መመሳሰልን* የሚያመለክት ነው:: የፈጣሪ - ንጉሥ ዓላማ የራሱን ባህሪይ በሰው ሰብእና ውስጥ መግለጽ ነበር:: ያ ባህርይው በሰው መንፈስ በኩል ክነፍሱ፣ ማለትም ከአዕምሮው፣ ከፈቃዱና ክስሜቱ ጋር በመገናኘት ቀጥሎም በፍጥረታዊ አካሉ ይገለጣል:: በዚህ መንገድ፣ ሰዎች በእግዚአብሔር የተፈጠሩት "ከውስጥ ወደ ውጭ" ይኖሩ ዘንድ ነው::

የሰው ልጆች የተፈጠሩት የእግዚአብሔርን ባህርይ ለመግለጽ ነበር:: በሌላ አባባል አስቀድሞ ሲፈጠር ይመስል የነበረውን ማንነቱን ማለት ነው:: ("በተፈጥሮው - ከተፈጥሮ በላይ" የሆነውን ማንነቱን ማለት እንችላለን፤ ምክንያቱም ፈጣሪው - ንጉሥ ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ ህልውና በመሆኑ ነው::) ሰብአዊው ሰው የፈጣሪውን ባህርይ ከራሱ ጋር ማዋሃድና ማንጸባረቅ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ መሠረታዊውን



መልኩን ሲይዝና በእርሱ ውስጥ የሚኖረውን መንፈሱን ሲቀበል ብቻ ነው::

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ዓለምንና በእርሱ ያለውን ሁሉ ያፈጠረ አምላክ፤ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሰራው መቅደስ አይኖርም"፤ እንደገናም ደግሞ፤ "የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደሆናችሁ፣ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚኖርባችሁ አታውቁምን? " ፈጣሪ - ንጉሥ በየትኛውም አይነት ህንፃ ውስጥ በቤተክርስቲያን ይሁን ብመቅደስ፣ በቅዱሳን ስፍራዎች ወይም በመስጊዶች ውስጥ አይኖርም:: በምድር ላይ እውነተኛ የሆነ የመኖሪያው ሥፍራ ሰብአዊ ፍጥረቶቹ ናቸው:: መንፈሱ አካላችንን ሲሞላው እኛ የእርሱ መኖሪያ ስፍራ እንሆናለን:: በዚህ መንገድ፣ ንጉሡ ሰብአዊ በሆነው ፍጥረቱ ውስጥ ንጉሣዊ መኖሪያ ይመሠርትና በእርሱም በኩል ቅኝ ግዛቱ የሆነችውን ምድር ይገዛል::

> *ሰብአዊው ሰው በእርግጥም ንጉሣዊ ቤተሰብ ነው፤ አባቱም ታላቅና ዘላለማዊ የሆነው መንግሥት ንጉሥ ነው::*

## ልዑላን ልጆችና ሙሉ ዜጐች

አዳምና ሄዋን የፈጣሪው - ንጉሥ ዘር ማንዘሮች ወይም ልጆች ናቸው:: በመሆኑም ሰብአዊው ሰው በእርግጥም ንጉሣዊ ቤተሰብ ነው፤ አባቱም ታላቅና ዘላለማዊ የሆነው መንግሥት ንጉሥ ነው:: ሰብአዊ ፍጥረታት ቅኝ ተገዢዎች አልነበሩም፤ ይልቁንም የመንግሥቱ ሙሉ የዜግነት መብት ክብር የነበራቸውና በምድር ላይ ላለ ለማንኛውም ነገር ነፃ መብት የተሰጣቸው ነበሩ::

እግዚአብሔር ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት፤ ግዙአትም፤ የባህርን ዓሦችና የሰማይንም ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዟቸው::"

በምድር ላይ ከተሰጣቸው ከመጠቀም ነፃነት የተከለከሉት፤ የአትክልት ስፍራ ከሆነው መኖሪያቸው ይገኝ የነበረው የንጉሡ ህጋዊ ሥልጣን የነበረበት አንድ ስፍራ ብቻ ነው:: እንዲህ ሲል ነግሯቸው ነበር፤ "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና::" ስለዚህ ገደብ በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ በሰፊው እናወራለን::

## እንደ ምክትል ገዢዎች የተሰጠ የሥራ ድርሻ

ንጉሡ አዳምንና ሄዋንን በምድር ላይ እንዲገዙ ሲያደርግ፣ ሰብአዊ ለሆነው ፍጥረት የውክልና ሥልጣን መስጠቱ ነበር:: በሰማያዊው ገዢ ሥር ሆነው የምድር ግዛት ምክትል ገዢዎች ተደረጉ:: ሰብአዊው ሰው ልክ እንደ "ትንሿ ሮም" ነበር፤ በምድር ላይ የተቀመጠውም ለሰማይ መንግሥት ዓላማና ምድርን እንደ ሰማያዊው ቤት የማድረግን ተልዕኮ ይዞ ነው:: ይህ ደግሞ፤ ቅኝ ግዛቶችን እንደመሠረቱትና መንግሥቱን ወክለው ቅኝ ግዛቶችን ይመሩ እንደነበሩት የሮም መንግሥት ምስለኔዎች ማለት ነው:: ልዩነቱ የሮም መንግሥት ምስለኔዎች ቁጥር በቅኝ ግዛቱ ውስጥ የተወሰነ ይኸውም ሦስት የሚያህል ሲሆን፤ በምድር ላይ የተወለደ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ግን የመግዛት ውክልና ተሰጥቶት ነበር:: ምድር በሁሉም የሰው ዘሮች በቅኝ ግዛትነት ትገዛ ዘንድ የተሰጠች ነበረች:: ይህን ተግባራዊ ግዳጅ ወይም የሥራ ድርሻ "አዳማዊ አስተዳደር" ስል ጠርቼዋለሁ::

የመግዛት ሥልጣን ማለት፣ መግዛትን፣ ማስተዳደርን፣ መቆጣጠርን፣ መምራትን፣ ውጤት ማስገኘትንና ተጽእኖ ማምጣትን የሚያካትት ነው:: ሰብአዊ ፍጥረታት በመሠረታቸው መንፈሳዊ ህልውናዎች ናቸው፤ በፍጥረታዊ አካል ውስጥ እየኖሩ ቅኝ ግዛታቸው በሆነው ምድር ላይ ያለውን ፍጥረታዊ ዓለም የመግዛት ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ:: ፈጣሪው - ንጉሥ፤ "ይግዙዋት" ብሎ ሲናገር፤ "በምድር ላይ የሚገዛ መንግሥት ይኑራቸው ማለቱ ነው:: ሰማያዊ የሆነውን አገሬን ወክለው ምድርን ይግዙዋት ማለቱ ነው":: የሰብአዊው ፍጥረት ተግባር የሰማይን ፖሊሲ ማስፈጸም፣ ህግን ማውጣትና የሰማያዊውን መንግሥት ሕይወት መዝራት፣ የምድርን ተፈጥሯዊ ሃብት ማስተዳደር፣ በእንስሳቶቹ ላይ መሰልጠን፣ በማስተዋልና በጽድቅ መግዛት እንዲሁም ሁሉንም ነገር በስርዓት መጠበቅ ነበር:: እነዚህ ነገሮች ሁሉ በግዛቱ አስተዳደር ሊከወኑ ይገባቸዋል::

## የሰማያዊ ገዢ ተግባር

ሰብአዊ ፍጥረቶች በፈጣሪው - ንጉሥ መልክ የተፈጠሩ እና ምድርን የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ፤ ለስኬታማ አገዛዛቸው ቁልፍ የሆነው ነገር፤ የመንግሥትና የዜጎቹን ፍላጎት ያገናዘበ ቅንነትን የተሞላ አስተዳደር መሆኑን ልብ ማለት ጠቃሚ ነገር ነው:: ፍጹማዊ በሆነ መንግሥት ውስጥ መሥራት የሚችለው ፍጹማዊ የሆነ የቅኝ ግዛት አስተዳደር ብቻ ነው

ቀደም ሲል፤ በቅኝ ግዛት ውስጥ የውክልና ስልጣን የተቀበለው አካል ሥራውን በሚገባ ያቀለጣጥፍ ዘንድ ከንጉሡ ጋር ቀጥተኛ የሆነ የግንኙነት መስመርና በንጉሡ ፍላጎት መሠረት ኃላፊነቱን ለመወጣት



ኃይል ሊኖረው እንደሚያስፈልግ ገልጫለሁ:: ለዚህ ነው ለ[illegible] ማለትም የንጉሡ የራሱ መንፈስ - ለሰብአዊው ፍጥረት የተሰጠው[illegible]

ገዢው ከንጉሡ ዘንድ የመጣና ቅኝ ግዛቱን በብቃት ወደ አገር ቤትነት ለመለወጥ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው:: እርሱ የንጉሡን ልብ፣ ሀሣብ፣ እቅድ፣ ፈቃድ እና መሻት ያውቃል፤ በዚህም ምክንያት በግዛቱ ላይ የንጉሡን ዓላማ ለማስፈጸም ሃላፊነትን የተቀበለ ነበር:: ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "በሰው ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው? እንዲሁ ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም::" በተጨማሪ ደግሞ፣ ሰብአዊ ፍጥረታት የተፈጠሩት በንጉሡ መልክና ምሳሌ በእነርሱም ውስጥ ከሚኖር የእርሱ ግላዊ ህልውና ጋር ነው፤ በመሆኑም የምድርን ቅኝ ግዛት የማይታየው መንግሥት ቅጥያ አድርገው ለመለወጥ ብቁዎች ናቸው:: ይህን የመለወጥ ሂደት የንጉሡ የራሱ ባህርይ ካላቸውና በራሱ በንጉሡ መንፈስ ከሚመሩት ይልቅ በተሻለ መንገድ ማን ተግባራዊ ሊያደርገው ይችላል? በዚህ መንገድ፣ ምድር በባህርይዋና በዓላማዋ ከአገር ቤት ጋር በቅርብ የተመሳሰለች ትሆናለች::

*በዚህም ምክንያት፤ የፈጣሪው - ንጉሥ መሻት ከማይታየው ዓለም ሆኖ የሚታየውን ዓለም መግዛት መሆኑን እናያለን:: የሚታየውን ዓለም በሰው መንፈስ አማካይነት ለመግዛት ፈለገ:: እናም መንፈስ ቅዱስ፣ እንደ የሰው መንፈስ ገዢነቱ፣ በሰውና በአገር ቤቱ መካከል ድልድይ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ በሰው መንፈስና በሰማይ መንግስት መካከል ቀጥተኛ የሆነ የተግባቦት መስመር ነበር::*

ለሰብአዊው ፍጥረት በአካባቢያቸው ላይ ይገዙ ዘንድ ሥልጣንንና ብቃትን የሰጣቸው በእነርሱ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ነው:: ቀደም ሲል እንደገለጽኩት የሰብአዊው ፍጥረት ዋንኛው ጉዳይ ኃይልን ማግኘት፣ በሕይወት ሁኔታዎች ላይ ተጽእኖ ማሳደርና መቆጣጠር ነው:: ይህንን ችሎታ የምንፈልግበት ምክንያት በምድር ላይ ምክትል ገዢዎች ሆነን የተሰጠንን ሃላፊነት እንድንወጣ ታቅደን የተፈጠርን በመሆናችን ነው:: ከመዝሙረኞች አንዱ፤ "የሰማያት ሰማይ የጌታ ነው፤ ምድርን ግን ለሰው ሰጣት" ሲል ጽፏል::

> *መንፈስ ቅዱስ የሰብአዊው ፍጥረት ከአገር ቤት መንግስት ጋር ለሚያደርገው ተግባቦት ድልድይ ነው*

## በአዲስ ግዛት ላይ አገዛዝ

እስኪ አሁን ደግሞ ለሰብአዊ ፍጥረት የተሰጠውን ተግባራዊ ግዳጅ (ድርሻ) በሌላ አቅጣጫ እንመልከት:: የንጉሡ ወራሾች የሆኑት ልዑል

ወይም ልዕልት ንጉሡ በሕይወት እስካለ ድረስ ዙፋኑን ሊወርሱ አይችሉም። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሊያጋጥም የሚችልበት ብቸኛው መንገድ (ንጉሡ በገዛ ፈቃዱ ዙፋኑን ለመልቀቅ ካልፈቀደ በቀር) የንጉሡ ወራሽ ወደ ሌላ ግዛት በመሄድ መግዛት ነው። ይህ ምንም እንኳን እልፎ አልፎ ብቻ የሚከሰት ቢሆንም በታሪክ ውስጥ ግን የታየ ሁኔታ ነው። ስለዚህ፣ ወራሹ በአንድ ግዛት ውስጥ ከንጉሥ - አባቱ ጋር አብሮ እስካለ ድረስ፣ እርሱ ወይም እርሷ፣ ልዑል ወይም ልዕልት ብቻ ሆነው ነው የሚቀሩት። ይሁን እንጂ ወራሾቹ የሚኖሩት በባዕድ አገር ወይም በቅኝ በተያዘ ግዛት ውስጥ ከሆነ፤ ንጉሡ አባታቸው በአገር ቤት ውስጥ በመግዛት ላይ እያለም፤ እርሱ ወይም እርሷ ሉአላዊ ገገርዎች መሆን ይችላሉ። በመሆኑም ንጉሡ ልጆቹ ልክ እርሱ እንዳለው ያለ ኀይል፣ ሥልጣን፣ ክብርና አገዛዝ እንዲኖራቸው የፈለገ ከሆነ፤ ወደ ሌላ ግዛት ወይም ግዛቶች ሲልካቸው የግድ ነው።

የማይታየው የሰማያዊ ግዛት ንጉሥ ዘላለማዊ ነው። ከቶውንም ሊሞት አይችልም። ሰማያዊ የሆነውን ዙፋኑን ማንም ሊወርስ (ሊተካ) አይችልም። ይሁን እንጂ በመልኩና በምሳሌው በፈጠራቸው በሰብአዊ ፍጥረት የሚደሰት በመሆኑ፣ በስሙ የራሳቸው የሆነውን ግዛት እንዲገዙ ይፈልግ ነበር።

ይህ በመጨረሻው ደቂቃ ያሰበው ሀሣብ አልነበረም። ምድራዊ የሆነውን ቅኝ ግዛት ያዘጋጀው የመጀመሪያዎቹን ሰዎች (ወንድና ሴት) ከመፍጠሩ በፊት ነበር። ልጆቹ ይገዟት ዘንድ ፍጹም የሆነውን የሚታይ (ፍጥረታዊ) ከባቢ አቀደ። የመጀመሪያው የሙሴ መጽሐፍ የሰው ፍጥረት - ምክትል ገገር ሆኖ ይገዛቸው ዘንድ - እርሱ ከመፈጠሩ በፊት ስለተፈጠሩት ምድር፣ ባህርና እንስሳት አፈጣጠር ይዘግባል። ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ እንዲህ የሚል ዘገባ እናነባለን፤ "እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ወሰደ ያበጀትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው"። ፍጥረታዊው ዓለም እርሱን ከከበበው የማይታየው ግዛት የተለየ በመሆኑ፤ የሰው ፍጥረት ህጋዊ ሆኖ ይገዛው ዘንድ ሙሉ በሙሉ ገና አዲስ የሆነ ግዛት ነበር።

በዚህ ምክንያት የሰው ፍጥረት የመፈጠሩ መልዕክት ግልጽ ነው። ብዙ ጊዜ እንደሚመስለን "ሃይማኖታዊ" ለሆነ ዓለማ አይደለም፤ መስዋእትን ለማቅረብም አልነበረም። መልዕክቱ የሚገልጸው ዘላለማዊ ስለሆነው ንጉሥ አስተዳደርና መንግሥት፤ እንዲሁም በምድር ላይ በመንፈሱ ሥልጣንና ኃይል ገገርዎች ላደረጋቸው የንጉሡ ልዑላን ልጆች ነው። መልዕክቱ በግዛቱ ውስጥ ስላለው የንጉሡ አገዛዝና ግዛቱ የእርሱን መንግሥት ወደምትገልጥበት ደረጃ ስለማሸጋገር ነው።



# ምዕራፍ ሦስት

## የነፃነት አዋጅ

*የመንግሥት ልዩ መብቶችና ጥቅሞች ትልቁ ስጋት የሆነው ነገር ነፃ የመውጣት መንፈስ ነው።*

የምድር ክልል (ግዛት) ተፈጥሯል፤ ቅኝ ግዛቱም ተመስርቷል። የንጉሡ ልጆች ንጉሡን ወክለው ምድርን ይገዟትና በምድርም ላይ ይበለጽጉ ዘንድ የተሟላ ቤትና ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። ይሁን እንጂ የሰማይን መንግሥት ግዛት በምድር ላይ የማስፋፋቱን እቅድ የሚያደናቅፍ አንድ ነገር ተከስቷል። በአገር ቤቱ ውስጥ የተጀመረ ዐመፅ ወደ ቅኝ ግዛቱ ተስፋፍቷል።

### እምነትን ማጉደል

#### ሴራው፣ መገልበጥ

ሴራው የተቀነባበረው የንጉሡ ከፍተኛ ጀኔራሎች ከነበሩት በአንደኛው ማለትም በሉሲፈር ነው። በሰማያዊው መንግሥት ላይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በማድረጉ ከነተከታዮቹ ከንጉሡ ፊት ተባረረ። ይህ ከሥልጣኑ የተባረረው የንጉሡ የቀድሞ ባለሟል ለበቀል ከመነሳሳቱም አልፎ እስከ አሁንም ምድርን የመግዛት - ኀይል እየፈለገ ነው። የንጉሡን ልጆች መቆጣጠር ከቻለ ንጉሡን መስደብ፣ የሰማያዊውን መንግሥት እቅድ ማደናቀፍና ቅኝ ግዛቱንም መያዝ እንደሚችል ያስብ ነበር።

#### እቅዱ፣ መለያየት

የሉሲፈር እቅድ በንጉሡ ልጆችና በአባታቸው መካከል የነበረውን ግንኙነት ማቋረጥና የቅኝ ግዛቱን ዜጎች እውነተኛ ከሆነው መንግሥታቸው ማለያየት ነበር። በመሆኑም ራሱን ለውጦ፣ የንጉሡ ልጆች ገና መግዛት ወደጀመሩበት ስፍራ በመሄድ፣ አጭበርባሪነትንና አሳችነትን ተጠቅሞ ወደ አስተዳደራቸው ሰርጎ ገባ።

#### ስልቱ፣ የነፃነት መንፈስ

በንጉሡና በንጉሡ ልጆች መካከል የነበረውን ግንኙነት መስበር የፈለገበት ዋንኛው ምክንያት ዐመጽንና የነፃነትን መንፈስ በማነሳሳት ነበር። ከንጉሡ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና የንጉሡንም መልካም ፈቃድ

ምን እንደሆነ በረቀቀ መንገድ ጥያቄን ካቀረበላቸው በኋላ፤ የንጉሡ ልጆች በያዙት ቅኝ ግዛት ላይ የአባታቸው ሥልጣን የማይፈቅደውን እንዲያደርጉ አነሣሣቸው፤ የዐመጽ እርምጃ እንዲያካሂዱም አበረታታቸው:: ይህን አስመልክቶ በሙሴ የመጀመሪያው መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለው ተዘግቧል::

*እባቡም ... ሴቲቱን አላት፣ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዟልን? አላት:: ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፤ በገነት ካለው ዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬ እግዚአብሔር አለ:- እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም:: እባብም ለሴቲቱ አላት:: ሞትን አትሞቱም ከእርሷ በበላችሁ ቀን አይኖቻችሁ እንዲከፈቱ፤ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ:: ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለአይንም እንደሚያስጐመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች፣ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባሏም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርሷ ጋር በላ:: የሁለቱም አይኖች ተከፈቱ:: ራቁታቸውንም እንደሆኑ ዐወቁ::*

የንጉሡ ልጆች ንጉሡ ለራሳቸው ደህንነት ሲል ከመሠረተውና በጥብቅ ካዘዛቸው ትእዛዝ ተላለፉ:: ዐመጸኛው ጄኔራል ስለንጉሡ ዓላማ ጥርጥር ዘራባቸው፤ ያን ጊዜ ልባቸውን አለመተማመን ሞላው:: ወዲያውኑ አባታቸው በሰጣቸው ነገር ሁሉ ላይ ጀርባቸውን አዞሩ፤ በምትኩም የተነገራቸውን ውሸት አምነው ተቀበሉ:: ልጆቹ ያሳዩት ምላሽ ከንጉሡ ባህርይ ፍላጐት ተጻራሪ ነበር:: በተጨማሪም፣ በመልኩ ከተፈጠሩበት የራሳቸው ከሆነው ባህርይ ውጭ ሆነው ነበር::

> **መንግሥተ ሰማይ ከሰው ፍጥረት ጋር የገባውን ህጋዊ ስምምነት አዳምና ሄዋን አፈረሱት**

ከራሳቸው ጥቅም አንጻር ጎጂ ያልመሰለው ድርጊታቸው በመሠረቱ ታላቅ ውድቀት ነበር፤ የእምነታቸውን ማጉደልና ከንጉሡ ልብና ፈቃድ መውጣታቸውን የሚያመለክት ነው:: በቅኝ ግዛቱ ላይ በተሰጣቸው በጥቂቱ ተግባራዊ ግዳጅ እንኳን ያልታመኑ ከሆኑ፤ እንዴት አድርገው ነው የመንግሥተ ሰማይን ባህል በምድር ማስፈን የሚችሉት? በተለይ ደግሞ አዕምሯቸውና ልባቸው ከንጉሡ ቀንደኛ ጠላት ጋር በተስማማበት በዚህ ወቅት እንዴት ይቻላል?

**ውጤቱ :- ክህደት**

የንጉሡ የራሱ ልጆች፤ "ከዚህ በኋላ በንጉሡ ህጋዊ ሥልጣን ሥር መሆን አንፈልግም፤ ከነገሥታት ንጉሥ በታች መሆን አንፈልግም፤



ለመንግሥተ ሰማይ አንገዛም" ብለው ዐወጁ:: ይሁን እንጂ ምድርም የመንግሥተ ሰማይ ንብረት ነች:: አዳምና ሄዋን ባመጹና ነፃነታቸውን ባወጁ ጊዜ፤ የጣሱት መንግሥተ ሰማይ ከሰው ፍጥረት ጋር የገባውን ህጋዊ ስምምነት ነበር:: ብዙ ሰዎች "ኃጢአትን" ግለሰብ እንደ ሰራው ቀላል ነገር ያስባሉ:: ይሁን እንጂ ከዚህ የጠለቀና የተለየ ነገር ነው:: ኃጢአት በመንግሥተ ሰማይ መሠረታዊ ባህርይና ሥልጣን ላይ ማመጽ ነው::

በዐመጻቸው፤ ልጆቹ የራሳቸውን ያልሆነውን አንድ ነገር ብቻ አልነበረም የወሰዱት፤ ይልቁንም ይህን ነገር ሊቀበል ላልተገባውና መቼም ቢሆን መች ብቁ ሊሆን ለማይችል ለሌላ አሳልፈው ሰጡት:: ሉሲፈር፤ ታማኝ ያልሆነ የመንግሥተ ሰማይ የቀድሞ ጄኔራል፤ ምድርን የመንግሥተ ሰማይ ባሕርይ ወዳላት መንግሥትነት ሊለውጣት ከቶ አይችልም:: የሚለውጣት ሙሉ ለሙሉ ታቃራኒ ወደሆነ፤ ወደ ጨለማ መንግሽትነት ነው::

## ታማኝነትን ማጉደልና ስደት

የልጆቹን ከዳተኝነት በተረዳ ጊዜ ንጉሡ ያደረገው ምን ነበር? ያደረጉት ምን እንደሆነ ቢያውቅም፤ ስህተታቸውን ያምኑ ዘንድ እድል ሰጣቸው:: እነርሱ ግን፣ እርስ በርሳቸው ይወነጃጀሉ ጀመር፤ ይህ ደግሞ ያምፁ ዘንድ ያሳታቸውንም ይጨምር ነበር:: ለስህተት የተጋለጡ ዐመጸኛ ልጆች እንደሚያደርጉት ሁሉ፤ በጥፋታቸው ከተያዙ በኋላ ነበር በስህተታቸው ያዘኑ የመሰሉት:: እነርሱን ከገነት ከማባረር ውጭ ንጉሡ ሌላ ምርጫ አልነበረውም:: ተዘጋጅቶላቸው ከነበረው ልዩ ቤት ተባረሩ፤ ምክንያቱም ከዚያ በኋላ በዚያ ለመኖር የሚያስፈልጋቸው ባህርይ አልነበራቸውም፤ እንደ ንብረታቸው አድርገው ለመጠበቅም ችሎታው አልነበራቸውም::

የሙሴ የመጀመሪያው መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤ "አዳምንም አስወጣው፤ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በኤደን ገነት ምስራቅ አስቀመጠ:: በዚህ ስፍራ "አስወጣው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው፤ "ከይዞታ ላይ መፈናቀልን፤ በተለይም የዜግነትን መብት መገፈፍን ነው":: በዚህ ስፍራ ላይ የዜግነትን መብት የመገፈፍ ጽንሰ ሀሣብ ጎልቶ እናየዋለን፤ ይህም ማለት፤ "ለትውልድ ሀገር ሊሰጥ የሚገባውን ታማኝነት ማጉደል" ያስከተለው ውጤት ነው:: አዳምና ሄዋን የራሳቸው ከሆነው ንጉሥ - አባታቸውና ከትውልድ አገራቸው ራሳቸውን ያገለሉ ያህል ይቆጠራል:: ይወዳቸው የነበሩት ሰዎች ክህደትን ከፈጸሙብትና ግንኙነታቸው ከፈረሰ በኋላ፤ እነርሱን ከገነት ማባረር ለንጉሥ - አባታቸው መራራ ሀዘን ነበር::

አዳምና ሔዋን የፈጸሙት ከፍተኛ አገርን የመክዳት ወንጀል ነው:: በውክልና ኃይል ያስተዳድሩ ዘንድ ንጉሡ ሥልጣንን ሰጥቷቸው ነበር:: ይሁን እንጂ ያንን ሥልጣን፣ ግዛታቸውን ከመንግሥተ ሰማይ ለመገንጠል ያለ አግባብ ተጠቀሙበት::

## የገዢው ወደ አገር ቤት መጠራት

አስደናቂ ከነበረው ገነት የተባረሩ ቢሆኑም፤ የቀደመው አገዛዛቸው፣ የቀደመው መንግሥት የአኗኗር ዘይቤያቸው፣ ንጉሡንና ባህርዩን መቃወማቸው እጅግ ወደከፋ ነገር ውስጥ መራቸው:: ንጉሡ አስቀድሞ እንዲህ በማለት አስጠንቅቋቸው ነበር:: "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፣ ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ":: በምድር ላይ ይህንን ስፍራ ብቻ ነበር ንጉሡ በራሱ ህጋዊ ሥልጣን ሥር ያረፈ መሆኑን ያስታወቀው ምክንያቱም በዚህ ስፍራ ያለ አግባብ አንድ ድርጊት ቢፈጸም ወደ ሞት የሚያመራ ነገር ነበር::

> አዳምና ሄዋን እንደ ሰብአዊ ፍጥረትነታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕይወት ምንጫቸውን አጡ- ይህም የንጉሡ መንፈስ ነበር::

ንጉሡ ትሞታላችሁ ያላቸው ሞት ቅጽበታዊ የአካላቸው ሞት አልነበረም:: አዳምና ሄዋን ወዲያውኑ በአካል አልሞቱም፤ ይልቁንም እንደ ሰብአዊ ፍጥረትነታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕይወት ምንጫቸውን አጡ - ይህም የንጉሡ መንፈስ ነበር:: አንድ ነገር ልብ በሉ፤ የንጉሡ መንፈስ፤ ለመንፈሳቸው፣ ለነፍሳቸውና ለአካላቸው ሕይወትን የሰጠ ነበር:: ንጉሡን መታዘዝ ባልፈለጉ ጊዜ፤ የተቃወሙትና ያጡት መንፈሱን ጭምር ነበር:: ገዢው ብቻ ነበር በሚታየውና በማይታየው ግዛት መካከል የጠነከረ ግንኙነት የነበረው:: በዚህ ምክንያት መንፈሳቸውና ነፍሳቸው ከአገር ቤት ተለየ፤ እናም ፍጥረታዊ የሆነው አካላቸው አዝጋሚ የሆነ ሞት መሞት ጀመረ:: ለጊዜውም ቢሆን አሁንም በአካል ሕያዋን ናቸው፤ ይሁን እንጂ በመንፈሳቸውና በነፍሳቸው ለንጉሡና ለመንግሥቱ ምውት ነበሩ::

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፤ ቅኝ የሆነው ግዛት ከእናት አገሩ ነፃ በሚሆንበት በየትኛውም ጊዜ፣ ገዢው ተገዶ ሊወጣ ወይም መንግሥቱ ሊያወጣው ይችላል:: እንደዚሁ ሁሉ፣ አዳምና ሄዋን ነፃነታቸውን ባወጁ ጊዜ፤ ገዢው ሰማያዊ ወደሆነው መንግሥቱ ተጠርቶ ነበር:: ይህንን ሁኔታ ሊያብራራ የሚችል አስደናቂ ክስተት፤ በባሃማስ የነበረው የአስተዳደር ሥልጣን ከእንግሊዞች ወደ አዲሱ ነፃ አስተዳደር በተሸጋገረበት ምሽት ተመልክቻለሁ:: የበሃማስ ህዝቦች፤ "ከዚህ በኋላ፣ ቀጥተኛ የሆነ አስተዳደራዊ ቁጥጥርን በሚመለከት፣ ከእንግሊዝ ጋር



ምንም አይነት ግንኙነት አይኖረንም" ይሉ ነበር፣ እናም ነፃነታችንን ተቀዳጀን::

በሺዎች የሚቆጠሩ በስሜት የተነሳሱ ባሃማሳውያን፤ ነፃነቱ በሚታወጅበት ዋዜማ ከእኩለ ሌሊት ጥቂት ሰዓት ቀደም ብሎ በክሊፎርድ አደባባይ ተሰብስበው ነበር:: ይፋዊ የሆነው የአስተዳደር ሽግግር ሲደረግ የታቀደው ከንጋቱ ሐምሌ 10 ቀን 1973 (እ.ኤ.አ) ከቀኑ 6:00 ነበር:: የንግሥቲቱ ወኪል የነበሩት ልዑል ቻርልስ በዚያ ተገኝተዋል፤ የእኛ ጠቅላይ ገገርም በስፍራው አሉ፤ ከጥቂት ጊዜያት በኋላም ማዕረጋቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ይባላል:: የተለያዩ የፈንጠዝያ ዝግጅቶችም ነበሩ:: እኔ የመሠረትኩት የሙዚቃ ቡድንም የህገሪቱን ሠጣቶች በመወከል የነፃነት ዝማሬ እንዲያሰማ ተጋብዟል::

ልክ ከሌሊቱ 11:50 በሚሆንበት ጊዜ የህብረቱ ባንድራ በአደባባዩ መካከል በነበረው የባንድራ ምሰሶ ላይ አሁንም ይውለበለብ ነበር:: የታላቋ ብሪታኒያ አርማ የሚያመለክተን ነገር ቢኖር አሁንም በእንግሊዝ አገዛዝ ሥር መሆናችንን ነው:: 11:59 በሚሆንበት ጊዜ ዝቅተኛ ማዕረግ ያለው አንድ ወታደር በዚያ የባንድራ ምሰሶ ሥር ቆመና ባንድራውን ማውረድ ጀመረ:: ሌላ ወታደር ደግሞ በአጠገቡ ቆሞ ነበር፤ እርሱም የነፃይቱን ባሃማስ አዲስ ባንድራ ሰቀለ:: የመንግሥት ሽግግሩ ሲደረግ እኛ የአይን ምስክሮች ነበርን:: የእንግሊዝ ባንድራ ቁልቁል ሲወርድ ንጉሣዊ የሆነ ገዢ ዳግመኛ ላይኖረን ጊዜው እየቀረበ ነበር:: አዲሱ ባንድራ ሽቅብ በወጣ ጊዜ ደግሞ ጠቅላይ ገዢያችን ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆኑ ሰዓቱ እየተቃረበ ነበር:: የእንግሊዝ ባንድራ ቁልቁል መውረዱን ሲያበቃና የባሀማስ ባንድራ ከፍታው ጫፍ ላይ በደረሰ ጊዜ ሁሉም ነገር አበቃ:: በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ልዑላዊው ገዢ ቤተመንግሥታቸውን ለቀቁ፤ ወደ አይሮፕላናቸው አመሩና ባሃማስን ጥለው ሄዱ:: ንግሥቲቱ ጠርተዋቸው ነበር:: ደግሞም እኮ እዚህ ለመቀመጥ ምንም አይነት ሥልጣን ወይም መብት አልነበራቸውም::

ምንም እንኳን በባሃማስ ህዝቦች ሕይወት አስደሳች ስለነበረው ጊዜ ባወሳም፤ ምድራዊ የሆኑ ዜጎች ሰማያዊ የሆነውን መንግሥት በተቃወሙ ጊዜ የነበረው ሁኔታ የሚማርክ አልነበረም:: እንደገናም ደግሞ ከሕይወታቸው እንግዳ የሆነውን ገዢ ማስወገድ አልተቻላቸውም:: የተቃወሙት የራሳቸውን ትወልድ ሃገርና የመንግሥቱን ባለጠግነት ሊሰጣቸው ያቀደውን የተወደደ ንጉሥ - አባታቸውን ነው::

> የሰው ልጆች የትውልድ ሃገራቸውንና የተወደደውን ንጉሥ አባታቸውን ተቃወሙ

እዳም ሰዋዊ የነፃነት ባንድራ በሰቀለ በዚያው ጊዜ ውስጥ ደግሞ፤ የሰው ፍጥረት ከንጉሡና ከመንግሥቱ ጋር የነበረው ግንኙነት ፈጽሞ እስኪቋረጥ ድረስ የሰማያዊው መንግሥት ባንድራ ቁልቁል እየወረደ ነበር።

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፤ የባሃማስ ገዥ የነበሩት ሰው ወደ እናት አገራቸው በተጠሩ ጊዜ፤ ይኖሩበት የነበረውን ቤተ መንግሥት መልቀቅ ነበረባቸው። በምድር ቅኝ ግዛት ላይም፤ ሰዎች ራሳቸው ሰማያዊ የሆነው ገዢ የሚኖርባቸው ህንጻዎች ነበሩ። ሰዎች ራሳቸውን ከንጉሥ አባታቸው ነፃ ባደረጉ ጊዜ፤ ይህ ህንፃ የጠላት ግዛትና ንጽህና የጎደለው ከባቢ ሆነ፤ በመሆኑም ገዢው ከዚህ በኋላ በዚያ ህንፃ ውስጥ አይኖርም። ወደ እናት አገር ቤት ተጠራ።

## ያለ ገዢው መኖር

አዳምና ሄዋን በንጉሡ ላይ ጀርባቸውን ካዞሩና የገዢውን ህልውና ካጡ በኋላ፤ ሕይወት ለእነርሱ ምን ትመስል ነበር? ያደረጉት የዐመጽ ተግባር ሁልጊዜ "ውድቀት" ሆኖ ይጠቀሳል፤ ምክንያቱም ሲለማመዱት የነበረው የሕይወት ምቾት አሁን ከወረዱበት ሁኔታ ጋር ሲነፃጸር የሚታየው ልዩነት ነው። ልክ አንድ ልዑል ተቀምጦበት ከነበረው ልዑላዊ ዙፋን ላይ በጭቃ ወደተሞላ ጉድባ ውስጥ ወድቆ እዚያው መኖር ጀመረ እንደማለት ነው። በሰዎች ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ነፃነት ማለት ለእኛ አዎንታዊ ገጽታ ያለው ነገር ነው። በ1776 አሜሪካ ከእንግሊዝ አገዛዝ ወጥታ ነፃነቷን ያወጀችበት የአሜሪካ አብዮት፤ በየዓመቱ በተለያዩ ፌንጠዝያዎችና በቤተሰብ ስብሰባዎች ይከበራል። ነገር ግን ሰው ከመንግሥተ ሰማይ ነፃ የወጣበት ነፃነት ክብረ በዓል የሚገባው አይደለም። ለቅሶ የሚገባው ነው፤ ምክንያቱም በሰው ላይ ከደረሱት ነገሮች ሁሉ ይህ እጅግ አስከፊው ነበር። አዎ ያ የተሰጠን መንግሥት ሊኖረን ከሚችለው ነገር ሁሉ በላይ የላቀ ነበር።

በምድር ላይ የገዢው አስፈላጊነት ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ፣ እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ሁኔታዎች ምን እንደሚመስሉ መረዳት እንጀምራለን።

## *መንግሥትን ማጣት*

ገዢን ማጣት ማለት፤ በምድር ላይ መንግሥታዊ ግዛት (ከባቢ) ማጣት ማለት ነው። ገዢው የመንግሥት ህልውና ማረጋገጫ በመሆኑ፤ የእርሱ በዚያ አለመኖር ደግሞ ያለምንም ጥርጥር የሚያሳየው የመንግሥት ሕልውና አለመኖሩን ነው። ከዚያ በኋላ ያለው የምድር ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ

> የሰው ዘር ከመንግሥቱ ነፃ መውጣት ከምንጊዜውም ይልቅ የከፋ ነገር ነው።



ከሰማያዊው መንግሥት ሁኔታ ጋር የተቃረነ ሆነ።

## ከእውነተኛ ሕይወት መቆረጥ

ምንም እንኳን ሰዎች የተፈጠሩት ሕይወትን ከውስጥ ወደ ውጭ እንዲኖሩት ታቅዶ ቢሆንም፤ አሁን ሁኔታው የተገላቢጦሽ ሆነ። መንፈስ ቅዱስን አጥተውታል፤ እርሱ ደግሞ ከአባታቸው ጋር ለነበራቸው ግንኙነት ዋነኛው መስመር ነበር፤ በመሆኑም አሁን ከውጭ ወደ ውስጥ መኖር ጀመሩ። ሙሉ ለሙሉም በአምስቱ የስሜት ህዋሶቻቸው ላይ የሚደገፉ ሆኑ። ፍጥረታዊው ዓለም ከሕይወት እውነታ አንፃር ሊሰጣቸው የሚችለው ውስን እይታ - በውስጣዊው ዓለማቸው ላይ ሸክም ሆነ። አዳምና ሄዋን ካመፁ በኋላ የምናነበው የመጀመሪያው ቃል "ተገነዘቡ" ወይም "አወቁ" የተባለበት ምክንያት ይህ እንደሆነ አምናለሁ። በድንገት፣ ራቁታቸውን እንደሆኑ "ተገነዘቡ"። ይህ ማለት ከዚህ በፊት ይህን አያውቁም ነበር ማለት ነውን? እንደዚያ አይመስለኝም። የሚያመለክተው ይህን እንደሆነ አምናለሁ፤ ራቁትነት አንድን ነገር በመንፈስ ከመገንዘብ ይልቅ ውጫዊ የሆነ ንቃተ ህሊና (ሀሳብ) ነው። የሰዎችን የሕይወት ትኩረት ከመንፈሳቸው ይልቅ አካልና ስሜቶቹ ተቆጣጥረዋል። ከዚያ በኋላ ሰዎች በልባቸው ውስጥ መንፈሳዊ እይታ አልነበራቸውም፤ ይልቁን ስሜታውያን ሆኑ።

> በስሜቶች ላይ ብቻ የተመሠረተ እይታ ወደ ግራ መጋባት እንደሚያመራ የታመነ ነው።

በስሜቶች ላይ ብቻ የተመሠረተ እይታ ወደ ግራ መጋባት እንደሚያመራ የታመነ ነው። የሰው ልጅ ለሕይወት ትርጉም ለመስጠት በነፍሱ ላይ መደገፍ ጀመረ - በአዕምሮው፣ በፈቃዱና በስሜቶቹ በኩል ውስጡ የሚያቀብለውን መረጃ የሚያዳምጥ ሆነ ማለት ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የምናየው፣ የምንሰማው፣ የምንዳስሰው፣ የምንቀምሰውና የምናሸተው ሁሉ በሰብአዊ ልምምዳችን ዋንኞቹ ነገሮች ሆኑ። በዚሁ ሁኔታ፣ ፈጣሪ - ንጉሣችንን ለመረዳት በዋነኛነት የምንጠቀምበት ይኸው ፍጥረታዊ ስሜታችን ሆነ። ለምሳሌ፤ የሳይንስ መስክ የማይታየውን ዓለም ለመረዳት ከሚታየው ዓለም ብቻ ለመነሣት ይሞክራል። ይህ አቀራረብ አደገኛ ነው፤ ምክንያቱም የሰው ልጆች ፍጥረታዊ የሆነውን ዓለም፤ ከሰማያዊው መንግሥት መንፈሳዊ እውነታ አንጻር እንጂ ከራሱ ከፍጥረታዊው ዓለም እይታ አንጻር እንዲቃኙት ከቶ አልተፈጠሩም።

እኔ ሳይንስ "መጥፎ" ነው እያልኩ አይደለም። እንዲሁም ደግሞ እውቀት ክፉ ነው አላልኩም፤ ነገር ግን ትክክለኛ ከሆነው አቅጣጫ ለቆ መሄዱን ነው የተናገርኩት። እውቀት በእግዚአብሔር የተፈጠረ እጅግ አስደናቂ ስጦታ ነው። ነገር ግን ትክክለኛ ስፍራውን መያዝ አለበት፤ ያን

ጊዜ ዓላማውን ሙሉ ለሙሉ ስኬታማ ማድረግና ሙሉ ኃይሉን ለመጠቀም ይችላል። የሚታዩት ነገሮች የተፈጠሩት ከማይታዩት ነገሮች ነው፤ እናም አንድን ነገር በትክክል ለመረዳት ብቸኛው መንገድ፣ ነገሩ እንዴት እንደተሰራና ማንስ እንደሰራው መረዳት ነው። የፈጣሪ መንፈስ ብቸኛ ምንጭ፣ ደራሲና የፍጥረት ሁሉ ሠሪ በመሆኑ፣ ስለ ፍጥረታዊው ዓለምና ስለራሳችን ሙሉ የሆነ መረዳት የምናገኝበት ብቸኛው መንገድ እርሱ ነው።

የዚህን እውነት ጥልቅ የሆነውን ታላቅነት ልንጨብጥ ያስፈልገናል፤ የንጉሡን መንፈስ ማግኘት በጣም የሚጠቅመን ከማይታየው ንጉሥ ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን የራሳችንን የሰው ልጅነት ለመገንዘብ ጭምር ነው። በእውነት እዚህ ለምን እንዳለን፣ የምንኖርባትን ዓለም እንዴት መረዳት እንደምንችል የምናውቀው፤ በገርው አማካይነት ብቻ ነው፤ ይህም ማለት አካባቢያችንን እንዴት በትክክል እንደምናይ ማለት ነው። ገርው እኮ ሙሉ ለሙሉ ስለኛ መሆን ጉዳይ ቁልፍ ነው። ከእርሱ ጋር ካልሆንን በቀር የንጉሡን ባህርይ በአግባቡ ለመግለጽ አንችልም፤ ያንን ህብረት የሚሰጠው (የሚያስችለው) ደግሞ ገርው ነው።

የንጉሡን ልብ የሚያውቀው ገርው ብቻ ነው። ከሱ የመነሻ ሀሳብ ጋር እውነተኛ የሆነ ግንኙነት ከሌለን፣ ሰው ሆነን እንደ ተወለድንበት ዓላማ ልንሆን አንችልም። ስለራሳችን ሙሉ የሆነ መልስ እናገኝ ዘንድ ማገናዘቢያችን ገርው ራሱ ነው፤ ስለ ራሳችን መረዳት እንችል ዘንድ ቁልፉ እርሱው ነው። እውነተኛና ሙሉ የሆነ ሰው ልንሆን ካስፈለገ፤ በሚቻለው መንገድ እንደገና ግንኙነቱን ልንቀጥልና መንፈስ ቅዱስ እንደገና ሊኖርብን የግድ ነው።

## ሥልጣንንና ኃይልን ማጣት

ገርውን በማጣታችን ምክንያት ከአገር ቤት ጋር ያለንን ተግባቦት ብቻ አይደለም ያጣነው፤ ይልቁንም እርሱ የሰጠንን ኃይልና ሥልጣን ጭምር ነው ያጣነው። ኃይል ማለት ሁኔታዎችን የመቆጣጠርና በእነርሱም ላይ ተጽእኖ የማሣደር ችሎታ ማለት እንደሆነ ልብ በሉ። ከአዳም ዐመጽ በኋላ ንጉሡ ለአዳም ከተናገራቸው የመጀመሪያ ነገሮች አንዱና ተግባራዊ የሆነው፤ "ወደ መጣህበት ምድር እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራ ትበላለህ" ያለው ነው። ቀደም ብሎ ግን እንዲህ ነበረ ያለው፤ "በምድር ሁሉ ላይ ይግዙ ... "። አሁን ግን ንጉሡ በሚያሳዝን ሁኔታ ይህንን አስታውቀው፡-

*"ምድር ከአንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካምህ ከእርሷ ትበላለህ፤ እሾህና አሜከላን ታበቅልብሃለች። የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ መጣህበት*



*ምድር እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ። አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህ። "*

ንጉሡ የተናገረው ስለ ፍጥረታዊው እሾህ ብቻ አልነበረም። ራስህን ለመመገብ እጅግ ከባድ ይሆንብሃል፤ ይህን ለማድረግ ወዝህን ማንጠፍጠፍ ይጠበቅብሃል ነበር ያለው። ከዚያ በፊት ግን የአዳም ተግባር አድካሚ አልነበረም። በፍጥረታዊው ዓለም ላይ ሥልጣንና ገዥነት ነበረው። የተሠራው ለእርሱ ነበረ እንጂ በተቃራኒው እርሱ እንዲሠራበት አልነበረም።

## የራስ አስተዳደር ውጤት

ገርው፤ የሰውን ልጅ ከአገር ቤት ጋር የሚያገናኝ ነበረ፣ ሰዎች በምድር ላይ ያላቸውን ሥልጣንና የመግዛት ኃይል በአግባቡ መተግበር እንዲችሉ የሚያደርግ ነበር። እርሱ በተዋቸው ጊዜ ምድር በመሠረቱ ነፃ ግዛት ሆነች። ያለ ገገር የሆነ ቅኝ ግዛት ራስን ወደማስተዳደር ያመራል። እንደገናም፣ ዘመናዊ ለሆነው አስተሳሰባችን፣ ነፃነትና የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚሉት ቃላት አወንታዊ ቃላት ናቸው። የነፃነትንና የራስ አስተዳደርን ቀናት እናከብራቸዋለን። ነገር ግን እንደገና፣ እያነሳነው ያለው የነፃነት ጉዳይ በጨቋኝ አገዛዝ ላይ የተቀዳጀነውን ዐይነት ድል አይደለም። የባዕድ አገዛዝን እግረ ሙቅ የማስወገድም ዐይነት አይደለም። ልክ የምትወዱትን ቤተሰብ፣ እናት አገርን፣ የቢሊዮን ዶላር ወራሽነትን ሁሉን በአንድ ጊዜ እንደመቃወም ያለ ነገር ነው። ጠቢቡ ሰለሞን ያለውን መጥቀስ እፈልጋለሁኝ፤ "ቅን የምትመስል መንገድ አለች፤ የምትመራው ግን ወደ ሞት ነው።"

ለአንድ መንግሥት፤ ነፃ ከመውጣት መንፈስ የበለጠ እጅግ አደገኛና ፈታኝ የሆነ በላጭ ነገር የለም። ይህ ለሰው ልጆች መንግሥታት የሆነ እንደሆነ የኃይል፣ የሀብትና ምናልባትም ክብርን እንደማጣት ተደርጎ ሊተረጐም ይችላል። ይሁን እንጂ ለሰማያዊው መንግሥት የሆነ እንደሆነ፣ ይህ ማለት የቤተሰባቸውን ስምና ሀብት ወራሾች የሆኑ ልጆች መንፈሳዊ ሞት ማለት ነው። ለልጆቹ ደግሞ የፍርሃት፣ ለመኖር ሲባል ብቻ የሚታገል አዕምሮና የሞት አይቀሬነት እውቀት ወደ ሕይወታቸው መግባት ማለት ነው።

ነፃ የሆነ ሰው ስትሆን፣ ራስህን በራስህ ማስተዳደር እንደሚገባህ ታውቃለህ። እንደዚሁ ሁሉ አንድ አገር ነፃ መንግስት ስትሆን፤ ሙሉ ለሙሉ በራሷ መንገድ ልትጓዝ ግድ ነው። የባሃማስ ገገር ልዑል የነበሩት ሰው ሐምሌ 10 ቀን በሃማስን ለቀው ሲወጡ፤ ሙሉ ለሙሉ በራሳችን ነበር - ይህም ማለት በራሳችን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት፣ ውስጣዊ አሠራሮቻችንን በሚመለከቱና በአስተዳደር ሁለንተናዊ ሁኔታዎች ሁሉ ራሳችን ሆንን። በዚሁ መልክ የሰው ልጅ ራሱ ራሱን ይችል ዘንድ

አደረገ:: ይሁን እንጂ ሰዎች የታቀዱት ስሜቶቻቸውን ብቻ እየተጠቀሙ ተግባራቸውን የሚያከናውኑ ተደርገው አልነበረም:: ወላጅ የሌላቸው ልጆች በማያውቁት ዓለም ላይ ከመሬት የወዳደቀ ምግብ እየለቀሙና በጭንቀት እየጮሁ፣ በርቀት በሚገኝ አገር ውስጥ እየተቀጡ እንደሚኖሩት ዐይነት ሕይወት ሊኖሩ አይጠበቅባቸውም:: ሰዎች ታቅደው የተፈጠሩት ስኬታሞች እንዲሆኑና እንዲበለጽጉ፣ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ኃይል የፈጠራ ችሎታቸውን ከፍተኛ ጣራ ይጠቀሙ ዘንድ ነው:: የገዢው ወደ አገር ቤት መጠራት በምድር ላይ ለሚኖሩት አጅግ አሳዛኝ ኪሣራ ነበር::

## ዓመጸኛ ሁኔታ

የሰዎች ነጻነታቸውን ማወጃቸውና በዚህ ምክንያት የገዢው ጥሏቸው መሄድ፤ የሰውን ልጅ ዓመጸኛ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንዲወድቁ አደረጋቸው:: በእያንዳንዱ የሰው ዘር ሕይወት ውስጥ እየተተገበረ ያለው ምድራዊው አስተዳደር፤ በመሠረቱ አመጸኛና የአገር ቤቱ መንግሥት ዓላማ የሌለው ሆነ:: በዚህ መንግሥት ውስጥ ከመነሻው ዓመፅ የተነሣ እያንዳንዱ ሰው ገና ሲወለድ ጀምሮ አመጸኛ ነው:: ይህንን ጉዳይ የሥነ መለኮት ምሁር የተርሴሱ ጳውሎስ እንዲህ ይገልጸዋል፤ "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል":: እኛ ሁላችን መሠረታዊ የሆነው ባህርይና በእርሱ ያለው የከበረ ነገር ሁሉ የሌለን ሆነን:: እርሱ ፍጹም የሆነ ንጉሥ ነው፤ መንግሥቱም ፍጹማዊ የሆነ አስተዳደር ነው:: እኛ ግን በእኛ ውስጥ የነበረውን ያንን የፍጹምነት መልክ አበላሸነው:: እናም በምድር ላይ ባለው አስተዳደር ውስጥ በግለሰብም ይሁን በህብረት የምናደርገው የጥረት መንገድ ሁሉ የዘቀጠ ነው::

## የጨለማና የሞት ባህል

አንድ አገር በቅኝ ግዛትነት ቆይቶ ነፃነቱን በተቀዳጀ ጊዜ፤ የራሱን ገዢ ይመርጣል ወይም ይሾማል:: ይህ ገዢ የራሱን አገር ባህል እንጂ የቀደመውን አገዛዝ ባህል ለህዝቡ አያስተምርም:: እንዲዚሁ ሁሉ፣ ሰማያዊው አስተዳደር ገዢውን ወደራሱ በጠራው ጊዜ፤ ሰዎች ሰማያዊውን ባህል መማር አቆሙ፤ የራሳቸውን ባህል ፈጠሩ እናም ለልጆቻቸው ሁሉ አስተላለፉ:: በመንግሥተ ሰማይ አሴት መለኪያ መኖራችን አበቃና ስለሕይወት ከራሳችን ነፃ አስተሳሰብ አኗያ መመልከት ጀመርን::

> የገዢው ተጠርቶ መሄድ በምድር ላይ ለሚኖሩ ሁሉ አጅግ አሳዛኝ ኪሣራ ነበር



እዚህ ጋ ቆም ብለን ራሳችንን እንጠይቅ፤ አሠራራችን ምን ያህል ጤናማ ነው? የባህርያችን ባህል ምን እየመሰለ ነው የመጣው? ምድር ገዢውን ካጣች በኋላ ከተፈጠሩት የመጀመሪያ ነገሮች አንዱ፣ የአንድ ሰው በታላቅ ወንድሙ መገደል ነው:: አዲሱን ባህል የጀመርንበት ይህ ምን ዐይነት መንገድ ነው! ምድርን ወደ ሰማያዊው መንግሥት ባሕል የማሸጋገሩ ነገር ቀርቶ የጨለማው መንግስት እና ባህል ሰፊነ በምድርም ላይ ተስፋፋ:: ዝሙት፣ ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት፣ ጋጠወጥነትና አንዱ በሌላው ላይ ማመጽ የጨለማው መንግሥት ባህሎች ሲሆኑ፤ ወጣቱንና ሽማግሌውን፣ ብርቱውንና ደካማውን፣ ማንንም ሳይመርጥ የሚያጠፋ ነው:: አሁንም፣ በወንጀል ላይ ወንጀልን እየፈጸምን ነው፣ ወንድም ወንድሙን እየገደለ እየተመለከትን ነው:: የንጉሡ ገዢ በማይገዛበት ስፍራ ሁሉ የምናገኘው ነፍሰ ገዳይነትንና ሰዎች በሰዎች ላይ የሚያደርጉትን የጭካኔ ድርጊት ነው:: ጋጠወጥነትና ጥፋት ቤተሰብን፣ ማህበረሰብን፣ ሥራንና አስተዳደርን መላውን የሰውን ልጅ ህልውና በጣም ይጎዳሉ::

ይህ ሁሉ ነገር የሆነበት ምክንያት የሰው ልጆች የንጉሡ አባታችን የቀድሞ ባለሟል የነበረውን፤ የምድርን ግዛት ለራሱ ለመውሰድ የፈለገውን የአመጸኛውን የማታለያ ውሸት በመስማታቸው ነው:: የናዝሬቱ ኢየሱስ ሉሲፈርን የሚገልጸው፤ "የውሸት አባት" እና "ነፍሰ ገዳይ" ብሎ ነው:: እንዲሁም ደግሞ፤ "ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ፣ ሊያጠፋ እንጂ ስለሌላ አልመጣም" ይለዋል::

ይህ ከክብር የወደቀው የቀድሞ ጄኔራል፤ በምድር ላይ የመግዛት ሥልጣንን ያዘ፤ ተገቢ ውጤቱም ታላቅ ጥፋትና ሞት ሆነ:: እንደ ህገ ወጥ ገዢነቱ በምድር ላይ ያለው ፍላጎቱ ነፃነትን ማምጣት አይደለም:: የሰዎችን ሕይወት መስረቅ እና ፍፃሜውም ማጥፋት ነው:: በምድር ላይ ባዕድ የሆነ ገዢ በመሆኑ እቅዱ ቀድሞ የነበረውን የህዝቡን ባህል መደምሰስ ነው:: አገዛዙን የሚያካሄደው አጥፊ በሆነ የጨለማ መንግሥቱ አማካይነት ሲሆን ሰዎች ወድደው ይሁን በግዴታ ለዚህ ዓላማው ተባባሪዎች ይሆናሉ::

> የጨለማው መንግሥትና ባህል በምድር ላይ መጣ፣ መስፋፋትም ጀመረ

ለዚች ፕላኔት (ምድር) የሠራንላት ነገር ምንድን ነው? ሰዎች በንጉሡ ላይ ክህደት ከፈፀሙበትና ገዢው ከተሰያቸው ጊዜ ጀምሮ፤ የሰው ልጅ የንጉሡን ቅኝ ግዛት ሊቆጣጠር የሞከረው ያለ ንጉሡ አዕምሮና ልብ ነው:: ያለ ንጉሡ ባህርይ ምድርን ለማስተዳደር መሞከራቸው የሚያስከትለው ለሕይወት ጥያቄያቸው መልስ ሊሰጡ በሚያደርጉት ትግል የሥልጣናቸውንና የኃይላቸውን መከፋፈል ነው:: ይህ እንግዲህ በምድር ላይ ያለው ድህነት፣ የዘር ማጥፋት፣ የሽብርተኝነት፣ የፖለቲካ ሽፍጥ፣ የአዳንዛኘ ዕጽ

ሱሰኝነት፣ የትዳር መፈራረስና ይህን ይህን ብለን የምንጠራው የማንኛውም ክፉ ነገር ሁሉ ምንጭ ነው። የመሠረትነው የአመጽና የግራ መጋባት መንግሥት ነው። ይህ ዓለም ያለገገርው ጥፋት ነው።

## ንጉሡ የሰጠው ተስፋ

የምድር ቅኝ ግዛት ገገርው በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ተጎሣቆለ። ያለ እርሱ መገኘት፣ የሰው ዘር ክብሩንና ሃላፊነት የመውሰድ አቅሙን አጣ፤ ግራ ወደ መጋባትና ወደተመሰቃቀለ ሁኔታ ውስጥ ወረደ። ህዝቡ እየኖረ መሞትን ተለማመደ። ምንም እንኳን እስከ አሁን ድረስ ብዙዎች በጥሩ ሁኔታ ነገሮችን ሊያከናውኑ ቢፈልጉም፤ ዛሬም የምድር እውነተኛው ገጽታ ይህ ነው። የአዳምና የሄዋን ዘሮች በመሆናችን፣ የሰማይን መንግሥት በመወከል መግዛት አልቻልንም፤ ምክንያቱም የመግዛት ሥልጣናችንን ለሉሲፈር የጨለማ ባህል አሳልፈን ሰጥተናል።

ይሁን እንጂ፤ የሰዎችን አመጽና የገገርውን መሄድ ተከትሎ ወዲያው የሆነው አንድ ነገር ነው፤ ንጉሡ የገገርውን መመለስና ምድር እንደገና የሰማያዊው መንግሥት ታማኝ ግዛት ሆና እንደምትታደስ፣ የሰጠው ተስፋ ነው። የሰማያዊው መንግሥት፣ ለሰዎች ከሰጣቸው ተስፋዎች ሁሉ እጅግ ታላቅ የሆነው ተስፋ የገገርው እንደገና መመለስ ነው፤ ምክንያቱም ማንኛውም የሰው ፍጥረት እውነተኛ ለሆነ ሕይወት የሚያስፈልገው እርሱ ነው። ለመላው ዓለም የሚያስፈልገው እርሱ ነው፤ ያለበለዚያ የምድር ግዛት፡ ለዘላለሙም የተመሰቃቀለችና ሞት የነገሰባት ሆና ትቀራለች።

አመጹ ከተካሄደ በኋላ ወዲያው እንኳን፤ ንጉሡ መንግሥቱን እንዴት አድርጎ እንደሚያድስ ጠቋሚ የሆነ ሀሣብ ተናግሯል። ሉሲፈርን እንዲህ አለው፤ “በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘሯ መካከል ጠላትነትን አኖራለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።” የንጉሡ እቅድ ቅኝ ግዛቱን እንደገና የሚመሠርተውንና የሚገዛውን በቅኝ ግዛቱ ውስጥ እንዲወለድ ዘሩን መላክ ነው። እርሱ የጨለማውን ግዛት ኃይል ይቀጠቅጣል፤ ተሰርቆ የተወሰደውን የመንግሥቱን ሥልጣን ይመልሳል፤ ኃይልንና ሥልጣንን አስቀድሞ ተሰጥቶት ለነበረው ለሰው ልጅ እንደገና ይመልሳል ዳግመኛ ለአንድ ጊዜ የሰማይን መንግሥት ወክለን የምድራችን አስተዳዳሪዎች ልንሆን ስፍራችንን እንይዛለን። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ንጉሡ ገገርውን በምድር ቅኝ ግዛት ላይ እንደገና ስለሚሾመው ነው።

## ገዢውን መሻት

ማንኛውም ሰው ለኃይልና ለሕይወት ምንነት ትርጉም ውስጣዊ ፍለጋው (መሻቱ) ይህ እንደሚሆን አምናለሁ፤ ባያውቁትና ባያስተውሉትም እንኳን የሚፈልጉት የገገርውን መመለስ ነው። ብዙ



ሰዎች በሕይወታቸው ያጡት አንድ ነገር እንዳለ ይሰማቸዋል፤ ይሁን እንጂ በትክክል ምን እንደሆነ እርግጠኞች አይደሉም። ይህንን የባዶነት ክፍተት በልዩ ልዩ ነገሮች ለምሳሌም በገንዘብ፣ በግንኙነት፣ በቡድኖች፣ በአደንዛዥ እፅ፣ በወሲብ፣ በአልኮል፣ በሥራ፣ በስፖርት ወይም በመዝናናት ሊያሟሉ ይሞክራሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ማንኛውም ሰው፤ ክርስቲያን፣ እምነት የለሽ፣ ሂንዱ፣ ቡዲሂስት፣ ሙስሊም፣ ሽንቶይስት፣ ሳይንሳዊ አመለካከት ያለው፣ አመጸኛውና ሰይጣንን አምላኪ እንኳን ቢሆን ትልቁ መሻታቸው ይሄው እንደሆነ አምናለሁ። ሰው ሁሉ በሕይወቱ የጐደለውን ሊያሟላ ይፈልጋል፣ የጐደለውን ሊያሟላ የሚችለው ገዢው በሕይወቱ ሲገኝ ብቻ ነው። የሰው ዘር ያለ ገገርው ምንም ነገር ለማድረግ አቅም አልባ ነው፤ ምክንያቱም መቼም ቢሆን መች በራሱ ሙሉ ሊሆን አይችልም፤ መሠረታዊ ስሪቱ የመንፈስ ቅዱስን በእርሱ ውስጥ መገኘት ይፈልጋል።

በመሆኑም፤ የንጉሡ ተስፋ ስለ መፈጸም አስመልክቶ ከሰማያዊው መንግሥት ለምድር የተላከው መልዕክት የገገርው እንደገና ተመልሶ መምጣት ነው - መልዕክቱ የሃይማኖት መልዕክት አይደለም። እንደገናም ደግሞ ሰዎች የራሳቸውን ችሎታ በመጠቀም ችግሮቻቸውን ለማስወገድ የሚጠቀሙበት ራስን የመርጃ ዘዴ አይደለም። መልዕክቱ ስለመንግሥቱና ስለ ንጉሡ መንፈስ መመለስ ነው።

# ምዕራፍ ዐራት

## የገዢው የመመለስ ተስፋ

*ዋናው ግብ መንገድ ሲሆን፣ ዝቅተኛው ከፍተኛ ሲሆን፣ ፍትህ አልባነት መሰፈኑ አይቀሬ ነው::*

ገዢውን ስለመመለስ የንጉሡን እቅድ በጣም በጥልቀት ከመመልከታችን በፊት፤ እስኪ ስለ መንግሥተ ሰማይና ምድርን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ስላሰው እቅድ ዋንኛ የሆኑ ነገሮችን እንከልስ::

- ✓ የዘላለማዊና የማይታየው መንግሥት ንጉሥ ወደፈጠረው ፍጥረታዊ ዓለም ማለትም ወደ ምድር የራሱን ባህርይና አገዛዝ ለማስፋፋት ፈለገ:: ለማያዊው መንግሥቱ፣ በዓለም ላይ የሚገዛበት፣ ተጽእኖ የሚያመጣበት፣ በፈቃዱና በዓላማው፣ በመሻቱም ሥር የሚያውልበት ነው:: መንግሥተ ሰማይ የእግዚአብሔር መንግሥት ወይም አገር ቤት ነው፤ ምድር ቅኝ ግዛቱ ነች::
- ✓ የሰው ልጆች የተፈጠሩት በንጉሡ መልክ ሲሆን፤ የንጉሡ መንፈስ በነሱ እንዲኖር ተሰጥቷቸዋል:: የንጉሡ መንፈስ ለመንፈሳቸው፣ ለነፍሳቸውና ለአካላቸው ሕይወትን ሰጥቷቸዋል::
- ✓ ሰዎች የተፈጠሩት እንደ ፈጣሪ - ንጉሣቸው አሠራር እንዲተገብሩ ታቅደው ነው:: የንጉሡ መንፈስ በሰዎች ውስጥ መገኘት የንጉሡ ባህርይ ጠባይ እንደነበራቸው የሚያረጋግጥ ነው:: እንደገናም ደግሞ እርሱ በሰማያዊው መንግሥት ላይ በሚገዛበት መንገድ በምድር ላይ የእርሱ በሆነ የፍቅር፣ የምህረት፣ የጨዋነትና የይቅርታ ባህርይ መግዛት እንደሚችሉ ዋስትና ይሰጣል::
- ✓ ንጉሡ ምድርን በቀጥታ የመግዛት ፍላጐት የለውም፤ ይልቁንም ቅኝ ግዛቱን በልጆቹ አማካይነት የማልማት፣ እና በምስለኔ ገዢዎቹ የመሥራት እቅድ ነበረው:: የንጉሡ መንፈስ ከሆነው ከዋናው ገዢ ሥር ሆነው በምድር ላይ አገዛዝን ይስማመዳሉ::



- ✓ የአዳምና የሔዋን የነፃነት ዕወጃ የሰው ዘር ከንጉሡ ጋር የነበረውን ህብረት አቋረጠው፤ ገዢውም ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዲጠራ ሆነ::
- ✓ የገዢው ምድርን መልቀቅ ማለት የሰማያዊው መንግሥት ለቆ መሄድና በምድር ቅኝ ግዛት ላይ የነበረው ቀጥተኛ ተፅዕኖ ማብቃት ማለት ነው::
- ✓ የሰው ልጅ በሰማያዊው አስተዳደራዊ ሥልጣን ላይ ካመጸ በኋላ፤ ንጉሡ ወዲያውኑ ለልጆቹ ገዢውን መልሶ እንደሚልክላቸው አስታወቀ::
- ✓ ፈጣሪው ንጉሡ ለሰው ልጆች ከገባላቸው ተስፋዎች ሁሉ ትልቁ ተስፋ፤ ገዢው ተመልሶ በመካከላቸው እንደሚኖር የገባላቸው ተስፋ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ የሕይወት ቁልፍ ነው::
- ✓ የንጉሡ መንፈስ ወደ ሰው ልጆች መመለስ የሚያመለክተው የንጉሡ መንግሥት ወደ ምድር መመለስ ነው::

ከላይ የዘረዘርናቸው ነገሮች ሁሉ የሚመሩን ወደዚህ መደምደሚያ ነው፤ የፈጣሪ - ንጉሥ የመቤዠት መርሃ ግብር ዋንኛ ዓላማ፤ የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሁሉ ከሰው ዘር ጋር የተነጋገረበት ዋንኛ ጉዳይ ሲሆን እርሱም የገዢው ወደ ቅኝ ግዛት ምድሩ መመለስ ነው::

በዚህ የእመሰካከት አቅጣጫ፤ አሁን ደግሞ የተቀደሰውን መጽሐፍ የብሉይ ወይም የመጀመሪያ ኪዳን ማዕከላዊ የሆነ ሀሣብ ወይም ጭብጥ እንመልከት፤ ይሄው መጽሐፍ የአይሁዳውያን ቅዱስ መጽሐፍ ስብስብ ተብሎ ይታወቃል:: እንዳንዶች የዚህ መጽሐፍ ጭብጥ በአንድ አምላክ ብቻ የማመን ሃይማኖት መፈጠር ነው ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ ስለ የጥንታዊው ዕብራዊያን መንግሥት መነሣትና መውደቅ ነው ይላሉ:: እንደገናም ሌሎች ደግሞ የተለያዩ ልምዶችና የመስዋእት አቀራረብ ዘገባዎች አድርገው ይመለከቱታል:: ከእነዚህ አመለካከቶች በመነሣት መጽሐፉን ከቃኘነው ማዕከላዊ የሆነ ጭብጡን እንስተዋለን::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጥና አብይ ትኩረት

የቅዱሳት መጽሐፍት አብይ ትኩረት ምንድን ነው? የኖህ፣ የአባቶቻችን የነ አብርሃም፣ የይስሃቅና የያዕቆብ እንዲሁም የእስራኤል ህዝብ ታሪክ የተዘገበበት ምክንያት ለምንድን ነው? በደም የሚቀርቡ መስዋዕቶች ዓላማስ ምን ነበር? በመጽሐፍቱ ውስጥ ስለ ካህናት፣ ስለነቢያትና ስለነገሥታት የዘር ሐረግ መዘገቡ ለምንድን ነው?

ምንም እንኳን ድርጊቶቹ በእስራኤል ህዝብና መንግሥት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ቢሆኑም፤ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ጭብጥ ዓለም ዓቀፋዊ ነው፡፡ ለህያው ፍጥረት ህልውና የተሃድሶ ቁልፍ የሆነ፣ በምድርም ላይ ለሚኖር ለማንኛውም የሰው ልጅ እውነተኛ የሆነው ሕይወት እንደገና መመስረት ነው፡፡ በዘገባዎቹ ላይ ያሉ ሰዎችና ሁኔታዎች የሚያሳዩን ነገር ቢኖር፤ ንጉሡ መንፈሱን በሰዎች መካከል መልሶ እንደሚልክ ያለውን እቅድና ደግሞም ገና በተፈጠሩ ጊዜ እንደነበሩበት ሁኔታ እንዲሆኑ ነው፣ ይተገብሩት ዘንድ ይገባቸው የነበረውንም ተግባር ያደርጉ ዘንድ እንዲችሉ፣ እና አስደናቂ የሆነውን የተፈጠሩበትን ዓላማና የነበራቸውን የድርጊት ኃይል ሙሉ ለሙሉ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ነው፡፡

> **የብሉይ ኪዳን**
> **መጻሕፍት ጭብጥ**
> **ለሰው ልጅ ህልውና**
> **የተሃድሶ ቁልፍ ነው፡፡**

የዘፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች፤ የሰማያዊው መንግሥት ግዛቱን በምድር ላይ ለማስፋፋት የነበረውን እቅድ ያመለክቱናል፡፡ ሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የእቅዱን መደናቀፍና ወዲያውኑ የተሰጠውን የተሃድሶ ተስፋ ያሳየናል፡፡ ከሶስተኛው ምዕራፍ ጀምሮ እስከ ብሉይ ኪዳን የመጨረሻ መጽሐፍ ያሉት ክፍሎች ደግሞ ገዢውን እንደገና ለመመለስ ያለውን የንጉሡን እቅድ የሚገልጹ ናቸው፡፡ በዚያ የምናነባቸው ሁኔታዎች፣ ሰዎችና መርሃ ግብሮች ሁሉ ይህንን የመጨረሻ ግብ የሚያገለግሉ ናቸው፤

1. በማያቋርጥ ሁኔታ የገዢውን እንደገና የመመለስ ተስፋ ያሳስባሉ፡፡
2. በምድር ላይ በሚኖሩ አንዳንድ ቤተሰቦች ሕይወት ውስጥ የንጉሡን ጣልቃ ገብነት ያሳያሉ፣ በዚህም የገዢውን እንደገና መመለስ ተግባራዊ የሚያደርጉትን ዘሮች ሕይወት መታደጉን ያሳያሉ፡፡
3. መንግሥተ ሰማይን የሚመስል መንግሥት በምድር ላይ እንደገና መመለስን ያሳያሉ፡፡
4. ገዢው ብቻ የምድርን ቅኝ ግዛት ከሰማያዊው መንግሥት ጋር እንደገና የሚያገናኝ እንደሆነ እውነቱን ይገልጣሉ፡፡
5. ዜጋ የሆኑ ልጆችን ከንጉሡ ጋር የሚያስታርቀውን ዘር መምጣትና የገዢውን መመለስ ሥልጣን አስቀድመው ይናገራሉ፡፡

በሌላ አባባል፤ ከሰው ልጅ አመጽ በኋላ፤ የንጉሡ መሻት በመሠረቱ ይህን ይመስላል፤ "ዓለምን የፈጠርኩበት ዓላማ ተደናቅፏል፤ እንደገናም አስተካክለዋለሁ፡፡ መንፈሴ ምድራዊ በሆነው ማደሪያ በሰው ላይ ከዚህ በኋላ አይኖርም፡፡ በመሆኑም መንፈሴን እንደገና በሰዎች ላይ እመልሳለሁ፤ መንግሥቴም በምድር ላይ እንደገና ይሠራል"፡፡



በብሉይ ኪዳን የምናየው የእግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ መግባት ወደዚህ ታላቅ ግብ የመድረስ መንገድ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ፍጥረት ተገለጠ፤ በዚህም "የእርሱ እቅድ እንዲህ ነበር፤ ዐመጻችሁ ተስፋ በሌለው ሁኔታ ውስጥ እንድትገቡ አድርጓችኋል፡፡ በመሆኑም እኔ ራሴ በአካል ወደ ምድር እመጣለሁ፡፡ የልብን ንጽህናና ሙሉነትን የምታገኙበትን መንገድ እንደገና አዘጋጃለሁ፡፡ እናም ገዢው በእናንተ ውስጥ ደግሞ ሊኖር ይመጣል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፣ ገዢውን እንደገና ደግሞ በእናንተ ውስጥ እንዲኖርና ምድር ሰማያዊ መንግሥቴን እንድትመስል የማድረግ ዓላማዬን እንዲተገበር በምድር ላይ እሾመዋለሁ"፡፡

## የሰው ልጅ ቅድስናን መፈለግ

የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በዝርዝር እንደሚያብራሩልን፤ አዳምና ሄዋን መንፈስ ቅዱስን ባጡ ጊዜ የሰው ዘር ሁሉ ያልተቀደሰ ሆነ፡፡ ከዚህ ቃል ጋር የተያያዙ ምንነታቸውን በርግጥ የማናውቃቸው ብዙ ሃይማኖታዊ ገጽታዎች እንዳሉ አስባለሁ፡፡ የዚህን ቃል ፍሬ ነገር ፈጣሪው - ንጉሥ ለእስራኤል ህዝብ በተናገረው ቃል ውስጥ እናገኛለን፤ "እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ህዝብ ትሆኑልኛላችሁ፡፡" በዚህ ረገድ ቅድስና የሚለውን ቃል የተጠቀመበት *ህዝብ* ከሚለው ቃል ጋር አያይዞ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ በግልጽ እንደምናየው እርሱ እየተናገረ ያለው መስቀልን በአንገት ላይ ስለማንጠልጠል ወይም ዘርፋፋ የክህነትን ልብስ ስለመልበስ ወይም በሆነ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ውስጥ ስለመግባት አይደለም፡፡

ታዲያ የቃሉ ጽንሰ ሀሣብ ምንድን ነው? በዚህ ስፍራ የምገልጸው ቃል ሁለት የተያያዙ ግንኙነቶች ያሉት ነው፡፡ አንደኛው "ንጹህ" የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ "መስጠት" ወይም "መለየት" የሚል ነው፡፡

እነኝህ ቃላት በመጀመሪያ ደረጃ የሚገልጹት፤ አንድ ነገር ለተለየ ተግባር "መለየቱን" ነው፡፡ በዚህ እሳቤ፤ ቅድስና የሚለውን ቃል ለብዙ ነገሮች እንጠቀምበታለን፡፡ ለምሣሌ በጣም የምወደውን ስኒዬን ለይቼ በማስቀመጥ፤ "ይህ ስኒ እኔ ብቻ የምጠቀምበት ስሆን፤ የምጠቀምበትም ሻይ ለመጠጣት ነው፤ ከዚህ ውጭ ለሌላ ለምንም ተግባር አይውልም" እላለሁ፡፡ የቀደስኩት በመለየትና ለተለየ ዓላማ ወስኜ በማስቀመጥ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ንጹህ የሚለው ቃል እንደ አውዱ ዝም ብሎ "ንጹህ" ከሆነ ነገር የዘላለ ትርጉም አለው፡፡ ንጹህ የሆነ ነገርን የሚያመለክት ነው፡፡

ከሰው ልጆች ጋር በተያያዘ መልኩ ንጉሡ እናንተ ለእኔ "የተቀደሳችሁ ሁኑ" ሲል ተናገረ፡፡ እንደ ሰው እንዴት ነው አንተ ቅዱስ የምትሆነው? ከዚህ ጋር በተዛመደ ሁኔታ ቅድስና ማለት፤ "እኔ ለአንተ ብቻ የተለየሁ ነኝ፡፡ ለአንተ መሰጠት ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ታማኝነቴም ለሌሎች

ሳይሆን ለአንተ ብቻ ይሆናል:: ከጀርባ የተሰወረ ዐላማ የለኝም" ማለት ነው::

ቀጥሎ ደግሞ ፈጣሪው ንጉሥ ራሱን "ቅዱስ" አምላክ ነኝ ብሎ ሲገልጽ ምን ማለቱ እንደሆነ እንመልከት:: ይህ ማለት ራሱን ለራሱ ብቻ የለየ ማለት ነውን? በፍጹም፤ ይህ ማለት እርሱ ለራሱ እውነተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው:: በማንነቱ፣ በእቅዱ፣ በሚናገረው ነገርና በድርጊቱ ሁሉ የታመነና የማይለዋወጥ ነው:: እኔ ቅድስናን የማዛምደው ከእውነታ ጋር ነው:: ንጉሡ ሙሉ በሙሉ "የተዋሐደ" ወይም "አንድ" ነው:: የእርሱ ባህርይ ንጹህ የሆነ በመሆኑ ምንም ዐይነት የተሰወረ ዓላማና እሳች የሆነ ሀሳብ ሊኖረው የማይችል ነው:: ለዚህም ነው ንጉሡ መዋሸት የማይችለው:: ለዚህ ነው ንጉሡ - አባት ከንጉሡ - ልጅ ጋር በገኘሮው እንደገና መመለስ የሚስማሙት:: ለዚህም ነው ንጉሡ - አባትና ንጉሡ - ልጅ ከገዢው ጋር ቅራኔ ውስጥ በፍጹም የማይገቡት:: የፈጣሪ - ንጉሥ ሦስቱ አካላት አንድ ወይም የተዋሐዱ ናቸው::

በመሆኑም በቅድስና መኖር ማለት፤ "ከራስ ጋር አንድ መሆን ማለት ነው::" የናዝሬቱ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ፤ "በሰማይ ያለው አባታችሁ ፍጹም (ቅዱስ) እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ" ብሎ ሲናገራቸው፤ ንጉሡ - አባታችሁ ከራሱ ጋር አንድ እንደሆነ ከራሳችሁ ጋር አንድ ሁኑ፤ ማለቱ ነው:: ተግባራዊ የሆነው ተዛምዶው ይህ ነው፤ አንድ ነገር እንደምታደርግ ከተናገርክ አድርገው:: አንድ ነገር ለማድረግ ቃል ከገባህ፤ ፈጽመው:: በእውነት የተቀደስክ ከሆንክ፤ አንድን ነገር እንደምታደርግ ተናግረህ ተቃራኒውን አታደርግም:: በአደባባይ የምታሳየው ባህርይ በግልህ ስትሆን ከሚታየው ባህርይ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ንጉሡ የሚያደርገው የትኛውም ነገር ከባህርይው ጋር የሚጋጭ የሚደብቀውም የለም:: ከማንነትህ ጋር የሚቃረን አንድ ነገር ካልተናገርክ ወይም ካላደረግክ በስተቀር ምንም አይነት ነገር አትደብቅም:: አዳምና ሄዋን ንጉሡን እስካልታዘዙበትና እስካልዋሹ ጊዜ ድረስ ሙሉ ለሙሉ ህብረት ነበራቸው፤ በእነርሱ ውስጥ ያስቀመጠውን መታመንም አፈረሱት::

> ቅድስና ከሐቀኛነት ጋር የተዛመደ ነገር ነው:: ይህም ማለት ከራስ ጋር አንድ መሆን ማለት ነው::

የብሉይ ኪዳን ማዕከላዊ ሀሣብ፣ አዳምና ሄዋን ባመጹ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ የሰውን ዘር ትቶ መሄድ ነበረበት የሚል ነው:: ምክንያቱም ከዚያ በኋላ የሰው ልጆች በአስተሳሰባቸው ንጹህ አልነበሩም ወይም እርስ በእርሳቸው ህብረት አልነበራቸውም፤ እንዲሁም ለእግዚአብሔር አልተሰዩም ወይም ከእርሱ ጋር መስማማት አልቻሉም:: ገዢው ንጹህ



የሆነ መንፈስ በመሆኑ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ባለው የሰው ዘር ማንነት ውስጥ ሊኖር ከቶውንም አይችልም::

## የንጉሡ እቅድ ደረጃዎች

የሰው ልጆች ራሳቸውን ከገዢው ካገለሉ በኋላ፤ ንጉሡ ታላቅ ተግዳሮት ነበር የገጠመው:: የሰው ልጆች በእርሱ መገኘት ውስጥ መኖር ያስፈልጋቸዋል፤ የርሱም መገኘት በውስጣቸው ሊኖር ይገባል:: ይሁን እንጂ ያሉበት ሁኔታ ይህ እንዲሆን አይፈቅድም:: ገዢውን ወደ ልጆቹ ለመመለስና ምድር የእርሱን መንግሥት ዓላማ በማንፀባረቅ እንድትቀጥል ለማድረግ በፈለገ ጊዜ ልጆቹ ያሉበትን ሁኔታ መለወጥ የሚችል አንድ ነገር መሆን ነበረበት::

የንጉሡ ገዢውን መልሶ የመላክ እቅድ ደረጃ በደረጃ የሚገለጥ ነበር::

1. ገዢው በሰዎች ውስጥ ባይሆንም በሰዎች ላይ የሚመለስበትን መርሃ ግብር ዘረጋ፣ ይህም የሆነው ህብረቱ (አንድነቱ) እንዳይጠፋ ለማድረግ ነው:: *የእርሱ መንፈስ ለሰማይ መንግሥት አገዛዝ ለመገዛት ራሱን በሚሰጥ በማናቸውም ሰው ላይ ሊመጣ ይችላል::* ገዢው ተጠርቶ የሄደ እና በምድር ላይ "ህጋዊ ባለመሆኑ"፤ ወደ ምድር የሚመጣው በሰው ሕይወት ውስጥ የሚገዛው ለአመራሩና ለአሠራሩ ራሱን በሰጠ ሰው ሕይወት ነው:: ይህ ግን ከአመጽ በፊት በመላው ዓለም ላይ እንደነበረው የአገዛዝ ዐይነት አይደለም:: ይህ "በምርጫ የሆነ አገዛዝ" ወይም "በመሰጠት መግዛት" ብለን የምንጠራው ዐይነት ነው::

2. የዕብራውያን ሰዎች የለመዱት የመስዋእት ሥርዓት፤ እኛም ከጥቂት ጊዜ በኋላ በዝርዝር የምናየው ይህ ሥርዓት፤ ገዢው በምድር ላይ በተሰየ ህዝብ ሥራውን እንዲሠራ አስቻለው:: እነርሱ ደግሞ የመንግሥቱን ወደ መላው ዓለም መመለስን የሚያመለክቱ ነበሩ::

3. ንጉሡ ራሱ ወደ ምድር ይመለሳል፤ በሰው ዘር መካከል ህብረትን ይመሠርታል፤ ይህም ገዢው እንደገና በሰዎች ወስጥ በቋሚነት ለመኖር የሚችልበትን አስፈላጊ መሠረት የሚጥል መንገድ ያመቻችለታል::

የሰውን ፍጥረት እንደገና ለማደስ ፈጣሪው - ንጉሥ ያሰውን መርሃ ግብር መረዳት፤ መላውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አግባብነት ባለው ብርሃን ውስጥ ያስቀምጣል:: መጽሐፉ እርስ በእርሳቸው የተቀጣጠሉ ታሪኮች ስብስብ ወይም፤ የመስዋእት አቀራረብ ዝርዝር መመሪያ ማስታወሻ አይደለም:: የተሃድሶውን መርሃ ግብር ያካተተ የንጉሡን መሻት የሚያሳይ መጽሐፍ ነው::

በዘፍጥረት መጽሐፍ፤ ዘሩ መጥቶ የእባቡን "ራስ ይቀጠቅጣል" ሲል፤ ይህ በመሠረቱ የሚያሳየው እርሱ ራሱ ወደምድር እንደሚመጣ የተነገረ የመጀመሪያው ተስፋ መሆኑን ነው:: እንደ ሰው ሥጋ እንደሚለብስና

እናም ኖህና አብርሃም ከሰማያዊው መንግሥት ጋር የራሳቸውን አቋም አስተካክለው ነበር፡፡

## የእስራኤል ነገድ

አብርሃም በተአምር የተወለደ ልጅ፣ ይስሃቅ፣ ነበረው፡፡ ይስሃቅም መንትያ ልጆች፣ ኤሣውና ያዕቆብ ነበሩት፡፡ ያዕቆብም ሊገለጥ ያለውን ዘር ይሸከም ዘንድ የተመረጠው የዘር ሐረግ ነበር፡፡ በኋላ ላይ የያዕቆብ ስም እስራኤል ተብሎ ተሰይሟል፤ እሥራኤል ማለት "የእግዚአብሔር ልዑል" ማለት ነው፡፡ እርሱም ሊመጣ ያለው የተስፋ ዘር ወራሽ ነበር፡፡ ያዕቆብ አሥራ ሁለት ልጆች ነበሩት፤ የእያንዳንዱም ልጅ ቤተሰብ አደገ፣ ትልልቅ ነገድም ሆነ፤ እንግዲህ የአሥራ ሁለቱ ነገዶች መነሻ ይህ ነው፡፡ ፈጣሪው - ንጉሥ ከያዕቆብ ልጆች መካከል ይሁዳን ሊመጣ ያለውን ዘር የሚሸከም የተለየ የዘር ሐረግ እንዲሆን መረጠው፡፡ ያም ቢሆን ሁሉም ነገዶች ገና ባልተገለጠው ተውኔት ውስጥ የሚጫወቱት የየራሳቸው ድርሻ ተቀምጦላቸው ነበር፡፡

## እስራኤላውያን ፡- የካህናት መንግሥትና የተቀደሰ ህዝብ

በመጨረሻውም፣ በራሳቸው ምድር ላይ ታላቅ ርሃብ ስለነበረ ዐሥራ ሁለቱ ነገዶች ወደ ግብጽ ምድር ወረዱ፡፡ ከያዕቆብ አንዱ በሆነው በዮሴፍ አማካይነት በሰማያዊው አስተዳደር ጣልቃ ገብነት ሕይወታቸው ሊጠበቅ ቻለ፡፡ ዮሴፍም በግብጽ ምድር ገዢ ከነበረው ፈርኦን በታች በሥልጣኑ ሁለተኛ ሰው ነበር፡፡ በመጨረሻው ግን እነዚያ ነገዶች ዮሴፍን በማያውቅ አዲስ ፈርኦን አገዛዝ የግብፅ ባሪያዎች ሆኑ፡፡ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላም፤ ፈጣሪው - ንጉሥ ከሌዊ ነገድ የሆነውን ሙሴ የሚባለውን ሰው እስራኤላውያንን ነፃ ያወጣቸው ዘንድ ጠራው፡፡ ይህም ሊመጣ ያለውን ዘር የትውልድ ሐረግ ከመጠበቅ ዓላማዎቹ አንዱ ነበር፡፡

በሙሴ ሕይወት ውስጥ ያነበብነው ነገር ሁሉ የሚያሣየው፤ በሙሴ ለሰማያዊው አስተዳደር ዓላማ በመስጠት ምክንያት በምድር ላይ የመንግሥቱን አገዛዝ መስፈን ነው፡፡ ለምሳሌ የሙሴ የእንቁራሪትና የዝንብን መንጋ በግብጻውያን ላይ የማምጣት ችሎታው፣ የሰው ልጆች "በምድር ላይ በሚንቀሳቀስ ፍጥረት ሁሉ ላይ" እንዲገዙ እንደሚለው ቃል በንጉሡ መንፈስ ኃይል አማካይነት በፍጥረታት ላይ ሥልጣናቸውን የመለማመዳቸው ምሳሌ ነው፡፡

በቀይ ባህር መከፈል ተአምር ጊዜም የሆነው ተመሣሣይ እውነት ነው፡፡ በዚህም የእስራኤል ልጆች በእግራቸው ባህሩን ለመሻገርና ከሚያሳድዷቸው ግብጻውያን ለማምለጥ ችለዋል፡፡ ሙሴ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የሰማያዊው አስተዳደር አገዛዝ በምድር ላይ ይሰፍንና ብዙ ምልክቶቹም ይገለጹ ዘንድ እንደ መሣሪያ ሆኖ ነበር፡፡



እዚህ ጋ ቆም ብዬ እንደገና ላሣስብ የምፈልገው ነገር አለ፤ አብርሃም፣ ይስሃቅ፣ ያዕቆብ፣ ሙሴና የእስራኤል ህዝብ ተጠብቀው የቆዩት ሃይማኖትን ለመፍጠር አልነበረም፡፡ መላውን ዓለም ከራሱ ጋር የማስታረቅና ገዢውን እንደገና ለመመለስ ያለውን የንጉሡን ግልጽ ዓላማ ለመተግበር የእሥራኤል ሕዝብ እንደመሣሪያ ሆኖ ያገለገለ ህዝብ ነው፡፡ ይህ በራሱ የነገሩ የመጨረሻው ፍፃሜ አልነበረም፡፡ እስራኤላውያን የተለየ ህዝብ ሆነው ተጠሩ ንጉሡን እንዲሁም የተለየና የተቀደሰ ሕዝብ እንዲሆኑ የፈለገበትን የርሱን ዓላማና ምክንያቱን እንደገና እንዲገነዘቡ ነበር የተጠሩት፡፡ ለዚህ ዓላማም ተለዩ፡፡ ቀጥሎ እንደምንመለከተው፤ "የካህናት መንግሥትና የተቀደሰ ህዝብ" እንዲሆኑ ነበር፤ ይህም ንጉሡ ለመላው ዓለም ያለው የተሃድሶ እቅድ ተግባራዊ እንዲሆን እንዲረዱ ነበር፡፡

በዚህ ዐውድ "መንግሥት" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል "ማምላካህ" የሚል ሲሆን ይህም "መግዛት" ማለት ነው፡፡ አሁን ወደ ምድራዊው አገዛዝ ጭብጥ እንመለሳለን፡፡ "መንግሥት" የመግዛትን ሃላፊነት ሲያመለክት፣ የካህናቱ ሚና ሰዎች ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር እንደገና ህብረት እንዲኖራቸው መርዳት ነበር፡፡ በዚህ መሠረተ ሀሳብ፣ የካህናቱ ሥራ ሕዝቡን ወደ ትክክለኛው ሥልጣን ማቅረብ፣ የመንግሥት ሥራ ደግሞ በዚያው ሥልጣን ደግሞ መስራትና መምራትን የሚያካትት ነው፡፡ ፈጣሪው - ንጉሥ በምድር ላይ መንግሥትን ወይም የካህናት መንግሽትን ይፈልጋል፡፡ አዳምና ሔዋን ከማመፃቸው በፊት ከርሱ ጋር እንደነበሩ፣ መላው የእስራኤል ህዝብ ከእርሱ ጋር አግባብነት ያለው ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልጋል፤ እያንዳንዱ የሰው ልጅ ካህን ሊሆን የተፈጠረ ነው - በግሉ ከፈጣሪው - ንጉሥ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሊያደርግ የተፈጠረ ነው - ሊገዛ እና በምድርም ላይ ሊሰለጥን፤ ያ የንጉሡ እቅድ ነው፡፡

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ከግብጽ ምድር በወጡ ጊዜ፤ በእርሱ መታመናቸውንና መታዘዛቸውን ቢቀጥሉ፤ በምድር ላይ ካሉ ህዝብ ሁሉ ታላቅ ህዝብ እንደሚያደርጋቸው ተናገራቸው፡፡ የሚኖሩበትን መተዳደሪያ ሥርዓት ሰጣቸው፤ ይህም ህግ ይባላል፡፡ ይህም እንደ የመንግሥቱ ካህናት እና በህብረት እንደሚኖሩ መሪዎች እንዴት ማሰብና መተግበር እንደሚገባቸው በግልጽ ሁኔታ የተቀመጠ ዝርዝር መመሪያ (ሥዕል) ነው፡፡ ይህንን ህግ ቢያደርጉት፤ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያቀርብላቸዋል፣ ይጠብቃቸዋል፤ የሚፈልጉትን ሁሉ ያገኛሉ፣ በጠላቶቻቸውም ከቶ ተሸናፊዎች አይሆኑም፡፡ ንጉሡ ለገዢው ለሚታዘዙትና ቤታቸውን፣ ማህበረሰባቸውን፣ እና ህዝባቸውን በእርሱ መመሪያ ለሚገዙ ሁሉ ምን እንደሚያደርግላቸው ያሳዩ ዘንድ ሕዝቡ በጠቅላላ እንደ ናሙና እንዲሆኑ ነበረ፡፡

የሚያሳዝነው፤ የእስራኤል ህዝብ ለተጠሩበት ለዚያ ታላቅ ዓላማ አልኖሩም፡፡ ልክ አዳምና ሄዋን እንዳደረጉት ሕዝቡ የንጉሡን ህግ

ተቃወመ:: ከዚያ በኋላ ከእርሱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሊኖራቸው አልቻለም:: በውጤቱም፣ በምድር ላይ ለሌሎች ህዝቦች የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌ ለመሆን ሳይችሉ ቀሩ:: ህዝቡ ወደ ንጉሡ እልፍ እልፍ የተመለሰበት ጊዜ ቢኖርም እንደ ሕዝብ ከሆኑበት ጊዜ አንስቶ ደግመው ደጋግመው ታቃውመውታል:: እንደዚህ ዐይነት ሁኔታዎች በተከሰቱበት ጊዜ ሁሉ፣ ንጉሡ እርሱን የማያውቁ ሌሎች ህዝቦች እንዲነሱባቸውና እንዲገዟቸው አድርጓል፤ በዚህም የእርሱን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ ወደ እርሱም ይመለሳሉ:: በመላው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፣ ህዝቡ እጅግ ብዙ ጊዜ በሌሎች ህዝቦች እንደ ከነዓናውያን፣ ሞዓባውያን፣ ኬጢያውያን ባሉ እጅ ወድቆ እናነባለን::

## የህጉ ትርጉም

የእስራኤል ህዝብ በመጀመሪያው ከግብጽ ባርነት በወጡበት ጊዜ፣ ስለ ንጉሡና ንጉሡ ስለሚሠራበት መንገድ ብዙ ረስተው ነበር:: ስለ ባህርዩና ስለፈቃዱ የነበራቸው መረዳት ጠፍቶ ነበር:: አብርሃም ከንጉሡ ጋር ስለነበረው ግንኙነት አያውቁም ነበር፤ ይሁን እንጂ የአብርሃም ዘሮች እንደሆኑ የደበዘዘ ሀሳብ ነበራቸው:: ይህም እግዚአብሔር ሙሴን ማን እንደሆኑና እንደ ነገሥታትና ካህናት መንግሥት እውነተኛ ዐላማቸው ምን እንደሆነ እንዲነግራቸው ባዘዘው ጊዜ ነበር፤

> *ለያዕቆብ ቤትና ለእስራኤል ሰዎች ሁሉ የምትላቸው ይህንን ነው፤ "በግብጻውያን ላይ ያደረኩትን ሁሉ አይታችኋል፤ በመላእክት ክንፍ እንደተሸከምኳችሁ ወደኔም እንዴት እንዳመጣኋችሁ ተመልክታችኋል:: አሁን እናንተ በሙሉ ልብ ብትታዘዙኝ ቃል ኪዳኔንም ብትጠብቁ ከማንኛውም ህዝብ ይልቅ የከበረ ሀብት ትሆኑልኛላችሁ:: ምድርና መላዋ የእኔ ቢሆንም፤ እናንተ የካህናት መንግሥትና የተቀደሰ ህዝብ ትሆኑልኛላችሁ::" ለእስራኤል ልጆች የምትናገራቸው ቃሎቹ እነዚህ ናቸው::*

በእነዚህ ቃላት፣ ንጉሡ ከእስራኤል ልጆች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት፣ እነርሱም ከእርሱ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት መሠረተ:: ከዚያ በኋላ ህዝቡ ሁሉ እርሱን ለመገናኘት በቀጥታ ወደ ተራራው እንዲወጡ እንዲነግራቸው ሙሴን አዘዘው:: እግዚአብሔር የፈለገው ሕጉን በቀጥታ ሊሰጣቸው ነበረ፤ አንድ ሰው ብቻ አገናኝ (አስተላላፊ) ሆኖ እንዲሰማው አልፈለገም፤ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ወደ እርሱ እንዲመጡ እና እንዲሰሙ ነበር የወደደው፤ ምክንያቱም ህዝቡ ሁሉ ገገርዎችና ካህናት እንዲሆኑ አቅዶ ስለነበር ነው:: ወደ ተራራው በመጣ ጊዜ፣ ንጉሡ ሊናገራቸው ወረደ፣ ሕዝቡም የንጉሡን ኃይልና ታላቅነት ባየ ጊዜ ፈራ:: ሙሴም እንዳይፈሩ ግን ንጉሡን ማክበር እንዳለባቸው ነገራቸው:: ነገር



ግን ከዚህ ይልቅ ሙሴ እንደ ሽምጋይ (መካከለኛ) ሆኖ እንዲያገለግላቸው ፈለጉ::

እንደገና፣ ንጉሡ ለህዝቡ እንደርሱ ባህርይ መኖር ማለት እንዴት እንደሆነ የሚያሳውቃቸውን ሕግ ሰጣቸው:: የንጉሡ የመጨረሻ ዓላማው (ፍላጐቱ) ሕጉ በድንጋይ ወይም በወረቀት ላይ ተጽፎ እንዲቀመጥ አልነበረም:: በልባቸው፣ በመንፈሳቸው ውስጥ እንዲቀመጥ ነበር ያቀደው:: የመጨረሻ እቅዱን በነቢዩ ኤርምያስ አፍ እንዲህ በማለት ነበር የገለጸው፤ "ከዚያ ጊዜ በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው . . . ህጌን በአዕምሯቸው አኖራለሁ፣ በልባቸውም ላይ እጽፈዋለሁ፤ እኔ አምላክ እሆናቸዋለሁ፣ እነርሱም ህዝብ ይሆኑልኛል:: " ይህ በቀጥታ በመጨረሻው ገዢው እንደሚመለስና በሰዎች ውስጥ እንደሚኖር የሚያመለክት ነው::

ለጊዜው ግን ወደያዝነው ሃሣብ እንመለስ፤ ሙሴ የህጉን ጽህፈት ተቀበለ፣ ይህም የመንግሥቱ ህግና መርህ ወይም ለህዝቡ የተሰጠ፤ "የመንግሥቱ ሥነ ሥርዓት ነበር:: ንጉሣቸው የእርሱ መንፈስ እንዴት እንደሚያስብና መንግሥቱ እንዴት እንደሚሠራ እንዲያውቁ ይፈልግ ነበር:: እንዲህ ያደረገውም ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ጠብቀው መጓዝ እንዲችሉ ነው:: ህዝቡ የንጉሡን ህግ የሚታዘዙ ከሆነ መንፈሱ ይደሰታል፤ ምክንያቱም በቅድስናና ከእርሱ ባህርይ ጋር ህብረታቸውን ጠብቀው ስለሚኖሩ ነው::

ሙሴ ከንጉሡ ጋር ከተገናኘ በኋላ ከተራራው በወረደ ጊዜ፤ ህዝቡ ህጉን ለመታዘዝ ተስማሙ:: ይሁን እንጂ እንደተመለከትነው ይህ ቃላቸው ለብዙ ጊዜ አልቆየም:: በመጨረሻው የሙሴ ምክትል የነበረው ኢያሱ፣ ንጉሡ ቃል ወደ ገባላቸው ምድር አስገባቸው:: በእዚህ ስፍራ ላይ እጅግ አስደናቂ ተአምራት ተከናውነው እንመለከታለን፤ ለምሣሌም የዮርዳኖስ ወንዝ መከፈል፣ የእያሪኮ ከተማ ቅጥር መፍረስ፣ ከጠላቶቻቸው ጋር ባደረጉት ጦርነት ወቅት ለሙሉ ቀን ያህል ፀሐይ ሳትጠልቅ መቆየቷ ጥቂቶቹ ናቸው:: እነዚህ ተአምራት የሚያረጋግጡት ነገር ቢኖር በፍጥረታዊው ግዝፈ ዓለም ላይ የመንግሥቱን አገዛዝ ነበር:: ይሁን እንጂ እነኝህ ሁሉ ተአምራት ሰማያዊው መንግሥት በመካከላቸው እንዳለ ቢያሳዩም፤ ህዝቡ ከንጉሡ ፈቃድ ዘወር አሉ:: ከመንግሥቱ ዜጎች ውጭ ያሉትን የአህዛብ ሴቶች አገቡ፤ ንጉሡ ባልፈቀደላቸው መንገድ እንደ ሌሎች ንጉሡን እንደማያውቁ ህዝቦች አደራረግ አደረጉ:: ቀስ በቀስም ከእርሱና ከመንግሥታዊ እቅዱ ተለዩ::

> **ፈጣሪው - ንጉሥ ሰዎች እንደርሱ ባሕርይ መኖር እንዴት እንደሆነ እንዲያዉቁ ሕግ ሰጣቸው::**

## ክህነትና መስዋእቶች

እንግዲህ ክህነት የተጀመረው እዚህ ጋ ነው። የእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍላጐት "ካህናት" የሚባል አንድ የተለየ ቡድን እንዲኖር እንዳልሆነ አምናለሁ። እርሱ ፈልጎ የነበረው መንግሥት ወይም የካህናት መንግሥት እንደነበር ልብ በሉ። ይሁን እንጂ እስራኤላውያን እርሱን መሰል ህዝብ ሆነው እንዲቀጥሉ ስለፈለገ፣ በእርሱ ላይ ባመጹ ጊዜና የመንግሥቱን ሥርዓቶች በጣሱ ጊዜ እንደገና የሚታደሱበትን መንገድ ሰጣቸው።

የካህናት መንግሥት ሆነው መጠራታቸውን በተው ጊዜ ንጉሡ የሙሴ ወንድምና ከሌዊ ነገድ የሆነውን አሮንንና ልጆቹን የመንግሥቱ ካህናት ይሆኑ ዘንድ ሾማቸው። በተጨማሪም ደግሞ እነኝህን ካህናት ይረዱ ዘንድ ከእስራኤል ልጆች መካከል ከሌዊ ነገድ የሆኑ የተወሰኑ ሌሎች ሰዎችን እንዲለይ ሙሴን አዘዘው። ካህናቱ ራሳቸውን ለንጉሡ ቀድሰው ሊጠብቁ ያስፈልጋቸዋል። በንጉሡ በተደነገገው ህግ መሠረት የመስዋዕት ስርዓቶችን በማቅረብ፤ የእስራኤልን ልጆች አመጽ በማስተሰረይ (በደላቸውን በመክደን)፤ ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደገና እንዲቀጥሉ ያደርጋሉ። በዚህ መንገድ፤ ገዢው የንጉሡን ፈቃድ ለህዝቡ ሊገልጽላቸው ችሏል፤ በእነርሱም በኩል የመንግሥቱ ባህል ወደ ምድር መጥቷል። የዚህ ሁሉ ነገር ውጤቱ፤ በምሣሌነታቸው በምድር ሁሉ ያሉ ሰዎችን ወደ ንጉሡ ያቀርቡ ዘንድ ነበር። በመሆኑም መስዋእቶቹ ሁሉ፣ ደሙን የሚያካትቱ የመስዋዕት አቀራረብ ስርዓቶች፣ ይቃጠሉ የነበሩ የእጣን መስዋእቶች፣ የመገናኛው ድንኳን የተለያዩ ክፍሎች፣ እናም መቅደሱ - የእነኝህ ሁሉ ነገሮች ዓላማ ህዝቡን እንደገና ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ፤ በዚህም አስቀድመው በተጠሩበት የጥሪ ዓላማ ውስጥ ለመክተት ነበር።

ካህናቱ የሚያቀርቧቸው መስዋእቶች የእንስሳትን መስዋእት ያካትት ነበር፤ ምክንያቱም ሰዎች የፈጠሩት የአመጽ፣ የግድያና የሞት ባህል ዕዳ ሊከፈል ያስፈልግ ስለነበር ነው። እንዲሁም የግለሰቦች የንጉሡ ሕግ ጥሰት ይካተታል። የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "እንደ ህጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነፃል፤ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።" በመሆኑም በመስዋዕት አቀራረብ ሥርዓት ውስጥ፤ ደሙ፣ ህዝቡ በመንግሥቱ ሕግ ላይ ስለፈፀሙት አመጽ ያስተሰርይ ዘንድ የሚፈስ ነው።

እጅግ ውስብስብ የሆኑትን ነገሮች ማለትም፤ ስለ ክህነት ልብስ፣ የአምልኮ ሥርዓትና ስለሚቀርቡት የእንስሳት መስዋእቶች ዝርዝር መመሪያዎች በምናነብበት ጊዜ፤ ሀሣባችን በጥቃቅን ነገሮች ይያዝና ጥቅል የሆነውን ዓላማቸውን እንስታለን። የንጉሡ የመጨረሻ የሆነው የግቡ



መርሃግብር፣ ካህናት፣ የክህነት ልብሶች፣ እጣኑ፣ ህብስቱ፣ መጠጫዎቹ፣ ቅድስተ ቅዱሳኑና አደባባዩ አልነበረም። አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ነገሮች ልክ ሚስጥራዊ እንደሆኑ ሃይማኖታዊ ነገሮች አድርገው ይመለከቷቸዋል። ይልቅስ እነዚህ ወደ ፍጻሜው የሚያመጡን መንገዶች ናቸው። እነርሱ በእግዚአብሔር (ጊዜያዊ የሆነ መርሃ ግብር) ውስጥ፤ እርሱንና ህዝቡን እንዲያገናኙና በዚህም ሣቢያ መንፈሱ (አሁን በመካከላቸው የሌለው ገዢ) ወደ እነርሱ እንዲመጣና ሁኔታዎችን እንዲለውጥ የሚያስችሉ ነገሮች ናቸው።

በብሉይ ኪዳን የነበሩት የመስዋዕት አቀራረብ ሥርዓቶች የመጨረሻ ግብ መርሃ ግብር የታቀደው፣ ህዝቡን የሚያነሳሳውና እያደገ የሄደውም ለዚህ ዓላማ ነበር። ሊቀ ካህኑ ወደ ውስጠኛው ክፍል በገባ ጊዜ (በኋላም ቅድስተ ቅዱሳን ተብሏል)፤ መስዋእቶቹ ተቀባይነት የሚያገኙ ት በህዝቡ ስም ነበር፤ በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ሊመጣና በኪሩቤሎቹ መካከል በነበረው የስርየት መክደኛ ላይ ሊቀመጥ ይችላል፤ ምክንያቱም ለቅድስና የሚያስፈልገው መስፈርት ተሟልቷል።

> **ጊዜያዊ መስዋእቶች ገዢውን በህዝቡ መካከል ያመጡ ነበር እንጂ ወደ ውስጣቸው አያስገቡም**

ወደ መንፈሱ የሚቀርብ ማንኛውም ነገር የተቀደሰ ሊሆን ይገባው ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ የተቀደሰ መንፈስ ነው። የመስዋእቱ ደም የሚያነጻው ህዝቡንና ቅድስተ ቅዱሳን ተብሎ በሚጠራው የመቅደሱ የውስጠኛው ክፍል ውስጥ በገዢው ፊት ለፊት የሚቆመውን ካህኑን ጭምር ነው። ከእነዚህ መስዋእቶች የተነሣ እጅግ ውብ የሆነ ነገር ተከስቷል። መንፈሱ ተመልሶ መጥቷል። ገዢው በምድር ላይ ተገኝቷል፣ ጊዜያዊ መስዋእቶች በሙሉ ገዢው በህዝቡ መካከል እንዲገኝ አድርገዋል እንጂ ወደ ውስጣቸው አላስገቡም ነበር። ገዢው በዚያን ጊዜ ወደ ሰዎች ውስጥ መግባት አይችልም ነበር፤ ምክንያቱም ቋሚ የሆነው መስዋእት ገና አልተዘጋጀም ነበር።

ሕዝቡ ያለማቋረጥ በሰማይ መንግሥት ላይ ያምጽ ስለነበር የእንስሳት መስዋእት በተደጋጋሚ መቅረብ ነበረበት። ምንም እንኳን መስዋዕቱ አመጸኛ ተፈጥሯቸውን ሊለውጠው ባይችልም ሰማያዊው መንግሥት በሕይወታቸው ጣልቃ እንዲገባ መንገድ የሚከፍት ጊዜያዊ የኃጢአት ማስተሰሪያ መንገድ ነበር።

በማናቸውም ጊዜ፣ የእስራኤል ልጆች አካሄዳቸውን ከንጉሡ ጋር ባስተካከሉ ጊዜ መንፈሱ በመካከላቸው ይገኛል፤ ሁሉንም ጦርነቶች ያሸንፋሉ፣ ከመካከላቸው በሽታ ይርቃል፣ ሰላምም ይሰፍናል። ለምን? ምክንያቱም እንደገና እንደ እውነተኛ ሰዎች መኖር ስለሚጀምሩ ነው። ገና

ከመነሻው ጀምሮ ሊኖሩ የተፈጠሩትና የታሰበላቸው ሕይወት ከካባቢያቸውና ከሁኔታዎች በላይ ሆነው እንዲኖሩ ነው።

ሕዝቡ ሰላም እንዲኖራቸው፣ እንዲበለጽጉ እና ሰማያዊ መንግሥትን በሚወክል ሕይወት ድርሻቸውን ይፈጽሙ ዘንድ፤ ገዢው በመገናኛው ድንኳን (በመቅደስ) በውስጠኛው ክፍል ማለትም በቅድስተ ቅዱሣን ውስጥ መገኘቱን ለማረጋገጥ ካህናት እጅግ ውስብስብ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ያልፋሉ። ህዝቡ እግዚአብሔርን ባልታዘዘ ጊዜ፤ መንፈስ ቅዱስ ጥሏቸው ይሄዳል፤ እናም ሕይወታቸው እንደገና ይመሰቃቀላል። በመስዋእቶቹ እማካይነት ምህረትን በተቀበሉና እንደገና እግዚአብሔርን በታዘዙ ጊዜ፤ መንፈስ ቅዱስ እንደገና ወደነርሱ ይመለሳል፤ ስኬታሞችም ይሆናሉ።

የመስዋእቱ ሥርዓት፤ ምንም እንኳን የሰውን ልጆች ከሰማያዊው መንግሥት ጋር የለየውን ችግር ሙሉ ለሙሉ ለመፍታት በቂ ባይሆንም ለዓላማው ውሏል። በመሠረቱ ይህ ጊዜያዊ የሆነው መንጻት የሚያመለክተው ህዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እስከ መጨረሻው ሊያቆይላቸው እንደማይችል ነበር። ደሙ "ይረጭባቸው" ነበር፤ ምክንያቱም የእንስሳት ደም አቅራቢውን ግለሰብ ከውስጥ ወደ ውጭ ለዘለቄታው ሊያነጻው ስለማይችል ነው። በመሠረቱ የወንዶችም ይሁን የሴቶች ልብ ያለማቋረጥ ክፉ ነው። ያልተቀደሰ (ከእራሱ ጋር ያልተስማማ፤ ያልተለየ) የሰው ልብ ክፉን የማድረግ ችሎታው ሁልጊዜም ከአፍንጫው ጫፍ ላይ ነው፤ እናም ሁልጊዜ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ፈጥኖ ይገለጣል።

ይሁን እንጂ ይህ የፈጣሪው ንጉሥ ከሰዎች ጋር አብሮ ለመስራት ያዘጋጀው ጊዜያዊ መርሃ ግብር ነው፤ ገና በውስጣቸው መኖር አልቻለም፣ ምክንያቱም ደግሞ ያለመቀደሳቸው ነው፣ በዚህም ሁኔታ ውስጥ እንኳን አገዛዙን ሊያሰፍን ይፈልግ ነበር። በሕዝቡ መካከል ለመሥራት በመስዋእቶቹ ሥርዓቶች አማካይነት የራሱን የቅድስና ከባቢ ፈጠረ፣ ይህንንም ያደረገው ንጽህናውና ከራሱ ጋር ያለው ህብረት በማይጋጭበት ሁኔታ ነው። የእስራኤል ነቢያት፣ ካህናትና ነገሥታት ንጉሡን በመወከል በምድር ላይ እንዲናገሩ ወይም አንድ ነገር እንዲያደርጉ ሲፈለግ የተወሰነ ጊዜ የንጉሡ መንፈስ በእነርሱ ላይ ይመጣ ነበር።

ብዙ ሰዎች በብሉይ ኪዳን ስለነበሩት የመስዋእት አቀራረቦች ሊያጠኑና ለሌሎችም ሊያስተምሩ ይወዳሉ። እንዲያውም አንዳንዶች በርከት ያለ ገንዘብ ያስገኙላቸውን መጻሕፍት ጽፈዋል፤ "የመገናኛው ድንኳን ዐስር ቁልፎች" በተሰኙ ህትመቶቻቸው አብራርተዋቸዋል። ብዙ ሰዎች የእነዚህን ነገሮች እውነተኛ ምንነት እንዳልተገነዘቧቸው ተረድቻለሁ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ (የእነዚህኞቹ የከፋ ነው) እነኝህን ነገሮች በማግዘፍ በሚያስተምሯቸው ትምህርቶች ሰዎችን ይበዘብዛሉ። እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ግብ አይደሉም። ሁልጊዜም ማስታወስ ያለብን፣



ጠቅላላ ዓላማቸው ለሰው ዘር ጥቅም ሲባል የሰማያዊውን መንግሥት አገዛዝ በምድር ላይ ለማምጣት የሚያስችሉ መንገዶች እንደነበሩ ነው።

## ነገሥታት

እስራኤላውያን በዙሪያቸው እንደነበሩት ሌሎች ህዝቦች፣ ተመሣሣይ ደረጃና የአኗኗር ዘይቤ እንዲኖራቸው፣ በመፈለጋቸው ምክንያት የራሳቸው ምድራዊ ንጉሥ እንዲኖራቸው ጠይቀው ነበር። ፈጣሪው - ንጉሥ ጥያቄያቸው የሚያስከትለውን ውጤት እንዲህ ሲል ተናገራቸው፤ "አይደለም፤ እናንተ በእውነቱ ምድራዊ ንጉሥ አያስፈልጋችሁም። ንጉሡ ቀረጥን በእናንተ ላይ በመጣልና የጉልበት ሥራ በማሠራት ይበዘብዛችኋል። እኔ ሁሉን ነገር የሰጠኋችሁ፣ መልካም የሆነውንም ነገር ሁሉ ያደረኩላችሁ ንጉሣችሁ ነኝ"። እንደገናም ሲናገራቸው ምከረ፤ "እናንተ እንደ ሌላ ህዝብ አይደላችሁም። እናንተ ለእነርሱ ምሳሌ ልትሆኑ የሚጠበቅባችሁ ናችሁ። እናንተ የኔ መንግሥት መሳይ እንድትሆኑ የታሰባችሁ ናችሁ።"

ሰብአዊ ነገሥታት ለህዝቡ የሰማያዊው ንጉሥ የመጨረሻ እቅድ አይደሉም። እርሱ የፈለገው ሁሉም የግዛቱ ገዢዎች መንግሥት በእርሱ እንዲመሩ ነው። ይህ ሀሳብ የሚያንፀባርቀው የርሱ የመጨረሻ ግብ በምድር ላይ የሚኖር ማንኛውም ዜጋ ከዋናው ገዢ በታች ሆኖ የአካባቢው ገዢ በመሆን ሥልጣን እንዲለማመድ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ የእስራኤል ልጆች ንጉሥ እንዲኖራቸው የግድ አሉ፤ በመሆኑም የሚፈልጉትን ሰጣቸው።

ህዝቡ ንጉሥ እንዲኖራቸው መፈለጋቸው የሚያመለክተው፤ ከሰማያዊው ንጉሥ ጋር ህብረት ማጣታቸውንና የተጠሩበትን ዓላማ ሙሉ ለሙሉ ያልተገነዘቡት መሆኑን ነው። ለነቢዩ ሳሙኤል ንጉሥ እንደሚፈልጉ ከነገሩት በኋላ፤ "ጌታም ሳሙኤልን እንዲህ ሲል ተናገረው፤ ህዝቡ ሁሉ የተናገሩህን ነገር አድምጣቸው፤ የናቁት እኔን ንጉሣቸውን እንጂ አንተን አይደለም።" እንደገና ሰማያዊውን ንጉሣቸውን ናቁ።

ይሁን እንጂ ንጉሡ የመቤዠት ዓላማውን ለመፈፀም የነገሥታትን ተቋም ተጠቀመበት። በእስራኤል ላይ ሁለተኛ ንጉሥ የሆነው ዳዊት፣ የሰማያዊው አስተዳደር የሚሻውን ነገር የሚሻ ንጉሥ ነበር። በሕይወቱ የሰማያዊው መንግሥት አገዛዝ እጅግ በብዙ መንገዶች ተገልጧል። ገና ወጣት ሳለ ግዙፍ የሆነውን ሰው ጎልያድን አስገራሚ በሆነ ሁኔታ መግደሉ፤ ሰዎች

> ሰብአዊ ነገሥታት የፈጣሪው - ንጉሥ የመጨረሻ ዕቅድ አይደሉም፣ እርሱ የፈለገው የግዛቱን ገዢዎች መንግሥት ነው።

*ህጻን ተወልዶልናልና፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፣ ሃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል:: ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያፀናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግስቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም::*

የማይታየውና የዘላለም መንግሥት ንጉሥ ንብረቱ (ምድር) እንደገና እንዲመለስ እየጠየቀ ነው:: ቅኝ ግዛቱ ሲመለስለት፣ አስተዳደሩን በምድር ላይ እንደገና ይመሰርታል እንደገናም ደግሞ መንፈሱን ገዢ አድርጎ ይሾማል:: ኢየሱስ፣ ንጉሡ በምድር ላይ አገዛዙን ለማስፈን ያለውን እቅድና በምድር የሚኖሩትም አብዛኞቹ እርሱ ራሱ መጥቶ ሁኔታዎችን እስኪያስተካክል ድረስ እንደሚቃወሙት ስለ ራሱ እንዲህ ሲል ምሳሌ ተናግሯል፤

*የወይን እርሻ ያለው ሰው ነበር፤ ቅጥርም ቀጠረለት፤ መጥመቂያም ማሰለት፤ ግንቡንም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ:: የሚያፈራበትም ጊዜ ሲቀርብ ፍሬውን ሊቀበሉ ባሮችን ወደ ገበሬዎች ላከ:: ገበሬዎቹም ባሮቹን ይዘው አንዱን ደበደቡት አንዱንም ገደሉት ሌላውንም ወገሩት:: ደግሞ ከፊተኞቹ የሚበዙ ሌሎች ባሮችን ላከ እንዲሁም አደረጉባቸው:: በኋላ ግን ልጀንስ ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከባቸው:: ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ እርስ በእርሳቸው፤ ወራሹ ይህ ነውና ኑ እንግደለውና ርስቱን እናግኝ ተባባሉ፤ ይዘውም ከወይኑ አትክልት አወጡና ገደሉት:: እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ በሚመጣ ጊዜ በእነዚህ ገበሬዎች ምን ያደርግባቸዋል ... የወይኑንም አትክልት ፍሬውን በጊዜው ለሚያስረክቡ ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጣቸዋል::*

## የሚመጣው ንጉሥ ሃላፊነት

የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ የሚጨርሰው ነቢዩ ሚልክያስ ከ ሰማያዊው አስተዳደር ስለሚመጣው ሰማያዊ ንጉሥ የተናገረውን ቃል እንዲህ ሲል በማወጅ ነው፤ "መጥቶም . . . እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፤ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል::" ይህም የዘሩ ማለትም ነቢዮ "መሲህ" እንደሆነ የገለጸው ዘር ኃላፊነት ነው፤ እርሱም የአዳምንና የሄዋንን ዘሮች ከፈጣሪው ንጉሣቸው ጋር ያስታርቃል:: ይህ በተፈፀመ ጊዜ፣ ገዢው በምድራዊ መኖሪያው (በነርሱ) ውስጥ ለመኖር ይመለሳል::

> **የዘለዓለማዊው መንግሽት ንጉሥ ርስቱን ሲወስድ ነው::**



## የገዢው መመለስ ለሰው ዘሮች ሁሉ ነው

ከሰማያዊ መንግሥት ዋነኛ ከሆኑት መልዕክቶች መካከል የገዢውን መመለስ አስመልክቶ ነብዩ ኢዮኤል አንዱን እንዲህ ሲል ያስተላልፋል፤

*"ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በስጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሣለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆችም ትንቢትን ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎችም ህልምን ያልማሉ፤ ጎበዞቻችሁም ራዕይን ያያሉ::"*

ነቢዮ ኢዮኤል የሚናገረው፤ "ንጉሡን እንዴት መታዘዝ እንደሚገባን እናውቅ ዘንድ ህጉን ማንበብም ይሁን ማጥናት የማያስፈልገን ጊዜ እንደሚመጣ ይታየኛል፤ ምክንያቱም የእርሱ መንፈስ በወጣቶችና በሽማግሌዎች ላይ ይመጣል፤ አስቀድመው ንጉሡን ለመታዘዝ ያልወደዱትን ያህል አሁን ሲታዘዙት ይወዳሉ::" ከዚያ በኋላ "የተመረጡ መሪዎች" የሚባሉ በገዢው የሚገዙ የተወሰኑ ግለሰቦች አያስፈልጉም:: መንፈሱን ያጡት የሰው ልጆች ሁሉ ናቸው፤ ኢዮኤልም የሚናገረው መንፈሱን የሚያፈስው "በሰዎች ሁሉ" ላይ ነው እያለ ነው - በወንድና ሴቶች፣ እስራኤላዊና እስራኤላዊ ባልሆነ፣ በጨዋና በባሪያ ሁሉ ላይ ነው:: ምድራዊ የሆነው መመዘኛ ከጾታ፣ ከዘር ወይም ከማህበራዊ ደረጃ ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ በገዢው መመለስ እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚሻሩ ይሆናሉ::

መንፈስ ቅዱስ የታቀደው ለተወሰኑ ሃይማኖቶች ወይም ብሔሮች ብቻ አይደለም:: መላው የሰው ዘር በውስጣቸው ይኖር የነበረውን መንፈስ ቅዱስን አጥተዋል፤ እናም ንጉሡ በዓለም ላይ የሚኖሩ ሁሉ በዘሩ በኩል ወደ ሕይወታቸው እንደገና እንዲያስገቡት ይፈልጋል:: ለመላው የሰው ዘር ገዢው የሕይወታቸው ቁልፍ ነው::

## ንጉሡ ተመልሶ የሚመጣበት ዘመን

የነቢዩን የኢዮኤልን መልዕክት በሰሙበት ጊዜ፤ ለእስራኤል ልጆች የመንፈስ በሰዎች ላይ የመምጣቱ ሃሣብ ምናልባትም የማይታመን ነገር ይሆናል:: በእነርሱ ልምምድ መንፈስ ቅዱስ የሚመጣው በካህናት፣ በነቢያትና በአንዳንድ ነገሥታት ላይ ብቻ ነው:: ወይም ደግሞ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በሁለቱ ኪሩቤሎች መካከል በሚገኘው በስርየት መክደኛው ላይ ነው:: ኢዮኤል መንፈሱ የሚመጣበትን ጊዜ፤ "የጌታ ቀን" እያለ ነው የሚጠራው:: በዚህ አውድ "ቀን" ማለት "ዘመን" ወይም "ዕድሜ" ማለት ነው:: በመሆኑም የጌታ ቀን ማለት ንጉሡ ወደ ምድር የሚመለስበትን ዘመን የሚያመለክት ይሆናል::

"ጌታ" የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ ላይ፤ "በራሱ ፀንቶ የኖረ ወይም ዘላለማዊ" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ይወክላል:: የነቢዩ መልዕክት፤

“የእንስሳት መስዋእት ወይም የሌሎች መስዋእቶች አቀራረብ፤ የሰው ዘር ከንጉሡ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት እንደገና ሲያድሱ ብቃት የላቸውም፤ በመሆኑም ንጉሡ ራሱ ይመጣል” የሚል ነው። ወደ ምድር በመጣ ጊዜ መንፈሱም አብሮ ይመሰሳል። ገዢው በወጣቶችና በሽማግሌዎች፣ በወጣት ሴቶችና በአሮጊቶች ላይ ይመጣል። ከዚህም በላይ ደግሞ፣ አንድ ጊዜ እንደገና በሰው ዘሮች ውስጥ ለመኖር ይችላል።

ነቢዩ ሚልክያስ፣ ንጉሡ ራሱ ከመምጣቱ በፊት የንጉሡን እንደገና የመመለስ ተስፋ የተናገረ የመጨረሻው ነቢይ ነው። ሰማያዊው መንግሥት ይህንን መልዕክት ሰጥቶታል፦

*“እነሆ መልዕክተኛዬን እልካለሁ፤ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል፤ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፤ የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልዕክተኛ እነሆ ይመጣል፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።”*

የመጀመሪያው መልዕክተኛ መንገድን “ያዘጋጀል”። ሁለተኛው መልዕክተኛ “የቃል ኪዳኑ መልዕክተኛ ደግሞ “የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፤ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።” ይህ መልዕክተኛ፤ “የምትፈልጉት ጌታ” ተብሎ ተገልጾልናል። የቃል ኪዳኑ መልዕክት ምን ነበር? የመንፈሱ ወደ ሰው ዘር እንደገና መመለስ ነው፤ ይህ ደግሞ ገና ከመነሻው ዐመጽ ጀምሮ የተነገረ ተስፋ ነው።

## የንገሡ መድረስ መታወጅ

ከብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ ከሚልክያስ ወደ አዲስ ኪዳን የመጀመሪያው መጽሐፍ ወደ ሆነው ማቴዎስ ወንጌል ስንገባ፤ የንጉሡን መምጣት መንገድ ጠራጊ መልዕክተኛ በድንገት እናገኘዋለን፤

*“በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሃ ግቡ ብሎ በምድረ በዳ እየሰበከ መጣ። በነቢዮ ኢሣያስ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጥርጊያውንም አቅኑ፤ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና።”*

“መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና”። በሌላ አባባል፣ የንጉሡ መንግሥት በደጅ ናት ማለት ነው፤ ምክንያቱም ንጉሡ ወደ ምድር መጥቶ ነበር። የዚህ መልእክት ጭብጥ ምንድን ነው? ገዢው። መጥምቁ ዮሐንስ እንደተናገረው፤ “እኔ ለንስሃ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ከእኔ በኋላ ግን ከእኔ የሚበረታው ይመጣል፤ እኔ ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር ልፈታ እንኳን አይገባኝም፤ እርሱ መጥቶ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል።”



ንጉሡ መጥቶ በመንፈሱ “ያጠምቃቸዋል”፣ በመሆኑም ከመንግሥቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያስተካክላል። የመንፈሱ መምጣት ከዚህ በኋላ በቋሚነት እንጂ ለጊዜው ብቻ አይደለም። ገዢው እንደሚባላ እሳት ትክክለኛ ያልሆኑ አመለካከቶችንና ፍልስፍናዎችን ያቃጥላል፤ በዚህም ህዝቡን ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ያለያዩትን እነዚህን ነገሮች ያስወግዳል። ግራ መጋባታቸውን ሁሉ ወደ መረዳት ያመጣል፣ የሕይወታቸውን ዓላማ ወደ ስኬት ለማምጣት ያላቸውን የእውቀት ርሃብ ያጠግባል። በመጨረሻም ከንጉሡና ከመንግሥቱ ጋር ለዘለቄታው እንደገና ይጣበቃሉ። ምድርም እንደገና የቅድስናና የኃይል ቅኝ ግዛት ትሆናለች፤ ምክንያቱም ነዋሪዎቿ አንዴ እንደገና ለመጨረሻ ጊዜ የቅድስናና የኃይል መንፈስ በውስጣቸው ይኖራልና ነው።